

# ፈለገ ጥበብ







www.ethiopianorthodox.org



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ
ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለሃይማኖት



www.ethiopianorthodox.org

# ፈለገ ጥበብ

1ኛ ዓመት ቁጥር 1

ሐምሌ 1991 ዓ.ም

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ

በየ 6 ወሩ የሚዘጋጅ መጽሔት


## ከአዘጋጁ ብዕር

ክብርና ምስጋና ለእግዚአብሔር ይድረሰውና እነሆ ከሃያ አንድ ዓመታት በኋላ ፈለገ ጥበብ ዳግም ትንሣኤ አገኘች። የጥበብ ምግብ ልትመግበን፣ የጥበብ መጠጥ ልታጠጣን።

በመሠረቱ የጥበብ ምንጭ ራሱ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። በመሆኑም ከእውነተኛው ምንጭ መጠጣት የሚቻላቸው በሥጋውና በደሙ በቀየሰው ጐዳና መራመድና ፈለጉን ተከትለው መጓዝ የሚችሉ ብቻ ናቸው። ዛሬ «በኢየሱስ» ስም በርካታ የሐሰት መንገዶች ተቀይሰው ሰውን ወደተሳሳተ አቅጣጫ ሲመሩት ይታያሉ። የትኛው ከየትኛው ለመለየት በሚያስቸግርበት ሁኔታ ባለንበት ሰዓት ትክክለኛውን መንገድ ተከትሎ ለመጓዝ ጠንካራ ሃይማኖትና የጸና ዓላማ ይዞ መገኘት ያሻል።

በተለይ ወጣቱ በዚህ በኩል ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ይጠበቅበታል። ፈለገ ጥበብ ለዚህ የድርሻዋን ለማበርከት አንድ ብላ ጀምራለች። በዚህ አጋጣሚ የመጽሔቷ ባለቤት የሆነው ወጣቱ ተሳትፎው ወሳኝ መሆኑን ለማስታወስ እንፈልጋለን። ከሁሉ በላይ ግን የአበው ሊቃውንት ድጋፍ፣ ምክርና ጸሎት ያስፈልገናል። ዕውቀትን፣ ትውፊትን ለትውልድ አውርሶ ከማለፍ የተሻለ ጸጋ የለምና ከምሁራን አባቶች የሚሰጠን ምላሽ ቀና እንደሚሆን እምነታችን ነው።

ከዚህ በተረፈ ይህ ይሻሻል፣ ይህ ይጨመርበት፣ ወዘተ የሚሉ ገንቢ አስተሳሰቦችና ትምህርታዊ ጽሑፎችን፣ ጥቆማዎችን ከናንተ ከአንባብያን እንጠብቃለን።

እግዚአብሔር ከሁላችን ጋር ይሁን

## ማውጫ


❖ የቅዱስ ፓትርያርኩ መልእክት . 4

❖ የሰንበት ት/ቤት

አመሠራረትና ዕድገት . . . 5

መድፍነ ፀር

❖ ክብረ ቅዱሳን . . . . . 8

ከወጣቱ ለወጣቱ . . . . . . . . 13

ሥርዓተ ቤተክርስቲያን

❖ የቤተክርስቲያን ሥርዓት . 20

እኔም ወጣት ነበርኩኝ

❖ አርበኛው መነኩሴ . . . 22

ሥነ ልቡናዊ አገልግሎት ለወጣቶች

❖ የአሸናፊነት ምሥጢር . 28

እስትግቡእ . . . . . . . . 33



አዘጋጅ ካሕሳይ ገ/እግዚአብሔር

ስልክ 11 23 69

550099/98

ፖ.ሣ.ቁ. 81286

አዲስ አበባ



www.ethiopianorthodox.org

# የብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ መልእክት

በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን ።

## « ህየንተ፡ አበውኪ፡ ተወልዱ፡ ለኪ፡ ደቂቅ፡ በአባቶች፡ ፈንታ፡ ልጆች፡ ተወለዱልሽ፡ » !

መዝ. ፵፬፡ ፲፮

እናንተ፡ የዛሬ፡ ወጣቶች፤ የነገ፡ አባቶች፤ እናቶች፡ ናችሁ ፤ እኛ፡ ለእናንተ፡ ስናስረክብ፤ እናንተም፡ በተራችሁ፡ ለተተኪው፡ ትውልድ፡ ታስረክባላችሁ ። ይህንን፡ ጥንታዊ፡ አደራ፡ ተረክባችሁ፡ ኃላፊነትን፡ በአግባቡ፡ ለመወጣት፡ የምትችሉት፡ ዛሬ፡ በምታደርጉት፡ ንቃት፡ የተሞላበትና፡ ትጋት፡ የታከለበት፡ እንቅስቃሴ፡ ነው ። ሃይማኖታችሁን፤ ትውፊታችሁን፤ በአጠቃላይ፡ የቤተ፡ ክርስቲያናችሁን፡ ሕግና፡ ሥርዓት፡ በሚገባ፡ አውቃችሁ፡ ራሳችሁንና፡ ሌሎችንም፡ መጠበቅ፡ የእምነት፡ ግዴታችሁ፡ ሊሆን፡ ይገባል ።

ትውልድ፡ መቁጠሩ፡ ብቻ፡ ዋጋ፡ አይኖረውም ፤ ቁም፡ ነገሩ፡ የተሟላ፡ ዕውቀት፡ ይዞ፡ መገኘት፤ የጠራውን፡ እምነትና፡ አሠራር፡ መውረስ፡ ነው ። ቁም፡ ነገሩ፡ የአንዲት፡ ቤተ፡ ክርስቲያን፤ የአንዲት፡ ጥምቀት፤ የአንዲት፡ ሃይማኖት፤ የአንድ፡ እግዚአብሔር፡ ልጅ፡ ሆኖ፡ መገኘት፡ ነው፤ ለቤተ፡ ክርስቲያንና፡ ለእግዚአብሔር፡ ታማኝ፡ ሆኖ፡ መገኘት፡ ነው፤ ለዚህ፡ ማሠሪያው፡ ደግሞ፡ ፍቅር፡ ነው ።

እናንተ፡ ወጣቶች፡ እርስ፡ በርሳችሁ፡ መከባበርን፤ መደማመጥን፤ መተጋገዝን፡ የመሳሰሉ፡ ቁም፡ ነገሮችን፡ ገንዘባችሁ፡ ማድረግ፡ አለባችሁ ፤ ያሰብነውን፡ መፈጸም፡ የምንችለው፤ ጠላቶቻችንን፡ /አጋንንትን፡/ ማሸነፍ፡ የምንችለው፡ አንድነታችንን፡ በፍቅር፡ ገመድ፡ ስናሥር፡ ብቻ፡ ነው ።

ሕፃናትና፡ ወጣቶች፡ እየተሰባሰቡ፡ በሚማሩበት፡ ጊዜ፡ ሁሉ፡ አባቶች፡ ሊገኙ፡ ይገባል ። አዋቂዎች፡ በሚማሩበት፡ ጊዜም፡ ወጣቶች፡ እንዲገኙ፡ ያስፈልጋል ። ከሁሉም፡ በላይ፡ ደግሞ፡ ካህናት፤ ሰባኪያን፡ ወንጌል፤ የአብነት፡ መምህራንና፡ የአድባራትና፡ የገዳማት፡ አለቆች፡ እንደማንኛውም፡ የገባኤ፡ መድረክ፡ ሊለዩ፡ አይገባም ። ምክንያቱም፡ የኖላዊነት፡ የሥራ፡ ድርሻ፡ በጋራ፡ መወጣት፡ አስፈላጊ፡ መሆኑ፡ በቅዱሳት፡ መጻሕፍት፡ የተነገረ፡ በመሆኑ፡ ነው ።

ቀደም፡ ሲል፡ በነቢያት፡ እንደተነገረው፡ የአባቶችን፡ ልብ፡ ወደ፡ ልጆች፤ የልጆችንም፡ ልብ፡ ወደ፡ አባቶች፡ የመመለስ፡ ጊዜው፡ እነሆ፡ አሁን፡ ነው ። « በአባቶች፡ ፈንታ፡ ልጆች፡ ተወለዱልሽ፡ » የሚለውን፡ የነቢዩን፡ ቃል፡ በቤተ፡ ክርስቲያናችን፡ ተፈጸመ፡ ማለት፡ የምንችለውም፡ ወጣት፡ ልጆቻችን፡ ልባቸውን፡ ለአባቶቻቸው፡ ሰጥተው፤ የቤተ፡ ክርስቲያናቸውን፡ ንጹሕ፡ እምነት፤ ሥርዓትና፡ ትውፊት፡ ጠንቅቀው፡ አውቀው፡ የቤተ፡ ክርስቲያናቸው፡ ተረካቢዎች፡ የመሆን፡ ብቃት፡ አላቸው፡ ብለን፡ ስናረጋግጥ፡ ብቻ፡ ነው ። ወጣት፡ ልጆቻችን፡ ለሚረከቡት፡ ከባድ፡ ኃላፊነትም፡ ብቁ፡ ሁነው፡ በጥበበ፡ እግዚአብሔር፡ ታንፀው፡ ይደጉ ፤ በፈሪሃ፡ እግዚአብሔር፡ የሚኖሩ፡ ይገኙ ። ወጣቶች፡ በቅንነትና፡ በሥነ፡ ምግባር፡ የታነፁ፤ እንዲሆኑ፡ ያስፈልጋልና ።

ስለዚህ፡ እግዚአብሔር፡ ለሀገራችን፤ ለቤተ፡ ክርስቲያናችንና፡ ለሕዝበ፡ ክርስቲያኑ፡ ሰላሙን፤ ለወጣት፡ ልጆቻችንም፤ ጥበቡንና፡ ማስተዋሉን፡ ይስጥልን ፤
እግዚአብሔር፡ ኢትዮጵያን፡ ይባርክ ። አሜን ።

አባ፡ ጳውሎስ፡ ፓትርያርክ፡
ርእሰ፡ ሊቃነ፡ ጳጳሳት፡ ዘኢ...
ወሐፄ፡ ዘመንበረ፡ ተክለ፡ ሃ...

# የሰንበት ት/ቤት አጀማመር በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን



ከ1935 ዓ.ም በፊት በኢትዮጵያ የሰንበት ት/ቤት ጎልቶ የሚታይ አልነበረም፤ የሰንበት ት/ቤት በትክክል ሥራውን የጀመረው በአዲስ አበባ ከተማ ባለው የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ በ1935 ዓ.ም ከተከፈተ በኋላ፣ ሚስተር ኤድዋርድ በሚባሉ ግብጻዊ ምሁር ጥረት ነበር።

በዚሁ ወቅት በእኒሁ አስተማሪ አስተባባሪነት በአዲስ አበባ ከተማ ባሉት ገዳማትና አድባራት ስምሪት ተጀመረ። አንድ ወጥ የሆነ ትምህርት ለመስጠትም መምህራን ከሳምንት በፊት እየሰለጠኑ በግብፅ አገር የታተሙ ካርዶችና ሌሎችንም የስፖርት መጫወቻዎች ገመድ እየተሰጡ ዋቸው በቂ ዝግጅትም እየተደረገ ይላኩ ነበር። በዚህ ረገድ በምስካየ ኅዙናን መድኃኔዓለም የተምሮ ማስተማር ት/ቤት በቀደምትነት የሚጠቀስ ነው።

ለመጀመሪያ ጊዜ የሰንበት ት/ቤት ማኅበርና፣ የወንጌል መልእክተኞቹ ማኅበር በሚል ስያሜ ይንቀሳቀስ ነበር፤ ነገር ግን በዚህ እንቅስቃሴ ከመቀጠል ይልቅ የአንድነት እንቅስቃሴ እንደሚበልጥ ስለታመነበት የወንጌል መልእክተኞችና የሰንበት ት/ቤት ማኅበር በሚል ስያሜ አንድ ሆኖ ሥራውን ቀጠለ።

ማኅበሩን የሚመራው የአመራር ኮሚቴውም በሥሩ የሚንቀሳቀሱ፣

- የሥነ ጽሑፍ ክለብ፣
- የድራማ ክለብ፣
- የመዝሙር ክለብ፣
- የትምህርትና የጥናት ክለብ፣
- የስፖርት ክለብ እና የመሳሰሉ ክለቦች ነበሩት።

ጽ/ቤቱም በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ቅጽረ ግቢ በስተ ደቡብ በኩል፣ ወደ መንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ መግቢያ በዋናው በር ሲገቡ በስተግራ በኩል ያለችው ሕንፃ ነበረች።

በ1953 ዓ.ም በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ መልካም ፈቃድ ከመንበረ ፓትርያርኩ የገንዘብ ድጋፍ እየተሰጠ ማለት ለመምህራኑ ለእሑድ እሑድ እንቅስቃሴ የሚረዳቸውን መጓጓዣ እየተከፈላቸው መምህራን ይላኩ ነበር።

ወደ የሀገረ ስብከቱ ሲኬድም እንዲሁ በቀላሉ ልጆች አይገኙም ነበር የሚገኙት ከ10 እና ከ20 የማይበልጡ እንደ ነበሩ በወቅቱ ወጣት ምሁራን በመሆን አገልግሎት ይሰጡ የነበሩ እነሊቀ ጉባኤ አበራ በቀለ ይመሰክራሉ።

ማኅበሩ በመንበረ ፓትርያርኩ ጠቅላይ ጽ/ቤት ሥር በክፍል ደረጃ በተከፈተ ጊዜም የክፍሉ ዋና ኃላፊ ሆነው ይመሩት የነበሩት በጊዜው አባ ገብረመድህን ገብረ ዮሐንስ በአሁኑ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለሃይማኖት ናቸው።

የሰንበት ት/ቤቶቹ ስፋት እየቀጠለ በሄደ ጊዜም ከሰዋሰው ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ ት/ቤት ተማሪዎች መካከል የማስተማር ችሎታ ያላቸው ደቀመዛሙርት እየተመረጡ፤ «የእሑድ ትምህርት መልዕክተኞች» የሚል ስም ተሰጥቶአቸው በበጎ ፈቃድ ያስተምሩ ነበር።

በመምህራኑ ጥያቄም፣ በወቅቱ የብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ዋና እንደ ራሴ በነበሩት በብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ ፈቃድና ትእዛዝ በቁጥር 118/59 በተጻፈ ማዘዣ፣ የሰንበት መምህራን ጽ/ቤት ተከፈተ። ከ1966 ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የወጣቶች መንፈሳውያን ማኅበራት አጠቃላይ ጉባኤ የሚባል አካል ተቋቁሞ የወጣቶች ጉልማሶች መንፈሳውያን ማኅበራት አጠቃላይ የስብከተ ወንጌል መንፈሳውያን ማኅበር ተብሎ በመሰየም ኅዳር 29 ቀን 1970 ዓ.ም በቁጥር 559170 እና በቁጥር 1428/8513/78 በተጻፉ ደብዳቤዎች እውቅና ወይም ሕጋዊ ሰውነትን አገኘ።

የዚህ ማኅበር መቋቋም ከዓላማዎቹ አንዱና ዋናው በየአብያተ ክርስቲያናቱ የተቋቋሙትንና የሚቋቋሙትን የወጣቶችና ጉልማሶች መንፈሳውያን ስብከተ ወንጌል ማኅበራትን አጠቃልሎ ለመምራት ነበር። ውጤቱ ግን የታወቀ አይደለም።

ከላይ በተገለጸው መልኩ የተቋቋሙት የሰንበት ት/ቤቶች ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደጉ በመምጣታቸው በወቅቱ «የታሪክና ድርሰት ስብከት ክፍል» ይባል በነበረው፣ በአሁኑ የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልእኮ መምሪያ ሥር መሆኑ ቀርቶ የወጣቶች ጉዳይ መምሪያ በሚል ስያሜ ራሱን ችሎ እንዲንቀሳቀስ ተደረገ።

www.ethiopianorthodox.org

የወጣቶች ጉዳይ የሚለው ስያሜ ዕውቅናው በቤተ ክርስቲያኒቱ ሕግ መረጋገጡን በቃለ አዋዲው ምዕራፍ አራት አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 1/መ እና፣ በአንቀጽ 17፣ ላይ ከተደ ነገጉት ሕጎች መረዳት ይቻላል።

ነገር ግን የደርግ መንግሥት ኢ.ኢ.ወ.ማ ብሎ የሰየመውን የወጣት ማኅበር በአገሪቱ ላይ ባቋቋመ ጊዜ (በደርግ ልዩ ትእዛዝ ይመስላል) መምሪያው የወጣቶች ጉዳይ መምሪያ መባሉ ቀርቶ የሰንበት ት/ቤቶች ማስተባበሪያ በሚል ስያሜ እንዲጠራ ተደረገ። ከዚህም ሌላ በባለ ሥልጣኖች አለመግባባት ምክንያት፣ ነሐሴ 10 ቀን 1976 ዓ.ም በቁጥር 6426/8513176 በተጻፈ ቀላጤ መምሪያው ታጥፎ በዋና ክፍል ደረጃ እንዲቀጥል፣ ተደርጎ ከቆየ በኋላ እንደገና በመምሪያ ደረጃ ሥራው እንዲቀጥል ተፈቀደ። ድሮውም ቢሆን፣ መምሪያው ለሥራ የሚንቀሳ ቀስበትና ለመምህራን የሚከፍለው በጀት አልነበረውምና፣ ከየካቲት ወር 1969 ዓ.ም ጀምሮ ግን ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ከግል ደመወዛቸው ላይ ብር 730.00 (ሰባት መቶ ሰላሳ ብር) በየወሩ እየተቆረጠ፣ በወጣቶች መምሪያ በኩል ለሰንበት ት/ቤት መምህራን እንዲመደብ፣ መጋቢት 15 ቀን 1969 ዓ.ም በቁጥር 138/69 በተጻፈ ደብዳቤ ፈቀዱ።

በዚህ መሠረት ለብዙ ዓመታት በበጎ ፈቃድ (በችሩፋት) ነፃ አገልግሎት ይሰጡ የነበሩት ወጣት መምህራን በየወሩ ብር 40.00 እና 20.00 ለትራንስፖርት እየተከፈ ላቸው በአዲስ አበባ ገዳማትና አድባራት እንዲያስተምሩ ማድረግ ተቻለ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማ የሰጡት አባታዊ ድጋፍ የሰንበት ት/ቤቶች አሁን ለሚገኙበት ደረጃ ያደረሰ ጽኑ መሠረት በመሆኑ፣ በሰንበት ት/ቤቶች የታሪክ ዓምድ፣ ምን ጊዜም ሊዘነጋ የማይችል ታላቅ የታሪክ ምዕራፍ ይዞ ይገኛል።

ፈለገ ጥበብ መጽሔታችን በየሦስት ወሩ እየታተመ እንዲሰራጭ የተፈቀደውም በ1970 ዓ.ም ነበር።

መምሪያው በዚህ መልክ ሥራውን እንደ ቀጠለ በግልጽ ይታወቅ እንጂ በሀገረ ስብከት ደረጃ የሰንበት ትምህርት ቤቶች መኖር በግልጽ የታወቀው ግን ከሰበካ ጉባኤ መቋቋምና መጠናከር ጋር ነው። ይልቁንም ከ1969 ዓ.ም ጀምሮ በየሀገረ ስብከቱ የተደረገው ስምሪት ለሰንበት ት/ቤት በስፋት መቋቋም ወሳኝ አስተዋጽኦ ነበረው።

በዚህ መሠረት በየሀገረ ስብከቱ ምን ያህል የሰንበት ት/ቤቶች እንደተ ቋቋሙ ግልጽ የሆነ ስታስቲካዊ መረጃ የተገኘው በ1975 ዓ.ም ነበር፤ በዚህ መረጃ መሠረትም (ኤርትራን ሳይጨ ምር) 915 የሰንበት ት/ቤቶች መቋቋ ማቸውን ያስረዳል፤

ከዚህ በኋላ ግን መረጃዎች ከየሀገረ ስብከቱ ከሞላ ጐደል ይላኩ ጀመር፣ ለምሳሌ በ1987 ዓ.ም የተላከው ስታስቲካዊ መረጃ እንደ ሚያስረዳው 915 የነበሩት የሰንበት ት/ቤቶች ወደ 5092 ከፍ ያሉ በመሆናቸው የ456.5% እድገት አሳይቷል።

በወጣቶች ምዝገባ በኩልም በ1975 ዓ.ም ኤርትራን ሳይጨምር (ወንዶች 27431 ሴቶች 16216 ድምር 43647 መመዝገባቸውን ሲያመለክት፤ በ1987 ዓ.ም ግን ወንዶች 134280 ሴቶች 151013 ድምር 285293 ወጣቶች መመዝ ገባቸውን ያረጋግጣል።

በዚህ ስታስቲካዊ መረጃ መሠረትም በ12 ዓመታት ውስጥ የታየው እድገት በወንዶች በኩል 389.5% በሴቶች በኩል 831.2% በአጠቃላይ 553.6% ነው።

ግንቦት 2 ቀን 1986 ዓ.ም በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትር ያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሰብሳቢነት 17 ብፁዓን ጳጳሳት የተገ ኙበት ቅዱስ ሲኖዶስም፣ ከቤተ ክርስቲያኒቱ ማእከላዊ አስተዳደር ጀምሮ እስከ አጥቢያ ቤተክርስቲያን ያሉትና ለወደፊት የሚቋቋሙት የሰንበት ት/ቤቶች የሚገለገሉበት አምስት ምዕራፎችንና ሰላሳ ሁለት ተራ ቁጥሮችን ያካተተ መመሪያ አውጥቶአል።

መመሪያው፣ የሠራተኞችን የሥራ ድርሻ (ጆብ ዲስክሪፕሽን) ተንትኖ ከማስረዳት ደረጃ ጀምሮ ከመንበረ ፓትርያርክ እስከ አጥቢያ ቤተክርስቲያን የተደራጁና የሚደራጁ የሰንበት ት/ቤቶችን አንድ ወጥ በሆነ መልኩ አሰባስቦና አስተባብሮ በሥነ ሥርዓት መምራትና ማደራጀት የሚያስችል መመሪያ ነው።

ከዚህም በላይ፣ የሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ተጠሪነቱ ለቅዱስ ሲኖዶስ ሆኖ በሊቀ ጳጳስ የበላይ ኃላፊነት እንዲመራ መደረጉን በመመሪያው በምዕራፍ አራት ቁጥር 17 ተደንግጎአል። ይህ ድንጋጌ ለሰንበት ት/ቤቶች መስፋፋትና መጠናከር፣ እንዲሁም መምሪያውን ከላቀ ደረጃ ላይ ለማድረስ ከፍተኛ ግምት የተሰጠው መሆኑን የሚያስርዳ የታሪክ ምዕራፍ ነው።

በየሰንበት ት/ቤቱ የተደራጁ ወጣት ልጆቻችን በአሁኑ ጊዜ የሚከታተሉት መንፈሳዊ ትምህርትን ብቻ አይደለም፤ በርካታ ማኅበራዊ

ናቸው፤ የተቸገሩትን በመርዳት፣ በየበዓላቱ ምእመናንን በማስተባበር ነዳያን የሚረዱበት መርሐ ግብር በመዘርጋት ከምእመናን በሚያገኙት ገንዘብ ነዳያንን በማገዝ ላይ ናቸው። አስተማሪ ያጡ ሕፃናትን በአቅማቸው እየረዱ የሚያስተምሩ የሰንበት ት/ቤቶች በርካታ ናቸው። በተለይ በልማት ሥራ የሰንበት ት/ቤት ወጣቶች ግንባር ቀደም ተሳታፊ ነታቸው በተግባር በማሳየት ላይ ናቸው፤ ለዚህም ብዙ ቁጥር ያላቸው ወጣቶች በልማት መርሐ ግብር እንዲሰለጥኑ ወይም የልማት አስተባ ባሪዎች ለመሆን እንዲችሉ ትምህር ቱን በግብርና ባለሙያዎች እንዲሰ ጣቸው ተደርጎአል፤

የሰንበት ት/ቤቶች መዝሙር በመላ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን አንድ ዓይነት ያሬዳዊ መዝሙር እንዲኖር ለማድ ረግ ከአዲስ አበባ ገዳማትና አድባራት የተውጣጡ ወጣቶች በቤተ ክርስቲ ያኒቱ ሊቃውንት ተጠንቶ በሊቃ ውንት ጉባኤ የተፈቀደ የዓመት መዝሙር ለሁለት ዓመት ያህል ጊዜ ካጠኑት በኋላ ድምፁ በመቀረፅ ላይ ነው። ይሁን እንጂ ድምፁን መቅረፅ ብቻ በቂ ሆኖ ባለመገኘቱ መዝሙሩ በመጽሐፍ ታትሞ እንዲወጣ ስለተፈቀደ ለኅትመት ቀርቧል፤ በቅርብ ጊዜ ታትሞ አገልግሎት ይሰጣል።

ከዚህም ሌላ ለብዙ ጊዜ አሳሳቢ ሆኖ የቆየው የሰንበት ት/ቤቶች ሥርዓተ ትምህርት ጉዳይ ከእስክ ንድርያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ከተሰኘችው የሰንበት ት/ቤቶች ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ ለጊዜው የመጀመሪያዎቹ አምስት መጻሕፍት ወደ አማርኛ ተተርጉመው ብቃታቸውና ጥራታቸው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የሊቃውንት ጉባኤ ከተመረመሩ በኋላ መጻሕፍቱ ታትመው አገልግሎት መስጠታቸውን እንዲቀጥሉ

ስለተፈቀደ አምስቱን መጻሕፍት አሳትመን ለየሰንበት ት/ቤቱ ለማሰራጨት በዝግጅት ላይ ነን።

ይሁን እንጂ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የሰንበት ት/ቤቶች ማ/መምሪያ፣ ሥራውን ጀመረ እንጂ አላገባደደም። ቤተክርስቲያኒቱ ከምትፈልገው ግብ ለመድረስ ገና ብዙ ሥራ ይቀራል። የሰንበት ት/ቤት ያልተቋቋመባቸው አብያተ ክርስቲያናት በጣም ብዙ ናቸው። ለተቋቋሙት የሰንበት ት/ቤቶችም፣ መምህራንን በቋሚነት የመመደቡ ጉዳይ ገና ከሐሳብ ደረጃ ያላለፈ ዐቢይና አሳሳቢ ሥራ ነው።

ቀጣዩ ሥርዓተ ትምህርት አስተርጉሞ፣ ለኅትመት ማብቃትና በየሰንበት ት/ቤቱ አገልግሎት እንዲሰጥ የማድረጉ ጉዳይም ቀላል ጥረት የሚጠይቅ አይሆንም። ለዚህ ሁሉ የመምሪያውንና በጠቅላላ የሰንበት ት/ቤቶችን ዐቅም ለማጠናከር ከአጥቢያ ቤተክርስቲያን ጀምሮ በየደረጃው ባለው የቤተክርስቲያኒቱ መዋቅር፣ ሁሉ ልዩ ትኩረት የሚያሻው የሥራ ዘርፍ መሆኑን ሊታመንበት የሚገባ ጉዳይ ነው።

በውጭ ርዳታ ዳዴ ብለን ለዚህ በመድረሳችን የውጭ ረጂዎቻችንን ውለታ መዘንጋት እንደሌለብን ብናስታውስም፣ ምንም ጊዜ ቢሆን የልመና ገንዘብ ማቆያ እንጂ ራት ለመሆን ስለማይበቃ፣ የልብ የሚያደርስ ዘላቂ ሥራ እንሥራ ከተባለ በራሳችን የምንተማመንበት ቋሚ የገቢ ምንጭ ከራሳችን የሚገኝበትን ብልሃት መፍጠር ለነገ ሊባል የማይገባው እርምጃችን ሊሆን ይገባል።

ከሊቀ ካህናት ኃይለሥላሴ ዓለማየሁ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሰንበት ት/ቤቶች ማ/መምሪያ ኃላፊ

## የፈላስፋው ቃላት

«ትምህርትን ለመማር አትድከም፣ በሕይወትህም ዘመን ሁሉ አትተዋት። የሚበቃኝ ብዙ ትምህርት ተምሬአለሁ ከቶ አትበል፣ የሰዎችን ትምህርት ሁሉ ብትማር እንደገና የምታገኘው ዕውቀት ይበዛልና፣ በአንድ ትምህርት መኖርም ሃኬተኛ ስለሚያደርግ ብዙ ሥራዎችን እንድታገኝበት ትምህርት የተባለውን ሁሉ ተማር።»

• • •

«...በእውነትና በሥራ ብቻ እንጂ በአፍና በምላስ እንፋቀር ዘንድ አይገባንም። በአፋቸው የክርስቶስን ፍቅር እያስትማሩ በልባቸው ፍቅር የሌላቸው ሲሳደቡና ሲጋደሉ እርስ በርሳቸውም ስለሃይማኖታቸው ሲወጋገዙ እንደሚኖሩ...አንሁን»

• • •

«...ልጆችህ ሊያከብሩህና ሊያፈቅሩህ የምትፈልግበት ጊዜ ይመጣልና በሕፃንነትህና በጉብዝናህ ወላጆችን አክብር»

ፈላስፋው ወልደ ሕይወት (የዘርዓ ያዕቆብ ደቀመዝሙር)

www.ethiopianorthodox.org

# ሠሠ ደፍኑ ፀር

ይህ ዓምድ መናፍቃንና አጽራረ ቤተክርስቲያንን የሚያጋልጡ ጽሑፎች የሚቀርቡበት የእመቤታችን፣ የጻድቃንና የሰማዕታት አማላጅነት፣ ተራዳኢነት የሚተነተንበት፣ ይሆናል።

## ክብረ ቅዱሳን



ክርዕሰ ደብር መሐሪ ኃይሉ

የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት የስብከተ ወንጌል ክፍል ኃላፊ

ክብረ ቅዱሳን በምንልበት ጊዜ በውስጡ ከዚህ ቀጥለው ያሉ ጉዳዮችን ለማየት እንገደዳለን።

እነሱም:- ክብረ ቅዱሳን ማለት ምን ማለት ነው?

- ቅዱስ የሚለው (ስም) ቅጽል የሚሰጣቸውስ ምንና ምን ለሙሩ ነው።
- የቅዱሳን ምልጃ እንዴት ነው የሚታየው (በቅዱስ መጽሐፍ እንየር።)
- የቅዱሳን ምልጃ በብሉይ ኪዳንና በሐዲስ ኪዳን
- የቅዱሳን ምልጃ
  - ሀ. በአፀደ ሕይወተ ሥጋ
  - ለ. በአፀደ ነፍስ

ቅዱሳን የሚያማልዱት ፍጡራን ሁነው ሳለ እንዴት የፍጡራን ባሕርይና ጩኸት አውቀው እንዴትስ ሰምተው ሊያማልዱን ይችላሉ? የሚሉትና ሌሎችም በቅዱሳን ክብርና ምልጃ ዙሪያ የሚነገሩ ጉዳዮችን በቅዱስ መጽሐፍ መሠረትነት በመጠኑ ለማየት እንሞክራለን።

ወደ ዋናው ሐተታ ከመግባታችን በፊት ክብርና ቅዱስ የሚለውን ሐረግ እብረን እንይ (እንመልከት)

### መጀመርያ ክብር ምንድነው?

ክብር ቃሉ ጌትነትንና ልዩነተኛነትን ዋጋንና ጥቅምንም አጠቃልሎ መወደድን ያሳያል፤ ዋና ትርጉሙ ለፈጣሪ የሚሰጥ ሲሆን ለፍጡራንም ይሰጣል። «ሰብእሰ እንዘ ኸቡር ውእቱ ኢያእመረ (መዝ.48፥20) ጠቅላላ የእግዚአብሔር ፍጥረት ሁሉ ክብር አለው» (ሉቃስ 2፥9። 1ቆሮ.11፥7። 15፥41። 1ጴጥ.2፥47) ለሰዎች እንደ ማዕረጋቸው ማክበር እንደሚገባ ሮሜ.13፥7። ክብር የሚለው የቃል ሐረግ ይህን ሲመስል:-

### ቅዱስ የሚለውን ደግሞ እንየው

ቅዱስ የሚለው ቃል የዕብራይስጥ ቃል ሲሆን የቃሉ ትርጉም

«የተለየ ንጹሕ ልዩ» ማለት ነው። በግዕዝም ቃሉ ከነ ትርጉሙ ሳይለወጥ ይህንኑ ይዞ ይገኛል።

1ኛ. ሰው ወይም ማንኛውም ነገር ለእግዚአብሔር አገልግሎት ሲለይ ቅዱስ ይባላል። ዘጸ.28፥41። ዘጸ.3፥5። ኢዮ.6፥9። ዘሌ.19፥2። ዘኁ.14፥20–21። 1ጴጥ.1፥15። 1ቆሮ.1፥2፤ 30። ሰው ከመንፈስ ቅዱስ በሚወለድበት ጊዜ የቅድስና ሥራ ይጀምራል። 1ቆሮ.15፥5። 1ተሰ.4፥7። 5፥23፤ 24።

«ክብርና ቅዱስ»ና ትርጉማቸው ከዚህ በላይ እንደ ተገለጸው ሲሆን ሁለቱ ተገናኝተው ሲናበቡ ክብረ ቅዱሳን ይባላል።

በመሠረቱ ክብረ ቅዱሳን ራሱ መድኃኔ ዓለም ክርስቶስ ነው። ለዚሁም ማስረጃ ኢትዮጵያዊው ሊቅ ቅዱስ ያሬድ ከተናገራቸው ቃላት በከፊል እንደዚህ ይቀርባል «ተሰብከ መድኅን ክብረ ቅዱሳን ቤዛ ብዙኃን አክሊሎሙ ለሰማዕት ሰያሚሆሙ ለካህናት መድኃኒቶሙ ለነገሥት ክብሮሙ ለመላእክት ሞገሶሙ ለሐዋርያት።»

ይኸውም የቅዱሳን ክብራቸው፣ የሰማዕታት አክሊላቸው፣ የካህናት ሿሚያቸው፣ የነገሥታት መድኃኒታቸው፣ የመላእክት ክብራቸው፣ የሐዋርያት ሞገሳቸው የሚሆን መድኃኔ ዓለም ክርስቶስ ተሰበከ ተናገረ ተገለጠ ታወጀ...ማለት ነው። (ድጓ የስብከት ክብረ ቅዱሳን ከሚለው ክፍል ይገኛል።)

### ክብረ ቅዱሳን ራሱ መድኃኔ ክርስቶስ ከሆነ እንዴት ለሰው ተሰጠ?

መድኃኔ ዓለም ክርስቶስ ራሱ ክቡር ሲሆን ሰውንም በራሱ ክብር አክብሮ ክቡር አድርጉታል። ራሱንም ቀድሶ ቅዱስ አድርጎታል። በመሠረቱ ከነውር ከኃጢአት በባህርዩ ንጹህ የሆነ ከፈጣሪ በቀር ሌላ የለም።

ነገር ግን «ኩኑ ቅዱሳነ እስመ አነ ቅዱስ አነ» እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ቅዱስ ነኝና እናንተም ቅዱሳን ሁኑ፤ ብሎአልና ሰው በእግዚአብሔር ቅድስና ይቀደሳል። ዘሌ.19፥2። 1ጴጥ.1፥15–17።

በፊት አገልጋዮቹ መላእክትን የቀደሰ ማለት ያከበረና ከፍ ከፍ ያደረገ እርሱ ነው፤ በኋላም ዓለሙን ሁሉ የቀደሰው ደሙን በፈቃዱ በመስቀል ላይ በማፍሰስ ተከታዮቹን ሁሉ ቀደሳቸው፣ አከበራቸው።

ስለዚህ 1ኛ ቅዱሳን ሰዎች (ጾታን ሳይለይ) ሁሉ ለቅዱስ ለእግዚአብሔር ሲሉ ሕይወታቸውን በሞት ስለ አሳለፉ በደማቸው ታጥበው ቅድስናን ገንዘብ ስለአደረጉ የቅድስናና የብፅዕና መዓረግ ተሰጥቷቸው እናገኛቸዋለን።

እንዲሁም ስለሰው ልጅ ሕይወት፣ ስለ ዓለም ሰላም፣ ጽድቅ የሠሩ፣ የተናገሩ ሁሉ ጾታ፣ ዕድሜ ሳይለይ ቅዱሳን ናቸው። በዚህም መሠረት ሐዋርያዊትና ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን የቅድስናና የብፅዕና መዓረግ ሰጥታ ቅዱሳን ብላ ሰይማቸው ትገኛለች።

በዚህም መሠረት ሐዋርያትና የእነርሱ ተከታዮች ሁሉ ወንድ፣ ሴት፣ ሕፃን፣ ሽማግሌ ሳይባል በጠቅላላ ቅዱሳን እንላቸዋለን።

2ኛ. ቅዱስ የሚያሰኛቸው አንቀጽ ምንድነው? ቅዱሳንስ የሚባሉት መለያቸው ምንድነው? ምንስ የሠሩ ናቸው? የሚለውን ጥያቄ ሁል ጊዜ እየተመላለሰ የሚቀርብ ጥያቄ ነው። ተገልጦም ሊታወቅ ያስፈልጋል። ይሁን እንጂ ቅዱሳን የሚባሉት:-

ሀ. ዓለምን በመላዋ ዞረው ያስተማሩና ስለ ክርስቶስ የመሰከሩ እንደ ሐዋርያት ያሉት ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ የቀደሳቸውና ቅዱሳንም ያላቸው ናቸው።

ለ. ስለ ክርስቶስ በዓላውያን ነገሥታት ፊት ቀርበው ሳይፈሩ ሳያፍሩ የመሰከሩ ሰማዕታት ናቸው። በዚህም ምክንያት ሕይወታቸውን ያጡ፤ ይኸንም የመሰለውን ምስክርነት ራሱ መድኃኔ ዓለም ክርስቶስ ሲያስተምር «አንሰ እንበይነዝ መጻዕኩ ወእንበይነዝ ተወለድኩ ከመ እኩን ስማዕተ በጽድቅ» ብሎ በተናገረው መሪ ቃል ነው።

ሐ. አብዛኛቸው ዕድሜ ልካቸው በምናኔ፣ በብቸኝነት፣ በጸሎት፣ በምልጃና በትምህርት ያሳለፉ ከከፉ ነገር የራቁ፣ ጣዕመ ዓለምን የናቁ ጻድቃን ሁሉ ቅዱሳን ይባላሉ። የቅድስናም መዓረግ ተሰጥቷቸው እናገኛቸዋለን። ቅዱሳን አንድ ጊዜ በእግዚአብሔር ጸጋ ተመርጠውና ከብረው ቅዱሳን ከሆኑ በኋላ አይሻሩም ጸጋውም አይወሰድባቸውም።

እነዚህ ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ሁሉ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን በዕድሜ፣ በወገን፣ በጾታ ሳትለይ ማለት ትንሽ ትልቅ፣ ሴት ወንድ፣ ኢትዮጵያዊ የውጭ ዜጋ ሳትል ለሁሉም የቅድስና የብፅዕና መዓረግ እየሰጠች የሕይወት ታሪካቸው እየጻፈች እንደ ስንክሣር (ገድለ ቅዱሳን) በመሰለው መጽሐፍ የሕይወት ታሪካቸው በክቡር መዝገብ እየመዘገበች ከትውልድ ወደ ትውልድ እያስተላለፈች ስለኖረች ቅዱሳን ሁሉ በዚህ ስም ሲጠሩ በዚህም መሠረት ሲከብሩና ሲከበሩ ኑረዋል አሁንም ይገኛሉ።

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅም ለዚሁ ታላቅ ምሥጢር እንዲህ ብሏል «ለኵሎሙ ቅዱሳኒሁ በሠናያቲሁ ወሀበሙ ከመይኩኑ ቅዱሳነ እንተ ይዕቲ ቅድሳቱ እንተ ኢትትነሠት ወኢትማስን» ለቅዱሳኑም ሁሉ በቸርነቱ ቅዱሳን ይሆኑ ዘንድ ሰጣቸው ይህችውም የማትፈርስና የማትጠፋ ቅድስት ናት (ቅዳሴ ዘዮሐንስ አፈወርቅ ቁጥር 36) ሲል አስተምሯል።

3ኛ. ክብረ ቅድስት ድንግል ማርያም ቅዱስ የሚለው ቅጽል ለሌሎች ቅዱሳን ሲሰጥ ለድንግል ግን ቅድስተ ቅዱሳን የሚል ቅጽል ነው የተሰጣት፤ ለምን ቢባል ፈጣሪ ፍጥረታት ቅዳሴ ቅዱሳን የሆነው ቅዱስ እግዚአብሔር ስለመረጣትና ከሁሉ በላይ ስለአከበራት የምሕረት መዝገቡ ስለሆነችና የእግዚአብሔር ወልድ በሥጋ እናት ለመሆን ስለበቃች ንጽሕት ሆናም ስለተገኘች ነው። ከላይ እንደ አየነውም ልዩ፤ ንጹህ፤ ቅዱስ በሚለው ላይ ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም የአዳም ዘር ብትሆንም ከዓለም (ከእንስተ ዓለም) ልዩ የሚያደርጋት ወልድን ከድንግልና ጋር አስተካክላ አስተባብራ በመገኘትዋ ነው፤ እንስተ ዓለም ከወለዱ፤ ድንግል አይባሉም፤ በድንግልና እያሉም አይወልዱም ንጽሕተ ንጹሐን፤ ቅድስተ ቅዱሳን ድንግል ማርያም ግን የድንግልና ሕይወትና የእናትነትን ባህርይ አስተባብራ በመገኘት ካለዘርዓ ብእሲ በድንግልና ወልዳ በድንግልና ጸንታ በመኖር ድንግል ወእም መባልዋ ከተፈጥሮ ሕግ በላይ የሆነ አስደናቂና አምላካዊ ምሥጢር በወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም ስለተፈጸመ ነው።

መልአኩም ወደእርሷ ተልኮ «...ደስ ይበልሽ ጸጋ የተሞላሽ ሆይ እግዚአብሔር ከአንቺ ጋር ነውና ያላት» (ሉቃ.1፥28) ድንግል ማርያም ፍጹም አምላክ የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን በድንግልና በመውለድዋ ልዩ ክብርና ቅድስና ስለተሰጣት ነው።

ክብርዋም ከቅዱሳን ሁሉ በላይ ነው። የቅድስት ድንግል ማርያም ቅድስና በውስጥ በአፍአ፤ በነፍስ በሥጋ ነው። ምክንያቱም እግዚአብሔር አብ ለልጁ ማደርያ አድርጎ (ማህደረ መለኮት) ስለመረጣት ልዩ ያደርጋታል።

ቅድስት ድንግል ማርያም አምላክን ለመውለድ ያበቃት ንጽሕናዋ ቅድስናዋ ነው። «ወሶበ ርእየ ንጽሕናኪ ለሊሁ እግዚአብሔር አብ ፈነወ ኀቤኪ መልአኮ ብርሃናዌ ዘስሙ ገብርኤል» እንዳለው አባሕርያቆስ።

ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም ክብር ኢትዮጵያዊው ሊቅ ቅዱስ ያሬድ አንቀጸ ብርሃን በተባለው ድርሰቱ «ቅድስት ወብፅዕት ስብሕት ወቡርክት ክብርት ወልዕልት አንቀጸ ብርሃን መዓረገ ሕይወት ወማኅደረ መለኮት ቅድስተ ቅዱሳን...» በማለት የሚገባትን ክብር በመስጠት ነው አድናቆቱን የገለጸው።

ቅዱስ አባ ሕርያቆስም «ወረከብኩ በውስቴታ ዘይብል ዘንተ ቅዳሴ ዘይቄድስ ካህን እኮ ማርያምሃ ዘድቁድስ አላ ውእቱ ይትቄደስ ወኵሉሙ እለ ሰምዕዎ ይትቄደሱ እስመ እግዚእ ትነስ ማርያም ቅድስት ይእቲ ወትረ በሰማይ ወበምድር» በማለት ክብረ ቅድስናዋን ገልጾ ተናግሯል።

### የቅዱሳን ምልጃ

#### በመሠረቱ ምልጃ ምንድነው?

ምልጃ ማለት በንባቡ ማስታረቅ ይመስላል። ነገር ግን ማስታረቅ ማለት በሁለት ፀበኞች መካከል ገብቶ አንተም ተው አንተም ተው ብሎ ማስማማት ሲሆን አማላጅነት ግን ከዚህ ለየት ይላል። ምክንያቱም ምልጃ አንዱ ሌላውን ሰው ያስቀየመ በደለኛ ጥፋቱን በመገንዘቡ ከአስቀየመው ሰው በኩል የነበረውና ሊኖረው የሚችለው ጥቅም ስለሚቀርበት እንዲሁም ከአስቀየመው ሰው ጋር በሰላም ካልኖረ ችግር ሊደርስበት ስለሚችል አስታርቁን ብሎ አማላጅ ይልካል። የተወሰኑ ሰዎች ግን አማላጅ በመላክ ፈንታ ራሱ ሂዶ ይቅርታ ለምን አይጠይቅም የሚሉ አሉ። ነገር ግን እንኳን በፈጣሪ ፍጥረታት በእግዚአብሔርና በበደሉ ሰዎች መካከል ይቅርና በሰው እና በሰው መካከል በአለው መፈራራት እንኳ ያስቀየመ ሰው ራሱ ቀርቦ ተቀያሚውን ሰው ይቅርታ ለምን አይጠይቅም ቢባል ያስቀየመውን ሰው ከማክበሩ የተነሣ በቀጥታ መሄዱን እንደ ድፍረት በመቁጠሩ፤ ወይም ያን ሰው በጣም በማስቀየሙ፤ እንዴት አድርጌ ዓይኑን ለማየት እችላለሁ ብሎ በመፍራት ወይም ደግሞ ያ አማላጅ የሚላከበት ሰው በደረጃው ከፍ ያለ ከመሆኑ የተነሣ በቀላሉ ሊያገኘው የማይችል በመሆኑ ነው።

በዚህም መሠረት የእግዚአብሔር ወዳጆች ቅዱሳን የእግዚአብሔርን መቅሰፍት ለማስወገድ በእግዚአብሔርና በሰዎች መካከል በመሆን ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡት ልመና፤ ሰው (አማኝ) ከፍተኛ ኃጢአት በመሥራቱ በቀጥታ ወደ እግዚአብሔር ሄዶ ይቅርታ መለመን እግዚአብሔርን እንደ

www.ethiopianorthodox.org

መድፈር ስለሚቆጥረው ነው። ይህም ድርጊት እግዚአብሔርን በጣም የማክበር ትሕትና እንጂ የአምላክን ክብር ለፍጡር አሳልፎ መስጠት አይደለም።

## የዘመኑ የሃይማኖት ተከራካሪዎች ስለአማላጅነት ምን ይላሉ?

በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ሌላ ሦስተኛ ሰው ሊገባ አይችልም እግዚአብሔርም እንደ ሰው አማላጅነት አይቀበልም ወይም ፍርዱን በአማላጅነት በምንም ዓይነት አይለውጥም። ስለዚህ በአማላጅነት ማመን ስሕተት ነው ይላሉ።

ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ግን ስለ ቅዱሳን አማላጅነት ቅዱሳት መጻሕፍትን መሠረት በማድረግ የሚከተለውን አቋም ወይም መሠረተ እምነት አላት። ለዚህም የቤተ ክርስቲያናችን ቀኖናዊያን መጻሕፍት ይቆዩና መሠረቱ ቅዱስ መጽሐፍ ስለሆነ ቅዱስ መጽሐፍ ስለ ቅዱሳን ምልጃ ምን ይላል? ነው የምትለው ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን።

ቅዱስ መጽሐፍማ የእግዚአብሔርን ሕግ የሚያከብሩና በእውነተኛውም እምነት የጸኑ ሰዎች የማማለድ መብት (ሥልጣን) እንደ ተሰጣቸው ያረጋግጣል። ይኸውም፤

1ኛ. የቅዱሳን ምልጃ በሕይወተ ሥጋ

2ኛ. የቅዱሳን ምልጃ በአፀደ ነፍስ የሚል ሲሆን በመጀመሪያ የቅዱሳን ምልጃ በሕይወተ ሥጋ እንመለከታለን።

«ኩናኒ በጽድቅ ፈታሒ በርትዕ» እግዚአብሔር የቅዱሳኑን ጸሎት የሚቀበል መሆኑን በመግለጥ ሰዎችን ወደ አማላጆች እንዴት አድርጉ እንዲላክ በሚከተሉት ማስረጃዎች እንመለከታለን።

«አሁን ግን ሴቲቱን ለባልዋ መልስህ ስጥ እርሱ ነቢይ ስለሆነ እንዳትሞት ይጸልይልሃል እርስዋን መልሰህ ባትሰጥ ግን እንደትሞት እወቅ አንተ ብቻ ሳትሆን ሕዝብህም በሙሉ ታልቃላችሁ። (ዘፍ.20፥7)

በመጽሐፈ «ኢዮብም የኢዮብ ወዳጆች አሁን ሰባት ወይፈኖችና ሰባት አውራ በጉችን ይዛችሁ ወደኢዮብ ሂዱ እዚያም ስለራሳችሁ ኃጢአት የሚቃጠል መሥዋዕት አቅርቡ፤ ባርያዬ ኢዮብ ይጸልይላችኋል። እኔም የእርሱን ጸሎት ስለምቀበል በበደላችሁ መጠን አልቀጣችሁም» (ኢዮብ 42፥8)

አማላጃችን አንድ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው። እንጂ የፍጡር አማላጅነት አስፈላጊ ጠቃሚም አይደለም የሚሉት ወገኖች ይህን የእግዚአብሔርን ምስክርነት ምን ትርጉም ይሰጡት ይሆን? እኔ የኢዮብን ጸሎትና ምልጃ ስለምቀበል ሂዱ እርሱ ይጸልይላችኋልና ይቅርታ አደርግላችኋለሁ አለ እንጂ ሌላ ሰው አያስፈልግምና ራሳችሁ ጸልዩ አላለም። እንዲሁም አቤሜሌክን አብርሃም ነቢይ ስለሆነ እንዳትሞት ይጸልይልሃል ነው ያለው፤ እኛም እኮ ቅዱሳንን ወደ እግዚአብሔር እንዲማልዱልን እንለምናቸዋለን እንጂ የእግዚአብሔርን ክብር ሰጥተን እናመልካቸውም። በእርግጥ ቅዱሳን ክቡራን ስለሆኑ እናከብራቸዋለን፤ አክብሮት ደግሞ አምልኮት አይደለም እኔ ወደ እግዚአብሔር ፊት ለመቅረብ ብቃት ስለሌለኝ የቅዱሳን አማላጅነት ያስፈልገኛል በማለት በትሕትና መቅረብ እግዚአብሔርን ማክበር እንጂ የእግዚአብሔርን ክብርና አምልኮት ለፍጡራን አሳልፎ መስጠት አይደለም።

## ቅዱሳን ፍጡራን ሲሆኑ እንዴት የኛን ጩኸትና ፍላጐት አውቀው ሊረዱን ይችላሉ?

የቅዱሳን ክብርና ዕውቀት፤ ዕውቀት ሰጭ ከሆነው ከእግዚአብሔር በተሰጣቸው ጸጋ ሁሉን ያውቃሉ። ለምሳሌ ኤልሳዕ ነቢይ በዚህ ዓለም በነበረ ጊዜ ደቀ መዝሙሩ ግያዝ በምሥጢር (በስውር) ከሶሪያዊው ንዕማን ስጦታ መቀበሉን ማንም ሳይነግረው እንዴት እንዳወቀ በሁለተኛው መጽሐፈ ነገስት (5፥25–27) መመልከት ይቻላል።

ሌላም ከሶርያ ንጉሥ ባለሟሎች አንዱ ለንጉሡ ስለ ኤልሳዕ እንዲህ ሲል ነገር ሠራ «ጌታ ሆይ እንዲህ አይደለም» ነገር ግን በእልፍኝህ ውስጥ ሆነህ የምትናገረውን በእሥራኤል ዘንድ ያለ ነቢይ ኤልሳዕ ለእሥራኤል ንጉሥ ይነገረዋል» በማለት ኤልሳዕ በቦታም አንድ አካባቢ ሳይሆን በጸጋ መንፈስ ቅዱስ ያውቅ እንደ ነበረ ተጽፎአል። (2ኛነገ.6፥12) በረሀብ ጊዜም የእስራኤል ንጉሥ ሊያስገድለው መልእክተኛ መላኩን ኤልሳዕ አወቀ (2ኛነገ.6፥12)

በዚሁም ዓይነት ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ የሐናንያንና የሰጲራን ምሥጢራዊ ተንኮል የነገረው ሳይኖር አውቆ በሞት ቀጣቸው (የሐዋ.5፥3–9)

ቅዱሳን ከዚህ ዓለም ከተለዩ በኋላ ፈጣሪ ይመስል የዚህን ዓለም ሁኔታና የኛን ፍላጐት እንዴት ሊያውቁ ይችላሉ? የዚህ ዓይነት ጥያቄ ባልታደሉ ሰዎች ሲቀርብ ይሰማል። በመሠረቱ የቅዱሳን ከሥጋ መለየት በበለጠ የሚያውቁ እንጂ የማያውቁ አያደርጋቸውም። በነፍሳቸው ሕያዋን እንጂ ሟቾች አይደሉምና ነው። ለዚህም ነው ጌታ ከሰዱቃውያን ጋር ስለሙታን ይነጋገር በነበረበት ጊዜ እግዚአብሔር የአብርሃም የይስሐቅ አምላክ ነው ሲባል እነዚህ የቀድሞ አባቶች በነፍስ ሕያዋን ስለሆኑ ነው እንጂ እርሱ የሙታን አምላክ ስለሆነ አይደለም፤ ያለው ማስረጃችን ነው (ማቴ.22፥31–32) በተጨማሪም መላእክትም ሆኑ ቅዱሳን በዚህ ዓለም ስለአለው ሁናቴ የሚያውቁ መሆናቸውን ከቅዱሳት መጻሕፍት ማረጋገጥ ይችላል።

«ጸጋውና ምሕረቱ ከቅዱሳኑ ጋር እንደሆነና የተመረጡትንም እንደሚያከብራቸው ይህን ሰዎቹ አይተው አልተረዱትም በአእምሮአቸውም አላኖሩትም። ስለዚህ የሞተው ጻድቁ ሰው ባልሞቱት ኃጢአተኞች ላይ ይፈርዳል። (ጥበብ.4፥15–16)

«እግዚአብሔርም እንዲህ አለኝ ሙሴና ሳሙኤል በፊቴ ቢቆሙ እንኳ ልቤ ወደዚህ ሕዝብ አይመለስምና ከፊቴ አስወግዳቸው ይሂዱ።» (ኤርም.15፥1–4)።

ይህ አባባል የሚያመለክተው ከኤርምያስ ዘመን በፊት ከሞቱት ብዙ ዓመታት ያሳለፉ ሙሴና ሳሙኤል ስለ እሥራኤል ዘሥጋ እግዚአብሔርን ይማጸኑና ይማልዱ የነበሩ መሆናቸውን ነው የሚያሳየው።

በመጽሐፈ ዜና መዋዕል ላይም የይሁዳ ንጉሥ ኢዮራም ብዙ ኃጢአት በመሥራቱ ከዓመታት በፊት በእሳት ሰረገላ ወደ ሰማይ ተወስዶ የነበረው ነቢዩ ኤልያስ የተግሳጽና የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ ላከለት ይላል። (2ኛዜና መዋዕ.21፥12–16)።

በትንቢተ ዘካርያስም ላይ የእግዚአብሔር መልአክ ስለኢየሩሳሌም ከተማ ይቅርታ ለምኖ እግዚአብሔር ልመናውን የተቀበለው መሆኑ ተገልጾአል። (ዘካ.1፥12–16)።

«መላእክቶቻቸው ዘወትር በሰማይ ያለውን የአባቴን ፊት ስለሚያዩ ከእነዚህ ከታናናሾቹ አንዱን እንዳትንቁ ተጠንቀቁ» (ማቴ.18፥10)» «ንስሐ በሚገባ በአንድ ኃጢአተኛ ምክንያት በእግዚአብሔር መላእክት ፊት ደስታ ይሆናል።» (ሉቃ.15፥10)።

የሚያስደንቀው ደግሞ በሉቃስ ወንጌል ላይ «አብርሃም» ባለጸጋው ነዌ ሲነጋገሩ አብርሃም በሰጠው መልስ ባለጸጋው በዚህ ዓለም ሳለ በተድላና በደስታ ሲኖር አልአዛር ግን በችግር እንደኖረ የነገረው ሳይኖር ሁኔታውን በዝርዝር ገልጦለታል። ታዲያ አብርሃም ስለእነ አልአዛር የዚህ ዓለም ኑሮ እንዴት ሊያውቅ ቻለ?

እንዲሁም ባለጸጋው በዓለም ስለአሉት ወንድሞቹ አስቦ አብርሃምን በለመነው ጊዜ ሙሴና ነቢያት አሉላቸው ብሎታል ሙሴና ነቢያት የተነሱት አብርሃም ከሞተ ከብዙ ዘመን በኋላ ሲሆን መጻሕፍት በዓለም ላይ መኖራቸውን አብርሃም እንዴት ሊያውቅ ቻለ?

ስለዚህ ዕውቀት ሲያብራራ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ብሎአል «አሁን በመስታወት እንደምናየው ዓይነት በድንግዝግዝ እናያለን በዚያን ጊዜ ግን እግዚአብሔርን ፊት ለፊት እናያለን።» (1ቆሮ.13፥12።)

እስከዚህ ድረስ የቅዱሳን ዕውቀት በሕይወተ ሥጋና በአፀደ ነፍስ የፍጡራንን ምንነት ማንም ሳይነግራቸው እንዴት ማወቅ እንደሚችሉ ከሞላ ጐደል ለማየት ሞክረናል።

ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ የቅዱሳን ምልጃ በብሉይ ኪዳንና በሐዲስ ኪዳን በአጭር በአጭሩ ለማየት እንሞክራለን። በመጀመርያ በብሉይ ኪዳን:- ቀደም ሲል የአብርሃምና የኢዮብ ምልጃ ምን እንደሚመስል አይተናል። አሁን ደግሞ ከሙሴ ጀምሮ እናያለን።

1ኛ. የግብፅ ንጉሥ ፈርዖን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ባለመስማቱ እግዚአብሔር ግብፅን በዕንቁራሪት (ጓጉንቸር) አስወረራት፤ መላዋ የግብፅ አገር በእንቁራሪት ተሸፈነች፤ ፈርኦንም ይህን አስደንጋጭ መቅሰፍት አይቶ ሙሴና አሮንን ጠርቶ (ጓጉንቸሮቹ) ከእኔና ከሕዝቤም እንዲርቁ ወደ እግዚአብሔር ጸልዩልኝ አላቸው። ሙሴም ወደ እግዚአብሔር ጸለየ (አማለደ) እግዚአብሔርም በሙሴ ምልጃ ጓጉንቸሮቹን በሙሉ ገደለ። (ዘጸ.8፥8–15።)

2ኛ. ተናካሽ የዝንብ መንጋ (ዘጸ.8፥25–31።)

3ኛ. እስራኤላውያን ጣኦትን በማምለክ ከባድ ኃጢአት በፈጸሙ ጊዜ እግዚአብሔር ሙሴን ጠርቶ ይህን ሕዝብ አጠፋለሁ (እደመስሳለሁ) አንተም በታላቅ ሕዝብ ላይ እሾምሃለሁ ባለው ጊዜ ሙሴ ወደ ፈጣሪው ወደ እግዚአብሔር አጥብቆ ጸለየ (አማለደ) በዚህ ጊዜ መሐሪ እግዚአብሔር በሙሴ ምልጃ ሊያደርገው ከአሰበው መቅሰፍት በራሱ መሐሪነት ተመልሶ መቅሰፍቱን አስቀረ ሕዝቡንም በሙሴ ጸሎት ምልጃ ይቅር አለ። (ዘጸ.32፥11–14።)

4ኛ. ሙሴ ኢትዮጵያዊትዋን ሴት ልጅ በማግባቱ ወንድሞቹ አሮንና ማርያም ሙሴን በመቃወም አሙት በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር የነገሩ ቆስቋሽና ጀማሪ የነበረችውን ማርያምን በለምጽ በሽታ መታት (በረዶ መሰለች)። ነገር ግን ሙሴ ሰባት ቀን ወደ እግዚአብሔር ጸለየላት (ማለደላት) እግዚአብሔርም በሙሴ ጸሎት (ምልጃ) ፈወሳት። (ዘኁል.12፥1–7።)

## የነቢየ እግዚአብሔር አማላጅነት

ስሙ በውል ያልተጠቀሰ ብእሴ እግዚአብሔር በሚል ስያሜ ብቻ የተጠቀሰው በመሰውያ ላይ ዕጣን እያጠነ በነበረው በኢዮርብዓም ላይና በመሰውያው ላይ ትንቢት በመናገሩ ንጉሡ ኢዮርብዓም ተው ያዙት ብሎ እጁን ዘረጋ በዚህ ጊዜ በትንቢቱ መሠረት በደቂቃ ውስጥ የተዘረጋች የንጉሥ እጅ እንደብረት ደርቃ እንደተዘረጋች ቀረች ሊያጥፋት ቢሞክርም አልቻለም።

ከአቅሙ በላይ ሲሆንበት አብእሴ እግዚአብሔር ጸሊሊተ ኀበ እግዚአብሔር በማለት ንጉሡ ወደ እግዚአብሔር ሰው አማልደኝ ብሎ በመለመኑ የእግዚአብሔር ሰውም ወደ መሐሪ እግዚአብሔር በመለመኑ የደረቀችው የንጉሡ እጅ ወደእርሱ ተመለሰች፤ ማለት (ታጠፈች) እንደ ነበረችውም ሆናለች ይላል። (1ኛነገ.13፥1–7)

## የነቢዩ የኤልያስ ምልጃ

ነቢየ እግዚአብሔር ኤልያስ በምልጃው (በጸሎቱ) ብዙ አስደናቂ ተአምራቶች ፈጽሞአል። ከእነርሱም መካከል:-

1ኛ. ሕገ እግዚአብሔርን የተው ወገኖችን ለመቅጣትና ለማሳፈር የሰማይ ዝናብ እንዳይዘንብ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ የሰማይ ዝናብም በኤልያስ ቃል ሦስት ዓመት ከስድስት ወር ሳይዘንብ ቀጥ አለ። ከእነዚህ ዓመታት በኋላ ግን ነቢዩ ኤልያስ ዝናብ እንዲዘንብ ወደ ፈጣሪው (ምልጃ) ጸሎት አቀረበ። ዝናብም በሚገባ ዘነበ። (1ኛነገ.17፥1–7) እንደገና (1ኛነገ. 18፥30–46) በጸሎቱ መሥዋዕቱን ከሰማይ እሳት ወርዶ በላለት።

2ኛ. ለሞተው ሕፃን ልጅ ስለ እናቱ ሲል ኤልያስ ወደ እግዚአብሔር ጸልዮ (ምልጃ) አቅርቦ የልጁም ነፍስ ተመልሳ ልጁም ከሞት ተነሣ። (1ኛነገ.17፥17–24።)

## የነቢዩ ኤልሳዕ አማላጅነት

ገቢረ ተአምር ኤልሳዕም በጸሎቱ (በምልጃው) ብዙ ተአምራቶች አድርጐአል። ከተአምራቶቹም መካከል አንደኛው የሞተውን ልጅ ጸልዮ ማስነሳቱ ነው። (2ኛነገ.4፥18–37) ራሱ ታሞ የሞተው ልጅ ነው ያስነሳው።

## የዳዊት አማላጅነት

«ምንተ ገብሩ እሉ አባግዐ እንዘ ኖላዊሆሙ አነ ዘአበስኩ» ጠማማም ሥራ እኔ አድርጌአለሁ። እነዚህ በጐች ግን ምን አደረጉ እጅህ በእኔና በአባቴ ቤት ላይ እንድትሆን»በማለት ከአንጀቱ በአቀረበው ጸሎት (ምልጃ) መቅሰፍቱ በፈጣሪ ቸርነት ተገታ። (2ሳሙ.24፥15–25)

## የኤርምያስ ምልጃ

በአሥር ቀን ጸሎት (ምልጃ) በእስራኤላውያን ታስቦ የነበረውን መቅሰፍት እንደተገታ ተገልጾአል (ኤርምያስ 42፥1–17)። እስካሁን ድረስ ከሞላ ጐደል ያየነው የቅዱሳን ምልጃ በዘመን ብሉይ ነው።

ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ የቅዱሳን ጻድቃን ምልጃ በዘመን ሐዲስ፤ እናያለን

ይህ የአማላጅነት አገልግሎት ሳይቋረጥ በዘመን ሐዲስም ማለት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ በነበረበት ዘመንና በዘመን ሐዋርያትም ይፈጸም እንደ ነበረ ከዚህ ቀጥለን እንመለከታለን። በወንጌል እንደ ተጻፈው «ልጄ ታሞ ለሞት ተቃርቦአልና ፈውስልኝ» በማለት ስለታመሙ ሰዎች

www.ethiopianorthodox.org

ወጥተው በአቀረቡት ምልጃ እንኳን ሲታመሙ ሲሞቱ ሳይቀር ከሞት እያስነሳ በጥያቄአቸው መሠረት ይፈቅድላቸው እንደነበር ቅዱስ መጽሐፍ ይነግረናል። (ማቴ.9፥18–20)

በዚህዓይነትጌታችንንእየለመኑልጆቻቸውን ያዳኑ ብዙ ናቸው (ማቴ.15፥21፤ ማቴ.17፥14፤ ማር.5፥22–44፤ ሉቃ.7፥1–10።)

ስለዚህ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አንዳንድ ጊዜ በሽተኞች በቀጥታ ሲለምኑት ይፈውሳቸው እንደ ነበረ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ከዚህ በላይ እንዳየነው ስለበሽተኞቹ ሌሎች ሰዎች በማለዱላቸው ጊዜ ይፈውሳቸው ነበር። በዚህ መሠረት አማላጅነት ማለት አንዱ ስለሌላው መጸለይና መለመን፤ ማማለድ ማለት ነው።

## አማላጅነት በዘመነ ሐዋርያት

ሐዋርያት በተሰጣቸው የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ መሠረት በሐዲስ አማንያንና በበሽተኞች ላይ እጃቸውን እያኖሩ መንፈስ ቅዱስን ሲያስጡና ሕመምተኞች ሲፈውሱ ያየ ሲሞን ይህን ታላቅ የመንፈስ ቅዱስ ሥልጣን እንዲሰጠው ገንዘብ ይዞ ወደሐዋርያት ቀረበና እንዲህ አላቸው እጄን በምጭንበት ሁሉ መንፈስ ቅዱስን ይቀበል ዘንድ ለእኔ ደግሞ ይህን ሥልጣን ስጡኝ አለ። ቅዱስ ጴጥሮስ ይህንን ሰምቶ ሲሞንን አጥብቆ ገሰጸው ንስሐም እንዲገባ መከረው። ሲሞን የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ (ጸጋ) በገንዘብ መግዛት (መለወጥ) ታላቅ ስሕተት መሆኑን ከተገነዘበ በኋላ ቅዱስ ጴጥሮስን ካላችሁት ማለትም ከተናገራችሁት አንዳች እንዳይደርስብኝ እናንተው ወደ ጌታ ለምኑልኝ አማልዱኝ! አላቸው። (የሐዋ.8፥14–25።)

ከዚህ ላይ ከሲሞን አባባል የምንረዳው ዓቢይ ቁም ነገር አለ ይኸውም አንዳች ክፉ ነገር እንዳይደርስብኝ እናንተ ወደ እግዚአብሔር አማልዱልኝ (ለምኑልኝ) ማለቱ በዚያን ጊዜ ሐዋርያት ስለበደሉ ሰዎች ወደ እግዚአብሔር ይጸልዩና ምልጃንም ያቀርቡ እንደ ነበረ ይረጋገጣል።

## የቅዱሳን ታላቅ ዕውቀትና ምልጃ በአጸደ ነፍስ

ቅዱሳን በአካለ ሥጋ ሆነው ማንም ሳይነግራቸው እጅግ ምሥጢራዊ የሆኑ ነገሮችን ካወቁ የዚህን ዓለም ውጣ ውረድና ፈተና አልፈው በአካለ ነፍስ ሲሆኑማ ምን ያህል የጠለቀ እውቀት ይኖራቸው? ቅዱስ ጳውሎስ «ዛሬስ በመስታወት በድንግዝግዝ እንደምናይ ነን በዚያን ጊዜ ግን ፊት ለፊት እናያለን ዛሬስ ከዕውቀት ከፍዬ አውቃለሁ በዚያን ጊዜ ግን እኔ ደግሞ እንደታወቅሁ አውቃለሁን» በማለት የቅዱሳን ዕውቀት በአጸደ ነፍስ ታላቅ እንደሆነ ተናግሯል። 1ቆሮ.13፥12፤ 1ሳሙ.28፥8–21፤ ሉቃ.9፥30፥32።

ቅዱሳን በአካለ ነፍስ ሆነው በምድር የሚሠራውን ነገር ማወቅ እስከ ቻሉ ድረስ የኛን ልመና ሰምተው መግለጽ አይሳናቸውም።

በአካለ ነፍስ ያሉ ቅዱሳን «ቅዱስና እውነተኛ ጌታ ሆይ እስከ መቼ ድረስ አትፈርድምን. ደማችንንስ በምድር በሚኖሩት ላይ እስከ መቼ አትቀበልምን?» በማለት በአካለ ነፍስ እንደሚከሱ ራዕይ 6፥9–11 በአጸደ ነፍስ ስለሚያውቁ ለቀረቡት ጥያቄዎች በቂ መልስ ነው። ቅዱሳን በአካለ ነፍስ ተበቀልልን ብለው ከለመኑ ለበጎ ነገር አማልዱን ስንላቸውማ ምን ያህል አብዝተው ይለምኑልን?

እንኳን ቅዱሳን (ጻድቃን) ይቅርና በበደልና በኃጢአት ይኖር የነበረው ባለጸጋ (ነዌ) በአካለ ነፍስ ሆኖ የወንድሞቹን በንስሐ አለመመለስ አውቆ አልአዛርን ስደድላቸውና ያስትምራቸው ሲል አብርሃምን ለምኖላቸዋል። ሉቃ.16፥20–31።

ጌታ ሐዋርያትን «አንትሙ ውእቱ ብርሃኑ ለዓለም» ያላቸው ብርሃንነታቸው በዚህ በኃላፊው ዓለም ብቻ ተወስኖ እንዲቀር አይደለም፤ አማላጅነታቸውም በሕይወተ ሥጋ ሳሉ ነው እንጂ ከሞቱስ በኋላ ማማለድ የለባቸውም እንዳይባልማ የሰው ልጅ በግርማ መንግሥት በክበብ ትስብዕት መጥቶ በጌትነቱ በተገኘ ጊዜ እናንተም በ12 መንበሮች ተቀምጣችሁ በ12ቱ ነገደ እሥራኤል ላይ ትፈርዳላችሁ ብሎአቸዋል። ማቴ.19፥28 ማማለድና መፍረድስ የቱ ይቀላል?

ጠቢቡ ሰለሞንም ቅዱሳን ጻድቃን ከሞቱ በኋላ በኃጥአኑ ላይ እንደሚፈርድባቸው ለደጋጉ እንዲፈርድላቸው ሲያስረዳ «ወብእሲሰ ጻድቅ መዊቶ ይኬንን ረሲዓነ እንዘሀለው ሕያዋኒ ሆሙ» ጻድቅ ሰው ግን ከሞተ በኋላ በሕይወት ሳሉ እግዚአብሔርን የዘነጉ ሰዎችን ይገዛል (ይቀጣል) ይላል። ጥበብ.2፥20 (አማርኛው ግን 4፥16 ላይ ነው።)

በዚሁም መሠረት መሞት ማለት 1ኛ የነፍስና የሥጋ መለያየት ሲሆን፤ 2ኛ መሞት ማለት ደግሞ በአካለ ነፍስ ወደ መንፈሳዊው (ረቂቁ ዓለም መሄድ) ወደ እግዚአብሔር መድረስ (መመለስ) ማለት ነው። በሞት ጊዜ ነፍስ ወደ እግዚአብሔር እንደምትሄድና ሟቹ ሰው በነፍሱ እግዚአብሔርን ማየት እንደሚችል መጽሐፍ ቅዱስ በሰፊው ያስረዳል።

ጻድቁ ኢዮብ በነፍሱ ወደ እግዚአብሔር እንደሚሄድ ሲያስረዳ «ይህ ቁርበቴ ከጠፋ በኋላ በዚያን ጊዜ ከሥጋዬ ተለይቼ እግዚአብሔርን እንዳይ [illegible]ታለሁ። እኔ ራሴ አየዋለሁ። አይኖቼም ይመለከቱታል» ሲል ተናግሯል። ኢዮብ.19፥26።

እንዲሁም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ መሞት ማለት በነፍስ ወደጌታ መሄድና ከጌታ ጋር በክብር መኖር ማለት መሆኑን ሲገልጽ «ለእኔ ሕይወት በክርስቶስ እምና መሞት ጥቅም ነውና። ነገር ግን በሥጋ መኖር ለኔ የሥራ ፍሬ ቢሆንም ምን እንደምመርጥ አላውቅም። በእነዚህም በሁለቱ እጨነቃለሁ። ልሄድ ከክርስቶስም ጋር ልኖር እናፍቃለሁ። ከሁሉ ይልቅ እጅግ የሚሻል ይህ ነውና» በማለት አስረድቷል። ፊልጵ.1፥24–24።

ነገር ግን በቅዱሳን ክብር የማያምኑ መናፍቃን ከዚህ በላይ የቀረበውን ማስረጃ ሳለመቀበል ብዙ ማደናገሪያ ለመደርደር ይሞክራሉ። ይህም የሚያሳየው «አውቆ የተደበቀን ቢጠሩት አይሰማም» እንደሚ ባለው እነሱ አውቀውና ወደው የቅዱሳንን አማላጅነት ስለካዱ ምንም ዓይነት ማስረጃ አይመልሳቸውም። ይሁን እንጂ መጽሐፍ ቅዱስ ግን «መኑ ውእቱ ዘይትዋቀሶሙ ለሕሩያነ እግዚአብሔር» የእግዚአብሔር ምርጦች ቅዱሳንን አልበቃችሁምና አታማልዱም በማለት የሚከራከራቸው የሚወቅሳቸው ማን ነው? እርሱ ያከበራቸውንስ የሚያዋርድ ማን ነው? በማለት አስተምሯል። ሮሜ.8፥30–31።

ቅዱሳንም በሃይማኖትና በምግባር የጸኑ ስለሆነ የሚሳናቸው ነገር የለም። ተራራ ማፍለስ፤ ሙት ማስነሳት፤ ሕሙማንን መፈወስ እንደቻሉ ካወቅን፤ ማማለድ እንደማይሳናቸውም እናምናለን።

እንግዲህ ክብረ ቅዱሳን እንዲሁ በአጭር ጊዜ ተነግሮ በአጭር ጽሑፍ ተጽፎ የሚያልቅ አይደለም። በአጭሩ ያልቃል ብሎ መገመት ወይም ማሰብ፤ አባይን በጭልፋ እንደሚባለው ይሆናል። ምክንያቱም የቅዱሳን ምልጃ በብሉይ ኪዳንና በሐዲስ ኪዳን፤ የቅዱሳን ምልጃ በአጸደ ሥጋና በአጸደ ነፍስ የቅዱሳን ረቂቅ እውቀት በሚል ርዕስ በአጭሩ ለመግለጽ ሞከርኩ እንጂ የእግዚአብሔርን ሕግጋት (ትእዛዝ) የፈጸሙና በጾምና በጸሎት ተወስነው የኖሩ በነፍስና በሥጋ ከፈጣሪያቸው ክብር የተሰጣቸው ብዙ ናቸው። ጸጋቸውና ክብራቸውም ተነግሮ አያልቅምና ለጊዜው ከዚህ ይቆየን።

ክብረ ቅዱሳን መድኃኔ ዓለም በረድኤት አይለየን

አሜን!!

## ከ ወ ጣ ቱ ለ ወ ጣ ቱ

# «የኔታ» ቤተልሔም

ቤተ ልሔም ካሣ ትባላለች፤ የሃያ ዓመት ወጣትና የአራተኛ ዓመት ዩኒቨርስቲ ተማሪ ናት። በያዝነው ዓመት ሐምሌ ወር በሒሳብ ትምህርት የባችለር ድግሪዋን ትጨብጣለች። ቤተልሔም በሕዝበ ክርስቲያን ዘንድ በይበልጥ የምትታወቀው ግን በዩኒቨርስቲ ተማሪነቷ ሳይሆን በሰንበት ት/ቤት በምታበረክተው የቤተክርስቲያን አገልጋይነቷ ነው።

ቤተልሔም በደብረ ጽጌ ቅዱስ ዑራኤል ሰንበት ት/ቤት መሳተፍ የጀመረችው ገና የስምንተኛ ክፍል ተማሪ በነበረችበት ወቅት ነበር። ከዛን ጊዜ ጀምሮ በሰንበት ት/ቤቱ በተለያዩ የሥራ ዘርፎች በተለይ ደግሞ በዘማሪነት ታላቅ አገልግሎት በማበርከት ላይ ትገኛለች። የተለያዩ የግዕዝ መዝሙሮችን በላቀና በረቀቀ ያሬዳዊ ዜማ ስታዜም ያዩ ሰዎች ቤተልሔምን «የኔታ» የሚል የአድናቆት የቅጽል ስም ሰጥተዋታል። ቤተልሔም ስሟ ብቻ ሳይሆን ምያዋም «ከቤተልሔም የዜማ ባሕር የተቀዳ ይመስላል» የሚሉም አልጠፉም።

እኛም በወጣቱ ዘንድ ብቻ ሳይሆን በካህናትና ምእመናን ጭምር ታዋቂ የሆነችውን ወጣት የፈለገ ጥበብ «የበከር እንግዳ» አድርገናታል።

**ፈ**ለገ ጥበብ – ለመጀመሪያ ጊዜ በሰንበት ት/ቤት የተመዘገብሽው መቼ ነበር?

**ቤ**ተልሔም – በ1982 ዓ.ም ክረምት ከ8ኛ ወደ 9ኛ ክፍል ስዛወር ነበር የገባሁት።

**ፈ**ለገ ጥበብ – በሰንበት ት/ቤት ከገባሽ በኋላ መንፈሳዊው አገልግሎቱ በመደበኛ ትምህርትሽ ላይ ያሳደረብሽ ተጽእና አልነበረም?

**ቤ**ተልሔም – ሁለቱንም በቅንጅትና በፕሮግራም አጣጥሜ እሠራቸው ስለ ነበር ችግር አልፈጠረብኝም።

**ፈ**ለገ ጥበብ – ብዙ ሰዎች ካለሽ ጥሩ የተፈጥሮ ድምፅ ባሻገር በግዕዝ ቋንቋ የዜማ ችሎታሽም ሲያደንቁሽ



ይሰማል። ይህንን ችሎታሽን እንዴት ነው ያዳበርሽው?

**ቤ**ተልሔም – በሰንበት ት/ቤታችን የተወሰነ የግዕዝ ትምህርት ከመዝሙር ጋር እንማራለን፤ ከዘር ቁጥር ጀምሮ አጣጣሉን፤ የግዕዝ አገባቡን ጭምር ስለ ምንማር አልከበደኝም። በዚሁ ላይ ፍላጎትና ጥረት ካለ ችግር አይኖርም።

**ፈ**ለገ ጥበብ – በየዐውደ ምሕረቱ ስትዘምሪ የሚያዩሽ አንዳንድ ሰዎች «የኔታ» እያሉ ሲጠሩሽ ሰምቻለሁ? ጓደኞችሽ በግንባር እንደዚህ እያሉ ይጠሩሻል?

**ቤ**ተልሔም – ሰዎች እንደዛ የሚሉኝ በማቀርበው መዝሙር እየተደሰቱ ይመስለኛል። ጓደኞቼ ግን በስሜ ነው የሚጠሩኝ።

**ፈ**ለገ ጥበብ – በአጠቃላይ ከሕዝብ የሚሰጥሽ የሞራል ድጋፍ ምን ይመስላል?

**ቤ**ተልሔም – ሕዝቡ ለኔ ብቻ ሳይሆን ለሰንበት ት/ቤታችን ጥሩ አመለካከት ስላለው ያበረታታናል፤ እኛም የምናገለግለው እግዚአብሔርን ስለሆነ በሥራችን እንደሰታለን።

**ፈ**ለገ ጥበብ – እስከ አሁን በሰንበት ት/ቤት በቆየሽባቸው ዘጠኝ ዓመታት ውስጥ የሰንበት ት/ቤቱን ይበልጥ እንዲጠናከርና እንዲስፋፋ የላቀ አስተዋጽኦ አበርክተዋል የምትያቸው የደብር አስተዳዳሪዎች (አስተዳዳሪ) ይኖራሉ?

**ቤ**ተልሔም – አዎን አሉ፤ በተለይ ለአከ ማርያም አየለ በኛ ላይ በጣም ከፍተኛ አድናቆት ነበራቸው፤ ያበረታቱንም ነበር። በይበልጥ ደግሞ በመዝሙር በኩል ትልቅ አስተዋጽኦ አድርገውልናል።

**ፈ**ለገ ጥበብ – የናንተ ሰንበት ት/ቤት ኅብረትና ጥንካሬ ከሌሎች

**በጸሎት እየተጋን ማገልገል አለብን**

www.ethiopianorthodox.org

ጋር ስታወዳድሪው በምን ደረጃ ላይ ይገኛል ትያለሽ?

**ቤ**ተልሔም – ሁሉንም ባይሆንም የምናውቃቸው የሰንበት ት/ቤቶች አሉ። የኛ ከእነዚህ ጋር ሲወዳደር ምን እንደሚመስል ሕዝቡ ቢመዝነው የሚሻል ይመስለኛል። የራሳችንን በተመለከተ ሁሉም የሰንበት ት/ቤታችን አባል እግዚአብሔርን ለማገልገል ከልብ ነው የሚሠራው፤ በትርፍ ጊዜያችን ጭምር ነው የምናገለግለው። ምክንያቱም በሰንበት ት/ቤት እግዚአብሔርን ነው የምናገለግለው፤ የሰንበት ት/ቤቶችን አሁን ካለበት ደረጃ የደረሰውም እያንዳንዱ አባል ከእግዚአብሔር በተሰጠው ዕውቀት ከልቡ እግዚአብሔርን ስለሚያገለግል ይመስለኛል።

**ፈ**ለገ ጥበብ – ከአሁን በፊትም ሆነ አሁን የተለያዩ ግለሰቦች መንፈሳዊ መዝሙሮችን በካሴት እያሳተሙ ለገበያ ሲያውሉ ይታያሉ። የመዝሙሮቹ የዜማ ጥራትና መንፈሳዊ ይዘት እንዴት ነው የምትገመግሚያቸው?

**ቤ**ተልሔም – በሙሉ ባይሆንም በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በመውጣት ላይ ያሉ መዝሙሮች ጥራታቸው እየቀነሰ መጥቷል። በኔ ግምት ያሬዳዊ ዜማ ጠብቀው የሚወጡ አይደሉም። አንዳንዶቹ «አንቺ ሆዬ» ዓይነት ናቸው። ገበያ እንዲያገኙ ተብለው የሚወጡ ይመስለኛል። የቤተ ክርስቲያናችን የዜማ ሥነ ሥርዓት ጠብቀው የሚወጡም አሉ። በአጠቃላይ ግን ለወደፊቱ የሰንበት ትምህርት ቤት ማደራጃ መምሪያ በዚህ በኩል ክትትልና ቁጥጥር ቢያደርግ ጥሩ ይመስለኛል።

**ፈ**ለገ ጥበብ – ማደራጃ መምሪያው ይህንን ችግር ለማቃለል ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከየአድባራቱ ሁለት ሁለት ወጣቶችን በማሰባሰብ መዘምራን ማሰልጠን ጀምሯል። ይህንን ስልጠና እንዴት ታይዋለሽ?

**ቤ**ተልሔም – የዚህ ዓይነት ሥልጠና ጥሩ ውጤት የሚያስገኝ ይመስለኛል፤ በመጀመሪያ ደረጃ መዝሙሮች አንድ ወጥ እንዲሆኑ ያስችላል። በሁለተኛ ደረጃ መዝሙሮቹ ያሬዳዊ መሥመራቸውን ሳይለቁ እንዲቀጥሉ ያስችላል። እስከ አሁን ባለው ሁኔታም ብዙ ለውጥ እየታየ ነው። ጥረቱ ግን ይበልጥ ተጠናክሮ መቀጠል አለበት።

**ፈ**ለገ ጥበብ – አንቺስ በግልሽ የመዝሙር ካሴት ለማሳተም (ለማውጣት) ዕቅድ አለሽ?

**ቤ**ተልሔም – በግሌ ሳይሆን በሰንበት ት/ቤቱ ስም ለማሳተም ሃሳቡ አለ። ሥራው ሰፋ ያለ ጊዜ የሚጠይቅ በመሆኑና እስከ አሁን በነበረው ሁኔታ ከትምህርቴ ጋር ስላልተመቸኝ ነገሩ ሊዘገይ ችሏል። ደግሞ ማውጣት ያለብን ጥራት ያለው፣ የቤተክርስቲያን አባቶችና ምእመናን የሚወዱት፣ ያሬዳዊ ዜማ የተከተለ ስለሆነ ሰፋ ያለ ጊዜ ይፈልጋል። ለወደፊቱ ግን በእግዚአብሔር ፈቃድ ካሴት ለማሳተም ዕቅዱ አለን።

**ፈ**ለገ ጥበብ – የወደፊት ዕቅድሽ ምንድነው?

**ቤ**ተልሔም – እግዚአብሔር እስከፈቀደ ድረስ ሰንበት ት/ቤቶችንና ቤተክርስቲያኔን ለማገልገል ነው።

**ፈ**ለገ ጥበብ – በአጠቃላይ ለሰንበት ት/ቤት ወጣቶች የምታስተላልፊው መልእክት አለ?

**ቤ**ተልሔም – ሁላችንም በሰንበት ት/ቤት ውስጥ ስንኖር ማሰብ ያለብን የእግዚአብሔርን አገልግሎት ነው፤ ምእመናን እኛ በምናቀርበው አገልግሎት ምን ያህል ትምህርት እንደሚያገኙ እያየን ተግባራችንን በትጋት ማከናወን አለብን፤ ግዴታም አለብን። በተለያዩ ጊዜያት በሚነሱ ውዥንብሮች እየተታለልን አገልግሎታችንን ማቋረጥ (ማቀዝቀዝ) የለብንም። ከውስጥም ከውጭም የተለያዩ ችግሮች ሊከሰቱ ይችላሉ፣ ግን ማንም ክርስቲያን ባጠገቡም ባለ ነገር፣ ከአቅሙ በላይ ቢሆንም ሊፈታ አይገባም፤ የሚገጥመንን ፈተና ለማሸነፍ ከእግዚአብሔር ጋር በጸሎት እየተጋን ማገልገል አለብን።

### ምናለ አንድ እኔን ብትተወኝ

ጥንት ነው አሉ፣ ነጋ ጠባ መሸ ነጋ ፈጣሪያቸውን «እድሜስጠኝ» እያሉ የሚጸልዩ አንዲት ባልቴት ነበሩ። «ሁል ጊዜ እድሜ ስጠኝ ከእለታት አንድ ቀን እግዚአብሔር ጸሎታቸውን ሰምቶ በሰው አምሳል ተገለጸላቸውና «ሁል ጊዜ እድሜ ስጠኝ እድሜ ስጠኝ ትያለሽ ለመሆኑ እድሜሽን ምን ያህል እንዳደርግልሽ ትፈልጊያለሽ?» አላቸው። ሁኔታው ያላሰቡት ያልገመቱት ቢሆንባቸው ደነገጡ።

አንድ ሺህ...ሁለት ሺህ... አምስት...አሥር አምስት መቶ ሊሉት ፈለጉና ሲያስቡት ጊዜ አነሰባቸው፤ ሺህ...አሁንም አላረካቸውም። ሚሊዮን ቢሉት እንኳን ዞሮ ዞሮ አንድ ቀን መሞታቸው እንደማይቀር ታሰባቸው። በዚህን ጊዜ «ምናለ አንድ እኔን ብትተወኝ» አሉትና አረፉት።

# አሥራት አብርሃም ባስልዮስ

ዲያቆን አሥራት አብርሃም ባስልዮስ የ30 ዓመት ወጣት ነው። የዕድሜውን ሦስት አራተኛ ያሳለፈው በሰንበት ት/ቤት ውስጥ ነው። ከ1979 ዓ.ም ጀምሮ በአመራር



አባልነት በማገልገል ላይ ይገኛል። የደብረ ጽጌ ቅዱስ ዑራኤል የሰንበት ት/ቤት ታሪክ ሲወሳ የዲያቆን አሥራት ስም አብሮ መነሳቱ የግድ ነው፤ አሥራትን ከሰንበት ት/ቤቱ የሰንበት ት/ቤቱን ከአሥራት ለይቶ ማየት አይቻልም።

አሥራት በሕፃንነቱ እርግቦችን መንከባከብና ማርባት ይወድ ነበር። ቀስ በቀስ በአካልም በአእምሮም እያደገ ሲሄድ ሲሞንና ጴጥሮስ በመረብ ዓሣ ማጥመዳቸውን ትተው ሰውን በወንጌል ሊያጠምዱ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ተከትለው እንደ ሄዱ ሁሉ እርግቦችን ትቶ «ሕፃናት እርግቦችን» ሊንከባከብ ወደ ሰንበት ት/ቤት ገባ። ዲያቆን አሥራት ባለፈው እምነት የለሽ የደርግ ሥርዓት ወቅት ሳይቀር በለጋ ዕድሜው ለሃይማኖቱ የሚቻለውን ሁሉ አድርጓል። ዛሬም ቢሆን ከ22 ዓመታት አገልግሎት በኋላ በቃኝ ደከመኝ አላለም። ለመሥራት ያለው ፍላጎት ለእምነቱ የሚያሳየው ቀናኢነት የጋለና የላቀ ነው።

እኛም የዲያቆን አሥራት ተመክሮ ለሌሎች ወጣቶችም ትምህርት ይሰጣል ከሚል ልምዱን

## ተግባራችን ራሱ ፍቅር ሊሰብክ ችሏል

እንዲያካፍለን ጠይቀነዋል። የቃለ ምልልሱ «ጭማቂ» እነሆ:-

**ፈ**ለገ ጥበብ – ወደሰንበት ት/ቤት እንዴትና መቼ እንደገባህ ታስታውሰዋለህ?

**ዲ**ያቆን አሥራት – ቀኑና ዓ.ምሕረቱን ሳይቀር አስታውሰዋለሁ፤ ኅዳር 21 ቀን 1969 ዓ.ም ነበር። ለዚህ ያበቁኝ አያቴ ነበሩ። አያቴ ገና ሕፃን እያለሁ ወደ ቤተ ክርስቲያን እየያዙኝ ይመጡ ነበር። እኔም ወጣቶች ሲዘምሩ፣ ዲያቆናት ሲቀድሱ እያየሁ በጣም ደስ ይለኝ ነበር።

**ፈ**ለገ ጥበብ – ዲያቆን እንደ ሆንክ ይታወቃል። ለመሆኑ የዲቁና ማዕረግ ያገኘኸው መቼ ነው?

**ዲ**ያቆን አሥራት – በ1972 ከብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ እጅ ነው የተቀበልኩት። በዝዋይ ማሰልጠኛ ሠልጥኛለሁ።

**ፈ**ለገ ጥበብ – ወደሰንበት ት/ቤት የገባኸው ገና በሕፃንነትህ ወቅት በመሆኑ ከሰንበት ት/ቤት ተሳትፎ ሌላ የአብነት ትምህርቱንም ትከታተል ነበር። ይህ በመደበኛው የዘመናዊ ትምህርትህ ላይ ችግር አልፈጠረብህም?

**ዲ**ያቆን አሥራት – ችግር አልፈጠረብኝም፤ ቀን ቀን መደበኛ ትምህርቴን እማራለሁ ማታ ማታ አባቶች ሥር ሁኜ የአብነት ትምህርቴን እከታተላለሁ፤ እንዲያውም የቤተ ክህነት ትምህርት መማሬ ዘመናዊው ትምህርት በተሎና በአጭር ጊዜ እንዲገባኝ የረዳኝ ይመስለኛል።

**ፈ**ለገ ጥበብ – አንተ የሰንበት ት/ቤት አባል በሆንክበት ወቅት ሰንበት ት/ቤቱ ምን ዓይነት አቋም ነበረው?

**ዲ**ያቆን አሥራት – እኔበምገባበት ሰዓት የቅዱስ ዑራኤል ሰንበት ት/ቤት አደረጃጀቱ ደህና ነበር። እርግጥ ወቅቱ አስቸጋሪ ነበር። እድገት በኅብረት በኋላ ደግሞ ቀይሽብር እንዲህ እንዲህ ዓይነት ችግሮች ስለነበሩ የአባላቱ ቁጥር አነስተኛ ነበር። በነበረው የወቅቱ ችግር ምክንያት እንቅስቃሴው ሊያይል ባይችልም ቃለ እግዚአብሔሩ አልታጐለም።

**ፈ**ለገ ጥበብ – በጊዜው ከቀበሌዎችም ሆነ ከሌሎች የመንግሥት አካላት በሰንበት ት/ቤት ላይ ይደርሱ ስለነበሩ ሌሎች ችግሮችስ በተጨማሪ የምትነግረን ይኖራል?

**ዲ**ያቆን አሥራት – በደርግ ጊዜ በጣም ተጽእኖ ነበረብን፤ የምንማርበት ት/ቤት ለኪነት ማሰልጠኛ እንዲሆን በማድረግ ሆነ ብለው አሥር ሰዓት ላይ እንዳንገለገልበት ያደርጉ ነበር። አንዳንዴ ደግሞ መዝሙር የምንዘምርበትን ልብሰ ተክህኖአችንን እየለበሱ ኪነት ይዘፍኑበታል። በዚህም ወጣቱ መንፈሳዊ ስሜቱ ይረበሽ ነበር። እሑድ እሑድም ወደ



www.ethiopianorthodox.org

አኢወማ ስብሰባ ካልወጣችሁ እንባላለን፣ በአሰሳ እንያዛለን።

**ፊለገ ጥበብ** – ሰንበት ት/ቤት መሳተፍ ከጀመርኩ በኋላ በጣም አስቸጋሪ ሁኔታ አጋጥሞኛ ነበር የምትለው ሁኔታ አለ?

**ዲያቆን አሥራት** – ከውጭ ብቻ ሳይሆን ከቤተክርስቲያናችንም ውስጥ በጣም አስቸጋሪ ሰዎች ነበሩ። ችግሮቹ ግን በእግዚአብሔር ኃይል ተወግደዋል። ከማስታውሳቸው ገጠመኞች በሰንበት ት/ቤቱ አመራር ውስጥ ከነበርን ሰዎች መካከል ሦስታችን በአብዮት ጥበቃ ታፍሰን ለብሔራዊ ውትድርና የተወሰድንበት አጋጣሚ ነው። እነዚህ ሰዎች እዚህ ከቆዩ ወጣቱን ወደ መንፈሳዊ ሕይወት ይመሩታል ከሚል ነበር የታፈስነው። ይሁንና በእግዚአብሔር ፈቃድ በደህና ተመልሼ የሰንበት ት/ቤቱን እንደገና ለማደራጀት ቻልኩኝ። እንዲያውም እግዚአብሔር ከዛ ሁሉ መከራ ሰውሮ ስላዳነኝ ከበፊቱ በበለጠ እግዚአብሔርን ለማገልገል ወሰንኩኝ።

**ፊለገ ጥበብ** – ከብሔራዊ ውትድርና መልስ ስለነበረው ሁኔታ ብታብራራልን?

**ዲያቆን አሥራት** – ደርግ ሳይወድቅ አፋፍ ላይ እንዳለ ነበር ከብሔራዊ ውትድርና የመጣሁት፣ ያኔ ሀሳቤ በግሌ ሥራ ለመሥራት ነበር። ይሁንና በወቅቱ የነበሩ የደብሩ አስተዳዳሪ መልአከ ሰላም ክፍለ ማርያም ተሻለ የሰንበት ት/ቤቱ ስለተዳከመ እናጠናክረው ስላሉኝ መጣሁ። ያኔ አምስት ልጆች ብቻ ነበርን። ሰኔ 3 ቀን 1983 ዓ.ም በአዲስ መልክ ተደራጅተን ሥራችንን ጀመርን። አሁን እግዚአብሔር ይመስገን የሰንበት ት/ቤታችን በሕፃናት ከ380 በላይ ትላልቆች (ወጣቶች) ደግሞ 570 በአጠቃላይ ከ950 በላይ አባላት አሉት።

**ፊለገ ጥበብ** – ሰንበት ት/ቤታችሁ ከሌሎች ሰንበት ት/ቤቶች የበለጠ ጐላ ብሎ ይታያል፣ ምክንያቶቹ ምንድናቸው።

**ዲያቆን አሥራት** – የመጀመሪያውና ዋናው ምክንያት በመካከላችን ጠንካራ ፍቅር ስላለን ነው። እርስ በርሳችን እንከባበራለን፣ እንግባባለን፣ ተጣጥመን ስለምን ሠራም ሥራችን ውጤት ሊያገኝ ችሏል፣ ተግባራችን ራሱ ፍቅር ሊሰብክ ችሏል። ሌላው የኛ ሰንበት ት/ቤት ከሌሎች ለየት የሚያደርገው አስተዳደሩ ነው። አንድ የሰንበት ተማሪ እንደመጣ ከበሮ፣ ጸናጽል፣ መቋሚያ አይዝም። በቅድሚያ ቤተ እግዚአብሔር ለማገልገል የሚያስ ችለው የሥነ ምግባር ትምህርት እየተ ከታተለ ለአንድ ዓመት ይቆያል። እንደገና ለአንድ ዓመት ያህል ያሬዳዊ መዝሙር እንዲማር ይደረጋል። ወደዋናው አገልግሎት የሚገባው በሦስተኛ ዓመቱ ነው። ሁለት ዓመት የአመክሮ ጊዜ አለ ማለት ነው።

በተለይ ለመዘምራን ደግሞ ስለመ ዝሙሩ ምሥጢራዊ ሥርዓት እንዲ ማሩ እናደርጋለን። የአስተዳደር ትምህርትም ይሰጣል። የተማሩትን ያያሉ፣ ያዩትን በተግባር ያውላሉ። ወጣቱ እርስ በርስ የሚማርባቸው የመተራረሚያ መድረኮችም አሉት። በየሦስት ወሩ አጠቃላይ ስብሰባ ይደረግና ወጣቱ በውስጡ የታዩትን ድክመቶች እያነሳ ይወያያል። ደካማ ባሕርይና አሠራር ባሳዩ አባላት ላይም ሂስ ይቀርባል። አንድ ሰው ጥፋት ከተገኘበት እንደ ጥፋቱ ለተወሰነ ጊዜ በአመክሮ እንዲቆይ ይደረጋል። በአጭሩ ስህተቶቻችን ሥር ሳይሰዱ እንዲታረሙ እናደርጋለን። የጥንካሬ ያችን ምሥጢር ከዚህ የመነጨ ነው።

**ፊለገ ጥበብ** – ወጣቱን መስለው በሰንበት ት/ቤታችሁ ሰርገው ለመግባት የሚሞክሩትን መናፍቃን በምን ዘዴ ነው የምትከላከሉዋቸው? ተመኩሮአችሁ ለሌሎች ብታካፍለን?

**ዲያቆን አሥራት** – የኛ ሰንበት የዚህ ዓይነት ችግር አጋጥሞት አያውቅም። በመካከላችንም መከ ፋፈል አልታየም። ለዚህም ሁለት ምክንያቶች አሉ። አንደኛው በሰንበት ት/ቤታችን የጽዋ ማኅበራት የሉም። ማኅበረ ጻድቃን፣ ማኅበረ ናላዊ፣ ምናምን የሚባል ነገር የለም። በማኅበር፣ በጽዋ ስም ነዳያንን ማብላት፣ የታረዘን ማልበስ፣ የተጠማን ማጠጣት፣ ወገንን መደገፍ ተገቢ መሆኑን እናምናለን። በበኩላችን በዓመት ሁለት ጊዜ ነዳያንን መግቦት እናደርጋለን፣ እናለብሳለን፣ ነዳያን ሲሞቱ አጥበን ገንዘን በነፃ እንዲቀበሩ እናደርጋለን። ለአባሎቻችንም ከዚህ የበለጠ አገልግሎት እንደ ሌለ ስለምናስ ተምራቸው ጽዋ ምናምን እንግባ አይሉም። የሥራ አመራር ኮሚቴ አባላትም በመመሪያው መሠረት ጊዜያቸውን ጠብቀው ስለሚለዋወጡ በመካከላችን ችግሮች አልተከሰቱም። መናፍቃን የሚገቡት በጽዋ፣ በማ ኅበር ስምና አመራር ላይ መከፋፈል ሲፈጠር ነው።

በግሌ ግን ወጣቱ ይሠራልናል፣ ያገለግለናል እያለ በተደጋጋሚ ስለሚመርጠኝ ለሕይወቴ አስቸጋሪ የሆኑ ሁኔታዎች አጋጥመውኛል። በየጊዜው በአማርኛና በእንግሊዝኛ የተፃፉ «እኛ እስከ አሁን አዲስ አበባ ያሉትን የሰንበት ት/ቤቶች ተቆጣጥ ረናል፣ እስከ አሁን ያስቸገረን የሩፋኤል ብቻ ነው። ለዚህ ደግሞ አንተ ስለማትለቅ ነው፣ ስለዚህ ከእንግዲህ ወዲያ በምግብ ወይም በመኪና አደጋ እናደርስብሃለን ከዚህ ቀን ጀምሮ ሰንበት ት/ቤቱን ልቀቅ»

ወዘተ የሚሉ ደብዳቤዎች ይደር ሱኛል። ደብዳቤዎቹ አሁንም በእጄ ላይ አሉ። ቢሆንም እነዚህ ነገሮች ለኔ ይበልጥ ጥንካሬ እየሰጡኝ ሄዱ። ለምን ነፍስንም ሥጋንም መቅጣት የሚችለው እግዚአብሔር እንጂ እንዲህ የሚሉትን መፍራት እንደሌለብኝ ከቅዱስ መጽሐፍ የተረዳሁት ስለሆነ እግዚአብሔር ይከበር ይመስገን በዚህ ሳልሸነፍ በእግዚአብሔር ፈቃድ አገልግሎቴን ሳላቋርጥ እየሠራሁ እገኛለሁ።

**ፊለገ ጥበብ** – ሌሎች የሰንበት ት/ቤቶች ከእናንተ ሰንበት ት/ቤት ሊማሯቸው ይገባል የምትላቸው ነገሮች አሉ? ወይም ደግሞ ለወጣት የሰንበት ት/ቤት አባላት የምታስ ተላልፈው መልእክት ይኖርሃል?

**ዲያቆን አሥራት** – ለሰንበት ት/ቤት አባላት ለማስተላለፍ የምፈልገው በመጀመሪያ እግዚአ ብሔር ፍቅር ስለሚወድ «ፍቅር ካላችሁ ደቀ መዛሙርቴ መሆናችሁን ማንም ያውቃችኋል» ነው የተባልነው። ስለዚህ እርስ በርሳችን መፋቀር ይገባናል። ለሰንበት ት/ቤቶች መድከምና መውደቅ መንሥኤ ከሚሆኑት አንዱና ዋናው አለመግባባት ነው። ወጣቱ በእሳትነት የዕድሜ ክልል ያለ ኅብረተሰብ በመሆኑ በሰንበት ት/ቤቶች በአመራር ላይ የሚቀመጡ በትምህርትም በእድሜም በሰል ያሉ ቢሆን ጥሩ ይመስለኛል። ከዚህም በላይ ወጣቶች ከአብነት መምህራን ሥር ባይለዩ ይመረጣል። መተሳሰብን፣ መከባበ ርን፣ ትህትናን፣ በአጠቃላይ ግብረገ ብነትን ይማራሉ። እኔ አውቃለሁ ከኔ በላይ የለም የሚለውን ስሜት ትተው መከባበርን ይለምዳሉ። ዕውቀትን ይቀስማሉ በአጠቃላይ አባቶቻቸውን መስለው ያድጋሉ።

# ዲያቆን አምሳሉ ተፈራ

በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ የ4ኛ ዓመት ተማሪ ነው። የ25 ዓ.ም ወጣት አምሳሉ ተፈራ ተወልዶ ባደገበት የመካነ ሕይወት አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ቤተክርስቲያን በሰንበት ት/ቤት ተመዝግቦ መንፈሳዊ አገልግሎት ማበርከት የጀመረው ገና የ11 ዓመት ሕፃን እያለ ነበር። አባቱ ካህን ስለ ነበሩ አዘውትሮ ወደ ቤተክርስቲያን የመሄድ እድል ነበረው። የቤተክርስቲያን ፍቅር የተቀረጸበት ገና በጨቅላ እድሜው ነበር። በእግዚአብሔር ፈቃድ በመንፈሳዊ ሕይወት እየተሳበ እየተማረከ መጣ። የልጃቸውን ፍላጐት ያስተዋሉት አባቱ «በል ከወንድሞችህ ጋር እየተማርክ እዚሁ እደግ» ብለው ሰንበት ት/ቤት አስመዘገቡት።

አምሳሉ ተፈራ 3ኛ ክፍል እያለ የጀመረው የሰንበት ት/ቤት ተሳትፎ ዛሬ ድረስ አጠናክሮ ቀጥሎበታል። በእድሜም፣ በእውቀትም እያደገ በሄደ ቁጥር ለቤተክርስቲያን የሚሰጠው አገልግሎትም እያሳደገ መጣ። ከተራ አባልነት ወደ አመራር አባልነት ተሸጋገረ። ዛሬ ደግሞ ከደብሩ አልፎ በክፍለ ከተማው ውስጥ የሚገኙትን 16 የሰንበት ት/ቤቶች ከሌሎች ጓደኞቹ ጋር በመሆን በማደራጀትና በመምራት ላይ ይገኛል። ቀሪውን ዲያቆን አምሳሉ ራሱ ያጫውተናል።


**ፊለገ ጥበብ** – የአብነት ትምህርትህን እስከምን ያህል ነው የዘለቅኸው?

**ዲያቆን አምሳሉ** – በጣም አልገፋሁም፣ ግን አንድ ዲያቆን ሊያሟላ የሚገባውን ያህል የቃል ትምህርት ውዳሴ ማርያም፣ አንቀጸ ብርሃን፣ መልክአ ማርያም፣ መልአከ ኢየሱስ፣ በዜማ ደግሞ እስከ መስተጋብዕ ውዳሴ ማርያም ተምሬ አለሁ። ትምህርቴን አሁንም አላቋ ረጥኩም ነበር። እየቀጠልኩ እያለሁ ነበር ወደ መንፈሳዊ ኮሌጅ የገባሁት፣ በዚህ ምክንያት ብዙ አልገፋ ሁበትም። እንደዛም ሆኖ ክረምት ክረምት እማራለሁ፣ የኮሌጁን ትምህ ርቴን ሳጠናቅቅ በሰፊው ለመማር ዕቅድ አለኝ።

**ፊለገ ጥበብ** – በሰንበት ት/ቤት በአመራርነት መሳተፍ የጀመርከው ከመቼ ጀምሮ ነው?

**ዲያቆን አምሳሉ** – በመሠረቱ ከሰንበት ት/ቤት ውጭ ያሳለፍኩት ሕይወት የለኝም፣ በመሆኑም ወደ አመራር የገባሁትም በልጅነቴ ነበር ማለት ይቻላል። ለዚህም ምክንያቱ ከልጅነቴ ጀምሮ ንቁ ተሳትፎና ልምድ ስለነበረኝ ይመስለኛል። ሰንበት ት/ቤታችን በአዲስ አበባ አሉ ከሚባሉ አንጋፋ ሰንበት ት/ቤቶች አንዱ ነው። በ1957 ዓ.ም ነው የተመሠረተው። ብዙዎቹ በኛ ሰንበት ት/ቤት ያለፉት ለትልቅ ደረጃ የደረሱ ናቸው። በዛው ላይ ድሮ የነበሩት አባላት ታሪካቸውን ይነግሩን ነበር። እኔም ገና በሕፃንነቴ ያለፉትን አባቶች ታሪክ መድገም አለብኝ የሚል ምኞት (ሐሳብ) አደረብኝ። በአጭሩ የተለያዩ ኮርሶችን ካጠናቀቅኩና በንዑሳን ኮሚቴዎች ስሳተፍ ከቆየሁ በኋላ ከ1982 ዓ.ም ጀምሮ የሥራ አመራሩ ምክትል ሊቀ መንበር ሆንኩኝ። ከዛን ጊዜ ጀምሮ ከሊቀ መንበርነት ሌላ ንዑሳን ኮሚቴዎችንም ደርቤ በመም ራት በተለይ ደግሞ በትምህርትና ኪነ ጥበብ ኮሚቴ የላቀ ተሳትፎ አደርግ ነበር።

www.ethiopianorthodox.org



# የነገ ችግሮቻችንን ለመፍታት የዛሬ አንድነታችን ወሳኝ ነው

**ፈ**ለገ ጥበብ – ያለህበት የመካነ ሕይወት አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ሰንበት ት/ቤት ከሌሎች ጋር ስታነጻጽረው እድገቱና ደረጃው ከምን ሁኔታ ላይ ይገኛል?

**ዲ**ያቆን አምሳሉ – ቀደም ሲል እንደጠቀስኩት ትምህርት ቤታችን አንጋፋ ነው፣ ወደ 34 ዓመት አስቆጥሯል። ከዛ አኳያ አሁን ደህና ደረጃ ላይ ይገኛል ማለት ይቻላል። በተለይም ደግሞ በሰሜን ክፍለ ከተማ ካሉት ጠንካራ ሰንበት ት/ቤቶች መካከል አንዱ ነው።

**ፈ**ለገ ጥበብ – ከልጅነትህ ጀምረህ እዚሁ ሰንበት ት/ቤት እንደማደግህ እስከ አሁን ድረስ ካየሃቸው የደብር አስተዳዳሪዎች ለሰንበት ት/ቤቱ መጠናከርና መስፋፋት የጐላ አስተዋጽኦ አድርገዋል የምትላቸውን አባቶች ልትጠቅስልን ትችላለህ?

**ዲ**ያቆን አምሳሉ – ሁሉም የሚቻላቸውን ያህል አድርገዋል፣ ነገር ግን ነፍስ ካወቅሁበት ጊዜ ጀምሮ ካየሁዋቸው ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩት መጋቤ ካህናት ዘውዱ ወልደማርያም አንዱ ነበሩ። ጥሩ ይመክሩን ያስተምሩን ነበር። ከዛ በተጨማሪ አሁን መልአከ መዊዕ ይባላሉ! በፊት መልአከ ሣህል ገብረክርስቶስ ስብሐት! በጣም ጥሩ እንቅስቃሴ ያደርጉ ነበር፤ መልአከ ሕይወት ሐረገ ወይን ብርሃንም ለሰንበት ት/ቤቱ ጥሩ አመለካከት ነበራቸው።

**ፈ**ለገ ጥበብ – ከሰንበት ት/ቤታችሁ አባላት መካከል የአብነት ትምህርትን በመማር አባቶችን ለመተካት የሚጥሩ ወጣቶች ይኖሩ ይሆን?

**ዲ**ያቆን አምሳሉ – ልክ ነው እንደ አጋጣሚ ሆኖ የኛ ሰንበት ት/ቤት እድለኛ ነው ማለት ይቻላል። ሊቀመንበራችን በአብነት ትምህርቱም በዘመናዊውም የተሟላ ዕውቀት የያዘ ነው። መጋቢ ሥርዓት ጌዴዩን ዓለሙ ይባላል። በዘመናዊ ትምህርት በዲፕሎማ የተመረቀ ሲሆን በአብነት ትምህርትም ጐጃም ድረስ በመሄድ ቅኔ የተቀኘ በዜማም በባዕታ ተምሮ ያደገ ስለሆነ እኛንም ያስተምረን ነበር። እኔና ሌሎች ወንድሞቼ ዲያቆናት የሱ አርአያ ተከትለናል። በሱ አርአያነትና አስተማሪነት ከኔ ጋር በአንድ ጊዜ ዲቁና የተሾምነው አራት ነን። እኛን ዓይተው የሚማሩ ሌሎች ሁለት ዲያቆናትም አሉ። በአጠቃላይ በሰንበት ት/ቤታችን እየተሳተፉ ማታ ማታ እየተማሩ፣ እያስተማሩ፣ እየቀደሱ፣ ቤተክርስቲያናቸውን የሚያገለግሉ ወጣቶች አሉ።

**ፈ**ለገ ጥበብ – በየሰንበት ት/ቤቱ ከሚታዩት ችግሮች አንዱ መናፍቃን መስለው በመግባት ወጣቱን የመመረዝና የመበረዝ ሁኔታ ነው። በናንተ ይህንን ለመከላከል የቀየሳ ችሁት ስልት አለ? ካለ ምን ዓይነት ስልት?

**ዲ**ያቆን አምሳሉ – የመጀመሪያው መከላከያችን ራሳችን አውቀን ተምረን መገኘት ነው። ሲመጡብን ከአባቶቻችን በተማርነው ትምህርት ተጠቅመን አሳፍረን እንመልሳቸዋለን፣ እንቆጣጠራቸዋለን። መናፍቃን በሚመጡበት ጊዜ ወጣቱ ቀደም ብሎ ዘዴያቸውን ስለሚያውቅ (ስለተማረ፣ ስለተነገረው) የዚህ ዓይነት ባሕርይ ጠባይ ባላቸው ወጣቶች ላይ የራሱ እርምጃ ይወስዳል፣ የሚከላከልበት ስልት ይቀይሳል። ለምሳሌ ያህል በ1986 ዓ.ም በአካባቢያችን የጀሆቫ እንቅስቃሴ ተከስቶ ነበር። በመጨረሻ ግን አከሸፍነው።

**ፈ**ለገ ጥበብ – በሰንበት ት/ቤት ውስጥ ማደግህ ለአሁኑ የኮሌጅ ትምህርትህ ምን ያህል እገዛ አድርጎልሃል?

**ዲ**ያቆን አምሳሉ – እጅግ በሚገባ ጠቅሞኛል። ብዙዎቹ የትምህርት ዓይነቶች በኮሌጅ ደረጃ የሚሰጡት በጥልቀትና በስፋት ቢሆንም አብዛኛዎቹን ሰንበት ት/ቤት እያለሁ ተምሬአቸዋለሁ። ለምሳሌ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት፣ የሐዲስ ትርጓሜ፣ ሥርዓተ ቤተክርስቲያን ወዘተ...ስለሆነም ብዙዎቹ ትምህርቶች ለኔ አዲስ አልሆኑብኝም። በአጭሩ ሰንበት ት/ቤት ለኮሌጁ መጋቢ ነው ማለት ይቻላል።

**ፈ**ለገ ጥበብ – በቅርቡ የሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ የሰንበት ት/ቤት ተማሪዎችን በየክፍለ ከተማው በማደራጀትና የአንድነት ጉባኤዎችን በማቋቋም የጀመረውን እንቅስቃሴ እንዴት ታየዋለህ?

**ዲ**ያቆን አምሳሉ – የዚህ ዓይነት እንቅስቃሴ የወጣቱን አንድነትና መንፈሳዊ ሕይወት ከማጠናከሩም በላይ መናፍቃንን በጋራ ለመዋጋት ስለሚያስችል ሊበረታታ የሚገባው ነው። እዚህ ላይ በየክፍለ ከተማው የተቋቋሙት የኮሚቴ ኃላፊዎች (አባላት) ትልቅ ሚና መጫወት አለባቸው። አሁን የተጀመረው አሠራር የሞያ ልምድን ለመለዋወጥ ስለሚያስችል ችግሮቻችንን ለመፍታት ትልቁ መድረክ ሊሆንልን ይችላል። የነገ ችግሮቻችንን ለመፍታት የዛሬ አንድነታችን ወሳኝ ነው።

**ፈ**ለገ ጥበብ – ከዚህ መንፈሳዊ ኮሌጅ ተመርቀህ ከወጣህ በኋላ በይበልጥ በምን ሥራ ላይ ለማተኮር ነው የምትፈልገው?

**ዲ**ያቆን አምሳሉ – የሁላችንም ሃሳብ ቤተክርስቲያናችንን ማገልገል ስለሆነ እኔም ከዚህ ኮሌጅ ከተመረቅሁ በኋላ ቤተክርስቲያኔን ባለ አቅሜ ሁሉ በሰፊው ለማገልገል ነው። በሞላና ባለ ችሎታዬ ሁሉ ማገልገል የመጀመሪያውም የመጨረሻውም ዓላማዬ ነው። ከዚህ ባሻገር በምመደብበት አካባቢ ሰንበት ት/ቤቶችን ለማጠናከር፣ በማስተማርና በማስተባበር ያለኝን ልምድ ለማካፈል ፍላጐት አለኝ።

**ፈ**ለገ ጥበብ – በመጨረሻ ለወጣት የሰንበት ት/ቤት አባላት የምታስተላልፈው መልእክት ካለ?

**ዲ**ያቆን አምሳሉ – እግዚአብሔር አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐንስ ወንጌል ምዕ.21፥15–17 ላይ ሦስት ጊዜ ትወደኛለህን ካለው በኋላ ሦስት የአደራ ቃሎችን ለሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ እንደሰጠ እናያለን። ይህ ሁሉ የሚያመለክተው ምእመናን የተባሉ በሙሉ ናቸው እረኛ የሚያስፈልጋቸው። ቤተክርስቲያን በእረኛነቷ እነዚህን ሁሉ ልትጠብቅ ይገባታል። በበጎች ሕይወት ስናይ ግልገሎች ጠቦቶች አሉ፤ እንደዚሁም ትላልቅ በጎች አሉ። እረኛው እነዚህን ሁሉ ጠብቆ እንደሚኖር ሁሉ ቤተክርስቲያንም ልጆቿን በአንድነት ጠብቃ ማገልገል አለባት።

ወደ ሰንበት ት/ቤት አባላት ስንመጣ ግልገሎችና ጠቦቶች የተባሉት ናቸው። ስለዚህ ማንኛውም የቤተክርስቲያን አባት (አባል) የሰንበት ት/ቤት አባላትን የመጠበቅ ኃላፊነት አለበት። ወጣቱም በአባቶቹ እየተጠበቀ ተኩላ እንዳይበላው በመጠንቀቅ ከቤተ ክርስቲያን ጥላ ሥር መሆን አለበት። አባቶች የመጠበቅ ኃላፊነት ያለባቸውን ያህል ወጣቱም አባቶች የሚያዙትን የማክበር፣ ቤተክርስቲያን ገብቶ የመማር ግዴታ አለበት። ወጣቶች የአባቶቻቸውን ታሪክ፣ ትውፊት፣ ሃይማኖታቸውን ለማወቅ እንዲረዳቸው በየሰንበት ት/ቤቱ በመግባት አባል መሆን አለባቸው።

በመጽሐፍ ቅዱስ እንደምንረዳው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ለቲቶና ለፊሊሞን የነገራቸው ወጣቶች ጐበዞች ሁሉ እንዲጠብቁ ነው። «...በቃልና በኑሮ፣ በፍቅርም በእምነትም በንጽሕናም ለሚያምኑቱ ምሳሌ ሁን እንጂ ማንም ታናሽነትህን አይናቀው እስክመጣ ድረስ ለማንበብና ለመምከር ለማስተማርም ተጠንቀቅ። በትንቢት ከሽማግሌዎች እጅ መጫን ጋር የተሰጠህን፣ በአንተ ያለውን የጸጋ ስጦታ ቸል አትበል። ማደግህ በነገር ሁሉ እንዲገለጥ ይህን አሳብ ይህንም አዘውትር። ለራስህና ለትምህርትህ ተጠንቀቅ፣ በእነዚህም ጽና ይህን ብታደርግ፣ ራስህንም የሚሰሙህንም ታድናለህና። (1ኛጢሞ.4፥11–16)።

ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስም «ልጆች ሆይ ኃጢአታችሁ ስለስሙ ተሰርዮላችኋልና እጽፍላችኋለሁ አባቶች ሆይ ከመጀመሪያ የነበረውን አውቃችኋልና እጽፍላችኋለሁ። ጐበዞች ሆይ፣ ክፉውን አሸንፋችኋልና እጽፍላችኋለሁ፣ አብን አውቃችኋልና እጽፍላችኋለሁ 1ኛዮሐ.2፥12–14።» እንዳለው ወጣቱ ምንም እንኳን ትኩስ ኃይለ ያለው ቢሆን ማሸነፍ የሚገባው ክፉ ሥጋዊ ስሜትን ነው። ስለዚህ ወጣቶች ዓለማዊውን ሥጋዊውን ነገር ሁሉ ትተው ከቤተ ክርስቲያን የሚገባውን ሁሉ ለመማር እንዲችሉ በሰንበት ት/ቤት በመማር፣ በማገልገል የአባቶቻቸውን ታሪክ ለመረከብ፣ ነገ በአባቶቻቸው እግር ለመተካት፣ ዛሬ ከአባቶቻቸው መማር አለባቸው። ዛሬ ካልተማሩ ነገ ማስተማር አይችሉም። ዛሬ በአደራ መልክ የሚሰጠውን ካላዩ፣ ካልተከታተሉ አደራቸውን ሊወጡ አይችሉም። ይህን ሁሉ ለማድረግ እንዲችሉ ሰንበት ት/ቤት ገብተው መማር አለባቸው። መልእክቴ ይኸው ነው።

## ምክር

ወዳጄ ሆይ በግብዞች መንገድ አትሂድ። ግብዝ ሰው በወንድሞቹ ላይ ይታበያል፤ በገንዘብ በከበረ ጊዜም በሚስቱ ላይ ሚስት ያገባል።

አዋቂ ነኝ ብለህ በመመካት ልብህን አታስንፍ። ምናልባት ስህተት የተገኘብህ እንደሆነ ሀፍረት ይሆንብሃልና። ለሐሜተኛ ሰው ጉዳይህን አታማክረው፣ ምሥጢርህን አይችልልህምና። ነገር አብዝተህ አትናገር፣ አሁን ያልሁት ምን ነበር እስከማለት ትደርሳለህና። ነገር የሚያበዛም ሐሰቱ እንደዛ የበዛ ነው።

ከትምህርት ሕፃናት መጽሐፍ የተወሰደ

ባገኘው ሰው ሁሉ የሚያምን ዕብድ ነውና ወዳንተ በሚመጣው ሰው ሁሉ አትመን፣ ሁሉን መርምር፣ መልካሙንም አጥንተህ ያዝ። ወዳጅህ ምሥጢርህን ያወጣዋልና ከወዳጅህ መቶ ጊዜ ተጠበቅ (ተጠንቀቅ)፣ ከጠላትህ ግን አንድ ጊዜ ተጠበቅ። ምሥጢርህ በልብህ ውስጥ እስካለ ድረስ በፈቃድህ የታሠረ ይሆናል። ከአፍህ ብታወጣው ግን አንተ በማሰርያው የታሰርህ ትሆናለህ።

www.ethiopianorthodox.org

# ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን



## የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት

ከመምህር ሀብተ ማርያም ተድላ

ማንኛውም ማኅበረሰብእ መኖር የሚያስችል ሕግና ሥርዓት አለው። ስንኳን በአርአያ እግዚአብሔር የተፈጠረ ክፉንና በጐን ለይቶ የሚያውቅ አእምሮ ያለው ሰው ይቅርና እንስሳት አራዊት እንኳ አብሮ መኖር የሚያስችል ተፈጥሮአዊ ሕግ አላቸው።

የአሁን ዓለማችን የተፈጥሮን ሕግና ሥርዓት ለመዘርዘር ሳይሆን ቤተክርስቲያናችን በአንድነት የምትመራባቸው ሥርዓታት ምንና ምን እንደሆኑ በመጠኑም ቢሆን ለመግለጽ ነው።

ቤተክርስቲያን እግዚአብሔር አምላክን የምታመልክበት የአምል ኮት ሥርዓት አላት። የጾም የጸሎትና የምስጋናም ሥርዓት አላት። ይህን በመሰለ ሁኔታ ክርስቲያኖችን በአንድነት የምትመራባቸው ዓበይት ሥርዓታት የሚከተሉት ናቸው። እነዚህም፣ 7 ሥርዓታተ ቤተክርስ ቲያን የሚባሉት ሲሆኑ:-

1ኛ. ሥርዓተ ጥምቀት

2ኛ. ሥርዓተ ሜሮን

3ኛ. ሥርዓተ ቍርባን

4ኛ. ሥርዓተ ንስሐ

5ኛ. ሥርዓተ ክህነት

6ኛ. ሥርዓተ ተክሊልና

7ኛ. ሥርዓተ ቀንዲል በመባል የሚታወቁት ናቸው።

የእነዚህም የያንዳንዳቸው ሥርዓት እንደሚከተለው እንረዳለን።

## 1ኛ. ሥርዓተ ጥምቀት

በመሠረቱ ጥምቀት እኛ የሰው ልጆች ሥጋውያን ሁነን ከሥጋ እንደ ተወለድን ሁሉ፤ ሁለተኛ መንፈሳውያን ሁነን ከውኃና ከመንፈስ ቅዱስ የምንወለድበት ሥርዓት ነው። በዚህም ዳግማዊ ልደታችን የእግዚአብሔርን መንግሥት እንወርሳለን።

የአጠማመቁ ሥርዓት ከ40 እና ከ80 ቀን ሕፃናት ጀምሮ በዕድሜ ሳይወሰን ሕፃናት መካከለኞች፣ ሽማግሌዎች፣ ወንድና ሴት ሳይባል ሁሉንም በእኩልነት መጽሐፈ ጥምቀት ተደግሞላቸው፣ ልብሰ ተክህኖ በለበሱ ቄስና ዲያቆን በሥርዓተ ጸሎቱ ከሚተባበሩአቸው ካህናት ጋር ሥርዓተ ቅዳሴ ተደርሶላቸው፣ ቄሱ አሐዱ አብ ቅዱስ፣ አሐዱ ወልድ ቅዱስ፣ አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ በማለት የተጠማቂውን አካል በሚያጠልቅ ኩሬ ወይም ዕቃ የተሞላውን ውሀ ከባረከ በኋላ አጠምቀከ (ኪ) በአብ፣ አጠምቀከ (ኪ) በወልድ፣ አጠምቀከ (ኪ) በመንፈስ ቅዱስ በማለት ተጠማቂውን(ዋን) ከውሀው ሦስት ጊዜ ብቅ ጥልቅ እያደረገ ያጠምቃል። ይኩን ስምከ እገሌ ስምኪ እገሊት በማለትም ስመ ክርስትና ያወጣለታል። (ያወጣ ላታል።)

ማንኛውም በዚህ ሥርዓተ ጥምቀት ዳግም ካልተወለደ መንግሥተ እግዚአብሔርን ማየት አይችልም ዮሐ.3፥5–19። በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አንድ ጊዜ ከተጠመቁም በኋላ ሁለተኛ ጊዜ ጥምቀት የተከለከለ ነው።

## 2ኛ. ሥርዓተ ሜሮን ሜሮን

«በለሳ» ከሚባል ዕንጨት ከሚሸቱና ዘይትንትም ካላቸው ዕፀዋት ተዋሕዶ፣ በብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ጸሎት ተባርኮ፣ የተከበረ ቅብዕ ነው። ይህም ማንኛውም ወደክርስትና ዓለም የሚገባ ሁሉ የመግቢያ በሩ ጥምቀት ሁኖ በጥምቀት ከተወለደ በኋላ በዚህ ቅብዐ ሜሮን ተቀብቶ የሚያድግበትና የሚጠነክርበት ነው። ከመንፈስ ቅዱስ መወለድን የሚያረጋግጥ ማሕተምም ነው።

## 3ኛ. ሥርዓተ ቍርባን

ጌታችን መድኃኒታችንና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዕለተ ኀሙስ ኅብስቱንና ወይኑን ባርኮና ቀድሶ፣ ኅብስቱን አማናዊ ሥጋዬ ነው፤ ወይኑም አማናዊ ደሜ ነው፣ ሥጋየን የበላ ደሜንም የጠጣ የዘለዓለም ሕይወት አለው በማለት የሰጠን ለዘለዓለም ከእሱ ጋር በሕይወት መኖር የሚያስችለን ዋስትናችን ነው።

የመቍረቡ ሥነ ሥርዓት የሚፈጸመው ሥርዓተ ቅዳሴውን በአከናወነ ካህን ሲሆን ማንኛውም ቆራቢ በድፍረት ሳይሆን በትሕትና ከኃጢአቱ ተጸጽቶ በንስሐ ከተመለሰ በኋላ ሲሆን ኅብስቱ ተለውጦ ሥጋ ወልደ እግዚአብሔር፣ ወይኑ ተለውጦ ደመ ወልደ እግዚአብሔር መሆኑንና በዚህም ኃጢአቱ እንደሚሠረይለት አምኖ ነው መቀበል ያለበት። ከዚህ ውጭ ሳያምን በድፍረት የሚቀበል ቢኖር ግን በቍራኬ ፈንታ መርገምን ይቀበላል። 1ኛ ቆሮ.11፥24–29፤ ዮሐ.6፥51።

## 4ኛ. ሥርዓተ ንስሐ

ንስሐ ማለት ባደረጉት ጥፋት ወይም በፈጸሙት በደል፤ እንዲሁም በሠሩት ኃጢአት መጸጸት፣ አጥፍቻለሁ ብሎ ማልቀስ ማለት ነው። ምን ጊዜም ቢሆን የሰው ልጅ ፍጹም ስላይደለ ኃጢአት መሥራቱ የማይቀር ነው።

ኃጢአቱን ሊያስቀርለት፣ ወይም እንደ ሳሙና ሙልጭ አድርጎ ሊያጥብለት የሚችል ይህ የንስሐ ሥርዓት ሲፈጸም ብቻ ነው። ማቴ.26፥75፤ ሉቃ.15፥18፤25።

ስለዚህ ማንኛውም ከሠራው ኃጢአት ለመንጻት በንስሐ እንዲመለስና እንዲታደስ በዚህ ሥርዓት መጠቀም አለበት። ንስሐ በደለኛውን እንዳልበደለ፤ ዘማዊውን እንደ ድንግል ታደርጋለችና (አረጋዊ መንፈሳዊ)

## 5ኛ. ሥርዓተ ክህነት።

ክህነት ለሁሉም ሳይሆን በልዩ ምርጫ ባሕርያቸውንና ብቃታቸውን በሚያውቁ፣ በሚመለከታቸው ሰዎች ለተመረጡ ጥቂት ሰዎች የሚሰጥ ከፍተኛ የቤተክርስቲያን ሥልጣን ነው።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከብዙ የእስራኤል ሰዎች መካከል ጥቂቶቹን ብቻ መርጦ «በምድር ያሠራችሁት በሰማይ የታሠረ ይሆናል፤ በምድር የፈታችሁት በሰማይ የተፈታ ይሆናል» በማለት በሰጠው ሥልጣን መሠረት ላይ ጸንቶ የሚኖር አምላካዊ ሥርዓት ነው። ማቴ.11፥42፤ ማር.6፥6–13፤ ሉቃ.9፥1–5፤ ዮሐ.20፥12–23።

ምሥጢራተ ቤተክርስቲያን በሙሉ ሊከናወኑ የሚችሉት በዚህ ሥርዓተ ክህነት ነው። ማጥመቅ ማቍረብ፣ የሚችሉት ካህናት ብቻ ናቸው። ማቍረብ ሊቀ ካህናት ከሚባል ከኢየሱስ ክርስቶስ የተገኘ በረከት ነውና። ኑዛዜውን ለካህን መንገር «ራስህን በካህን አስመርምር» ያለውን የጌታችንን ትእዛዝ በመከተል ነው። ማቴ.8፥4።

ክህነት አንድ ጊዜ ብቻ የሚሰጥ ሲሆን ሥልጣንም አንዲት ብቻ ሁኖ ከፍተኛና ዝቅተኛ የለውም። ከቅስና ጀምሮ እስከ ፓትርያርክ ድረስ ያለው ሥልጣን ክህነት እኩል ነው። የተለያዩ የሥራና መዓርጋት ግን አሉ። እነሱም ተስዓቱ መዓርጋት ይባላሉ።

ተሰዓቱ መዓርጋት የተባሉትም የሚከተሉት ናቸው።

1ኛ. ሊቀ ጳጳሳት

2ኛ. ጳጳስ

3ኛ. ኤጲስ ቆጶስ

4ኛ. ቀሲስ

5ኛ. ዲያቆን

እነዚህ በጸሎትና በአንብሮተ እድ የሚሾሙ ናቸው። ከእነዚህም ከዲያቆኑ በቀር ሁሉም በቅብዕ ይከብራሉ። ፍትሐ ነገ. ራብዕ፣ ገጽ 50።

6ኛ. ንፍቀ ዲያቆን

7ኛ. አናጕንስጢስ

8ኛ. መዘምር

9ኛ. ዲያቆናዊት

እነዚህም አንብሮተ እድ ሳይደረግላቸው በጸሎት ብቻ የሚሾሙ ናቸው። ንዋያተ ቅድሳትን በማቅረብና በመዘመር፣ እንዲሁም በመላላክ የሚያገለግሉ ናቸው።

## 6ኛ. ሥርዓተ ተክሊል

ተክሊል ማለት ወንድና ሴት ተስማምተው በሚጋቡበት ጊዜ ካህናት የሚፈጽሙት መንፈሳዊ ሥርዓትና አገልግሎት ነው። የክርስቲያኖች ጋብቻ ከሌሎች ሰዎች ጋብቻ ልዩ የሚያደርገው ይኸው የተክሊሉ ምሥጢር አፈጻጸም ሥርዓት ነው።

ይኸውም በመጀመሪያ ሰውን ሲፈጥረው ወንድና ሴት አድርጎ እንዲበዙና ምድርን እንዲሞሉአት ቅዱስ ፈቃዱ መሆኑን በማረጋገጥ አንድ ጊዜ ከተገናኙም መለያየት ፈጽሞ የማይገባቸው እንደሆነ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ስለዚህ ወንድ አባቱንና እናቱን ትቶ ሚስቱን ይከተላል፣ አንድ ሥጋም ይሆናሉ፤ እግዚአብሔር አንድ ያደረጋቸውን ሰው ሊለያቸው አይችልም» ብሎ የተናገረውን መለኮታዊ ቃል በመመስከር የሚጸልዩት ጸሎትና የሚፈጽሙት የጋብቻ ሥርዓት ነው። ማቴ.19፥5–6፤ ዘፍ.1፥26፤ 2፥24።

## 7ኛ. ሥርዓተ ቀንዲል

ቀንዲል ከአባቶቻችን ከሐዋርያት ተያይዞ የመጣና ሕሙማን ሥጋና ሕሙማን ነፍስ የሚፈወሱበት ኃይል ማድረግ የሚችል የቅብዓ ቅዱስ ሥርዓት ነው።

ቅዱስ ያዕቆብም የሚታመም ሰው ቢኖር የቤተክርስቲያን ካህናትን ይጥራና ይጸልዩለት፤ ዘይትም ይቀቡት፣ በጌታ ስም የሃይማኖት ጸሎት ሕመሙን ትፈውሳለች፣ ኃጢአትንም ታስቀራለችና ብሏል። ያዕ.5፥14–16። ኃጢአትን ማስቀረትና ድውይን መፈወስ የሚቻለው የቀናች እምነት ስትኖር ብቻ ነው።

ክርስቲያኖች ለሰው ልጅ ሰባት ሀብታት ተሰጥተውታል በማለት ያምናሉ፤ ያስተምራሉም። ሰባት ሀብታት የሚባሉትም:-

1ኛ. የእግዚአብሔር መንፈስ

2ኛ. የጥበብ መንፈስ

3ኛ. የማስተዋል መንፈስ

4ኛ. የምክር መንፈስ

5ኛ. የኃይል መንፈስ

6ኛ. የዕውቀት መንፈስ

7ኛ. እግዚአብሔርን የመፍራት መንፈስ፣ ኢሳ.11፥2–3።

እነዚህንም የኢትዮጵያ ሊቃውንት

ሀብተ ትንቢት

ሀብተ ክህነት

ሀብተ መንግሥት

ሀብተ ኃይል

ሀብተ መዊዕ

ሀብተ ዝማሬ

ሀብተ ጣዕመ ዝማሬ ናቸው ብለዋቸዋል።

እንግዲህ እነዚህ ሥርዓታትም ሀብታት ከቅዱስ መጽሐፍ የተገኙ ናቸው።

www.ethiopianorthodox.org

# እኔም ወጣት ነበርኩ



ጸባቴ አርአያ ሥላሴ አጽብሃ ይባላሉ። በትግራይ ክፍለ ሀገር በተምቤን በተለይ ጻድቃኔ በሚባል አካባቢ ሐምሌ 16 ቀን 1912 ዓ.ም ተወለዱ። በአሁኑ ጊዜ ዕድሜአቸው ለዘጠና አንድ ፈሪ ሆኖአቸዋል ማለት ነው። ጸባቴ አርአያ ሥላሴ እድሜአቸውን በሙሉ ያሳለፉት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነው። በሥራ ዓለም ብቻ 52 ዓመታት ቆይተዋል። ዛሬም ቢሆን ሥራቸውን የሚያከናውኑት በጠንካራ መንፈስና በከፍተኛ ፍላጐት ነው።

ጸባቴ ከኢጣልያ ወረራ ጊዜ አንስቶ በሕይወት ዘመናቸው በርካታ ጦርነቶችን አይተዋል። በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ በብዙዎቹ ተሳትፈዋል። ኢጣልያ ሀገራችንን በወረረችበት ወቅት በእረኝነትና በቆሎ ተማሪነት እየተሰማሩ ከአርበኞች ጋር የድርሻቸውን ተወጥተዋል። በ1935 ዓ.ም የትግራይ ሕዝብ የአፄ ኃይለ ሥላሴን አገዛዝ በመቃወም «የመጀመሪያው የወያኔ ጦርነት» (አመጽ) ሲያውጅ ሁለቱን ወገኖች ለማስታረቅ ከተላኩት የትግራይ አድባራትና ገዳማት ልዑካን መካከል ጸባቴ አርአያ ሥላሴ አንዱ ነበሩ።

በ1953 ዓ.ም እነ ጀኔራል መንግሥቱ ነዋይ በንጉሥ ኃይለ ሥላሴ ላይ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ሲያካሄዱ ጸባቴ ከመጀመሪያው እስከ ፍጻሜው እዛው ዋናው ክቡር ዘበኛ ግቢ ነበሩ። ብዙዎቻችን ስለ ታኅሣሡ መፈንቅለ መንግሥት በትንሹም ቢሆን እናውቃለን። ልዑል አልጋ ወራሽ በአባታቸው በአፄ ኃይለ ሥላሴ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ አድርገው እንደ ነበርስ የምናውቅ ስንቶቻችን ነን? ጀኔራል መንግሥቱና ወንድማቸው ገርማሜ ባደረጉት የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ባደባባይ ተሰቅለው ሲሞቱ አልጋወራሽ ግን እንደ ሕፃን ልጅ በጅራፍ ተገርፈው ታለፉ። ጸባቴ የዚህን ሁሉ ምሥጢር ያውቃሉ፤

በሥራ ወዳድነታቸው፣ በጀግንነታቸው፣ ለሃይማኖታቸው በሚያሳዩት ቀናኢነት በሁሉም ዘንድ ታዋቂነት ያተረፉት ጸባቴ አርአያ ሥላሴ በቤተ ክህነት አባቶችና በንጉሠ ነገሥቱ ጭምር የተወደዱና የተከበሩ

## አርበኛው መነኩቤ

ከካሕሳይ ገ/እግዚአብሔር

ነበሩ። በመሆኑም ይመስላል ዓለም አቀፍ ኃላፊነትን ለመወጣት ወደ ኮርያ ለዘመተው የኢትዮጵያ ጦር መንፈሳዊ አባት (መሪ) ሆነው የተመረጡት።

ከሁሉም በላይ ጸባቴ አርአያ ሥላሴ ታላቅ የልማት አርበኛ ናቸው፤ በደብረ ሊባኖስ ውስጥ የሚገኙትን 1ኛ. በእቴጌ ጣይቱ የተመሠረተውና በኋላ በንግሥተ ዘውዲቱ ተስፋፍቶ የተሠራውን የሴቶች ገዳምን 2ኛ. በአፄ ኃይለ ሥላሴ የተመሠረተው (በአባ ሃና ይተዳደር የነበረው) የቤተ ሰሊሆም ጡረታ ቤትን (የደካሞች መሰብሰቢያ) 3ኛ. በራስ ካሣ የተመሠረተው የጫጋል ቀራንዮ መድኃኔ ዓለም ገዳምን (ጡረታ ቤት) በመጨረሻም ትልቁ የደብረ ሊባኖስ ገዳምን አጣምረው በማስተዳደር ተወዳዳሪ የማይገኝለት የሥራ ፍሬ ያስመዘገቡ አባት ናቸው። በአጠቃላይ የጸባቴ አርአያ ሥላሴ ታሪክ እጅግ ሠፊ ነው። ለአሁኑ ለወጣቱ ትውልድ ትምህርት ይሰጣሉ ያልናቸውን ብቻ ቆንጥረን አቅርበናል። መልካም ንባብ።



### ቃለ መጠይቅ

ፈለገ ጥበብ – ነገር ከሥሩ ውሃ ከጥሩ ነውና በመጀመሪያ የትና መቼ እንደተወለዱ የት እንደ ተማሩ በአጭሩ የሕፃንነት ዘመንዎ ምን ይመስል እንደ ነበር ቢያጫውቱን?

ጸባቴ አርአያ ሥላሴ – የተወለድኩት በትግራይ ክፍለ ሀገር ተምቤን አውራጃ ውስጥ ጻድቃኔ በምትባል ቀበሌ ሐምሌ 16 ቀን 1912 ዓ.ም ነው። በሕፃንነት ዘመኔ እዛው ትውልድ መንደሬ በምትገኘው የጻድቃኔ እመቤታችን ቤተ ክርስቲያን ትምህርት ጀመርኩኝ። በኋላም ቀቀማ ወደሚባል ሌላ ገዳም ተዛውሬ መንፈሳዊ ትምህርቴን ቀጠልኩኝ። እዚሁ ገዳም እንዳለሁ ፋሽሽት ኢጣልያ ሀገራችንን ወረረ።

እንደ አጋጣሚ በዚያን ጊዜ የኢጣልያን ወረራ ለመመከት መጥቶ ከነበረው የኢትዮጵያ ሠራዊት ጋር አቡነ ይስሐቅ ወደገዳማችን መጡና ከሳቸው የዲቁና ማዕርግ ተቀበልኩኝ። ብዙም ሳልቆይ በወረራው ምክንያት ትምህርቴን አቋረጥኩኝ። ከነፃነት በኋላ ተመልሼ ትምህርቴን እዛው ገዳም ቀጠልኩ ጸዋትወ ዜማ ድረስ በሚገባ የተማርኩት ከዚሁ ገዳም ነው። በመጨረሻም ወደ ጨሄን ገዳም በመሄድ ትምህርቴን ቀጠልኩ። የገዳሙን ትምህርት ካጠናቀቅኩ በኋላ በ18 ዓመቴ መነኮስኩ፤

ፈለገ ጥበብ – ወደ ኋላ ልመልስዎትና የኢጣልያ ወረራ ምን ይመስል እንደ ነበር፤ እግረ መንገድዎንም በወረራው ወቅት ጊዜዎን ምን እየሠሩ እንዳሳለፉት ቢገልጹልን?

ጸባቴ አርአያ ሥላሴ – ፋሽስቶች አካባቢውን ሁሉ በአውሮፕላን ይደበድቡ ነበር። እኛም በየዱሩ ገባን። ልጅ ብሆንም ትዝ ይለኛል። በተለይ ወርቅ አምባ ላይ የተደረገው ጦርነት ከፍተኛ ነበር። ልዑል ራስ ስዩም፣ ልዑል ራስ ካሣ፣ ዋግሹም ከበደ፤ አቡነ ይስሐቅ ሆነው ጦርነቱን ይመሩ ነበር። የኢትዮጵያ ጦር እየገፋ መጥቶ በጨበጣ ተቀላቀለ። ጣልያኖች ተርበተበቱ። በዛች ዕለት ብቻ 60 ሺህ የኢጣልያ ወታደር ረገፈ ይባላል። የባንዳው ቁጥርማ አይነገርም።



ጸባቴ አርአያ ሥላሴ (ሻምበል) በወታደራዊ የልብስ ማዕረጋቸው (መሃል)

ኢትዮጵያውያን ሁሉም ጀግኖች ቢሆኑም በተለይ ዋግሹም ከበደ ሲበዛ ጀግና ነበሩ። በጀግንነት ከወደቁ በኋላ ጐራዴ የያዙበት እጃቸው በጠላት ደም ከመጨማለቁ የተነሳ የተላቀቀው በመጥረቢያ ኃይል ተፈልቅቆ ነው። ሌላው ትዝ የሚለኝ ውጊያ በቆላ ተምቤን (አግቢ) ላይ የተካሄደው ጦርነት ነው። ያኔ እኛ አፋፍ ላይ ሆነን ቁልቁል እንመለከት ነበር። ጠላት ኩንታል ኩንታል የሚያክል በርሜል መርዝ ከአየር ይጥላል። ጦርነቱ እየተፋፋመ ሲሄድ አየሩ ከሁለቱ ወገን በሚወጣው የባሩድ ጭስ ተሸፈነ። ከሁለት ቀናት በኋላ ጠላት ተምቤን ገባ። ከዛም በጦር ሜዳ የደረሰበትን ጉዳት የሸፈነ እየመሰለው ሕፃን፣ ሽማግሌ፣ ሴት ሳይል ያገኘውን ሁሉ አረደ፣ ፈጀ።

እነ ደጃዝማች ገ/ሕይወት፣ ደጃዝማች መስፍን እዛው በተምቤን አካባቢ በአርበኝነት ጠላትን መዋጋት ቀጠሉ። አንድ ቀን አርበኞች ምሳ ሊበሉ መንደር ገቡ። እኛ አፋፍ ላይ ሆነን አካባቢውን እንቆጣጠራለን። በመሀሉ የፋሽስት ወታደሮች ክሩቅ ሲመጡ አየን። ከዛም «ኧረ ቀያይ በሬዎች ማሳ ገብተው እህሉን ሊበሉ ነው» ብለን ተጣራን። «ቀይ በሬ» ማለት ጣሊያን ማለት ነው። አርበኞችም ይህንን ስለሚያውቁ በአፋጣኝ ወጥተው ቦታቸውን ያዙ። ሌላ ጊዜም በዚህ መልክ ለአርበኞች መልእክት እናደርስ ነበር።

አንዳንዴ ደግሞ እንደቀድሞ ቆሎ ተማሪ እንሆንና ገዳም እንገባለን። ጣሊያኖች ገዳም ውስጥም ይመጣሉ። መነኮሳትን አርበኞችን ትደብቃላችሁ፣ ለአርበኞች ምግብ ታቀብላላችሁ፣ በዚህ በኩል ማን አለፈ? እዚህ አካባቢ ማን ዋለ? እያሉ ያስቸግሩዋቸዋል። እንደዛም ሆኖ የወገንን ምሥጢር የሚናገር አንድም አልነበረም። ለምሳሌ ያህል የደጃዝማች አባይ ልጅ ቃለ ክርስቶስ አምስቱን የአርበኝነት ዘመን ያሳለፉት በየገዳሙ የቆሎ ተማሪ በመምሰል ነው። አባታቸው አርበኛ ስለነበሩ ኢጣሊያኖች ቢያውቁ ወድያው ነበር የሚገድሉአቸው። ጣልያኖች ቃለ ክርስቶስን (ከኛ ጋር እያሉ) ብዙ ጊዜ አግኝቶዋቸዋል። ቢሆንም አላወቁዋቸውም። በመጀመሪያ በአርበኝነት ወደበረሀ የወጡ አርበኞች በርካታ ነበሩ። በአካባቢያችን እስከመጨረሻው የቆዩት ግን ደጃዝማች ገ/ሕይወት ነበሩ። ከነፃነት በኋላ ግን አልተሾሙም። ምክንያቱም ኃይለ ሥላሴ ሥልጣን ላይ የወጣው በኛ ደም ነው ይሉ ስለነበርና ባንዳዎችን በእጅጉ ይቃወሙ ስለነበር ነው።

ፈለገ ጥበብ – ለመሆኑ ወደ አዲስ አበባ እንዴት መጡ?

ጸባቴ አርአያ ሥላሴ – በአጋጣሚ በእግዚአብሔር ፈቃድ ነው። በበኩሌ አዲስ አበባ ቀርቶ መቀሌ ከተማ ድረስም እመጣለሁ የሚል ሕልምም አልነበረኝም። በገዳሜ በጥሩ ሁኔታ አገለግል ነበር። በወጣትነቴ ቁስገበዝ እስከ መሆንም ደርሼ ነበር። ወደ ጥያቄህ ልመለስና በ1935 ዓ.ም በትግራይ የመጀመሪያው «የወያኔ አመጽ» ተነስቶ ነበር። ከብዙ ውጊያ በኋላ አመጹ በኃይል ተገታ። ራስ መንገሻ በዚያን ጊዜ ከወያኔ ጋር አሉበት ይባላል፣ ሸሽተው ወደ ተምቤን ሄዱ። ደጃዝማች ገ/ሕይወት ግን ወደ ጫካ ገቡ።

ከዛ ከአዲስ አበባ መልእክተኞች መጡ። ከመልእክተኞች መካከል አቡነ ዮሐንስና (ያኔ ሊቀ ሊቃውንት ገብረ መስቀል ይባላሉ) መምህር ሰይፉ ነበሩበት። ተምቤን እንደ ደረሱ ከልዑል ራስ መንገሻ ጋር ተገናኙ።



www.ethiopianorthodox.org

«እጅዎን በሰላም ይስጡ ጃንሆይ እኛ ምንም አናደርገውም ብለዋል ስለዚህ እናስታርቆት» አሉዋቸው። እርሳቸውም እሺ አሉና ወደ አዲስ አበባ መጡ። እንደገቡ ግን ወድያው ታሠሩ።

ያኔ ታድያ አቡነ ዮሐንስ እግረ መንግዳቸው ከነበርኩበት ገዳም መጥተው አብረን ቅዳሴ ገባን። እኔ ገባሬ ሠናያት ሁኜ ቅዳሴውን መራሁ። አስቀድስን ከወጣን በኋላ ምሳ ላይ አስጠሩኝና «ከኔ ጋር አብረህ አዲስ አበባ አትሄድም ወይ?» አሉኝ። እኔም ጥሩ ደስ ይለኛል፣ የምሄደው ግን የሚያስተምሩኝ ከሆነ ነው አልኩዋቸው። ለመማር እፈልግ ነበር። በዛው ላይ አቡነ ዮሐንስ የተማሩ ሊቅ ስለነበሩ እምቢ አይሉኝም ብዩ አሰብኩ።

አዲስ አበባ እንደ መጣሁ ወድያውኑ ያቀረብኩላቸው ጥያቄ «ትምህርት ቤት ያስገቡኝ» የሚል ነበር። እርሳቸው ግን እስቲ ቆይ እስከዛው ብለው በዓታ በምግብና ሥራ አስገቡኝ። ቀጥሎ ፈለገ ሕይወት ት/ቤት ሞግዚትና መጋቢ ሁኜ ተቀጠርኩኝ። ለአራት ዓመታት እዛ አገለገልኩኝ (ከ1939–1942) ከዛም ወደ ትንሣኤ ዘጉባኤ ተዛውሬ ለአራት ዓመታት ያህል በጥራዝ ክፍልና በማረም ሥራ አገለግያለሁ (ከ1942–1946) ያኔ የትንሳኤ ዘጉባኤ ጉጅ ነበረች። አጠቃላይ ሠራተኞች ከአሥር አንበልጥም ነበር።

ፈለገ ጥበብ – ከንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የጠበቀ ትውውቅ እንደነበርዎት ሰምቻለሁ ለመሆኑ ከንጉሡ ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ የተዋወቁት እንዴት ነበር?

ጸባቴ አርአያ ሥላሴ – የረሳሁትን አስታወስከኝ፣ ገና በዓታ እያለሁ አንድ ቀን ቅዳሴ ገብተን ስንቀድስ ጃንሆይ መጡ። ያኔ በጣም ልጅ ነኝ በዛው ላይ ቁመናየ የሰጠ ነው! ወጥቼ ሳጥን አዩኝ። ከዛም አቡነ ዮሐንስን ጠርተው «ምንድነው ይህ ልጅ ካህን ነው መነኩሴ?» አሉዋቸው። «መነኩሴ ነው» ሲሉዋቸው «እግዚአብሔር ይይልዎት ይህንን የመሰለ ልጅ...? አሉ።

አቡነ ዮሐንስም መልሰው «ምን ላድርግ ያመነኩሰው የነበረበት ገዳም ነው እዚህ የመጣው ለትምህርት ብሎ ነው» አሉዋቸው።

ጃንሆይም «እንግዲህ ከዚህ ገዳም እንዳይወጣ ልብሱንና ምግቡን እኛ እንችላለን ወደ ከተማ ፈጽሞ እንዳይወጣ» ብለው አዘዙ። ወደ ቤተ መንግሥት እንዳልሄድ ግን ተከለከልኩኝ።

ፈለገ ጥበብ – ለምን ተከለከሉ?

ጸባቴ አርአያ ሥላሴ – የቤተ መንግሥት ወይዛዝርት ያሳሱታል ከሚል ነው። ምግብ ግን ከቤተ መንግሥት ይመጣልኝ ነበር። በኋላ ግን ምግቡም ቀረና ከሌሎች መነኮሳት ጋር አብሬ መመገብ ጀመርኩኝ። ፊትም ቢሆን የሚመጣልኝ ምግብ ከሌሎች ጋር እየተካፈልኩ ነበር የምበላው።

ፈለገ ጥበብ – በተባበሩት መንግሥታት ሥር ወደኮርያ ከዘመተው የኢትዮጵያ ክብር ዘበኛ ጦር ጋር በአባትነት ዘምተው መመለስዎ ይታወሳል። ለመሆኑ ለዚህ ኃላፊነት የተመረጡት እንዴት ነበር?

ጸባቴ አርአያ ሥላሴ – የዕድል የአጋጣሚ ጉዳይ ይመስለኛል። በእርግጥ ቅድም እንዳልኩህ ቁመናየ የተስተካከለና የተሟላ ነበር። ብቻ አንድ ቀን በትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት የተለመደ ሥራዬን በማከናወን ላይ እንዳለሁ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ አስጠሩኝና «አንድ ቦታ ለመሄድ ተመርጠሃልና ተዘጋጅ» አሉኝ። «ወዴት?» አልኩአቸው «ኮርያ የጦሩ አባት ሆነህ ትሄዳለህ እዛም ጦሩን ትባርካለህ ታስተምራለህ» አሉኝ እኔም ፈቃደኝነቴን ገለጽኩላቸው።

ወድያውኑ ጀኔራል መንግሥቱ ነዋይ ተጠርተው መጡ። ያኔ ኮነሬል ነበሩ። አባታችን «እንግዲህ የመረጥንላችሁ መነኩሴ እኚህ ናቸው» አሉና አስተዋወቁኝ። ጀኔራል መንግሥቱም አየት አደረጉኝና «ወጣት ስለሆኑ በጣም ይስማሙናል» አሉና ይዘውኝ ሄዱ።

ፈለገ ጥበብ – እርስዎ መነኩሴ ነዎት ከወታደሩ ጋር ከመዝመትዎ በፊት የተሰጥዎት ወታደራዊ ትምህርት ነበር?

ጸባቴ አርአያሥላሴ – በመሠረቱ እኔ የሄድኩት በመንፈሳዊ አባትነቴ ጦሩን ልናዝዝ! ላስትምር ነው። እንደዛም ሆኖ ወደ ኮርያ ከመሄዱ በፊት በጃንሜዳ ለሃያ ቀናት ወታደራዊ ትምህርት ተከታትያለሁ። የሰለጠንኩት ብቻየን ሁኜ ነው። ማንም ሰው አላየኝም። በትንሽ ቆቤ ላይ የወታደር የብረት ባርኔጣ አደርጋለሁ። ልጅነት ስላለኝ ሥልጠናው አልከበደኝም። አሰልጣኞቼ ከጠበቁት በላይ ስለሆንባቸው በጣም ይገረሙ ነበር። ሥልጠናየን እንደ ጨረስኩ ሙሉ ወታደራዊ ልብስ ለበስኩ፣ ከቆብቶው ጋር! እንድያውም ቀብቶውን ጃንሆይ ራሳቸው ነበር ያስታጠቁኝ።

ፈለገ ጥበብ – የኮርያ ጉዞ እንዴት ነበር?

ጸባቴ አርአያሥላሴ – ወደ ኮርያ ከመነሳታችን በፊት ጦሩ እዚህ በንጉሡ ፊት የሰልፍ ትርኢት አሳይቶ ነበር። የዕድል ነገር ሆኖ ጦሩን በሰልፍ እየመራሁ በጃንሆይ ፊት ያለፍኩኝ እኔ ነበርኩ። ከዚህ የተነሣነው ግንቦት ወር 1946 ዓ.ም ነበር። ከአዲስ አበባ ጅቡቲ ድረስ በባቡር ሄድን። ከዛም በመርከብ ተሳፍረን ሌትና ቀን ተጉዘን በተነሳን በ48ኛ ቀናችን ቡሰን ከተባለች የኮርያ ወደብ ደረስን። ከዛም በባቡር ተሳፍረን ወደ ጦር ግንባር አመራን።

ከተዘጋጀልን ቦታ እንደ ደረስን ጸሎት አደረግኩኝ፣ ጦሩ በየክፍሉ ተመድቦ ሄደ። እኔም ምድቤ ከጦሩ አዛዥ ኮሎኔል አስፋው ወ/ማርያምና ከምክትል አዛዡ ኮሎኔል ካሣ ጋር ጠቅላይ ጦር ሰፈር ስለ ነበር ወደዛ ቀጠልኩ። ከኛ ጋር አንድ ሐኪምም ነበር። እኔ በቀጥታ ከጦርነቱ መሃከል ባልገባም ቅዳሴና እሑድ በየጦሩ ግንባር እየሄድኩኝ ጦሩን እናዝዛለሁ፣ ትምህርት እሰጣለሁ።

ፈለገ ጥበብ – ስለ ኮርያው ጦርነት ካነሳን አይቀር በጊዜው ስለ ነበረው የጦርነት ሁኔታ በተለይ ደግሞ የኢትዮጵያ ጦር ተሳትፎ ምን ይምስል እንደ ነበር በትንሹ ቢነግሩን?

ጸባቴ አርአያ ሥላሴ – የኛ ጦር በነበረበት ግንባር የአሜሪካ፣ የቱርክ፣ የግሪክ፣ የኮርያ፣ የእንግሊዝ ወዘተ ጦር ነበር። በጀግንነት ግን የኛን የሚወዳደር አልነበረም። የኛ ጦር በተሰለፈበት ግንባር ሁሉ አንዴም አልተሸነፈም። ሌላው የኛ ጦር የጀግንነት ምልክትና ከሌሎች የሚለየው አንድም አባል ወታደር በጠላት ያልተማረከብን መሆኑ ነው። ከነሕይወቱ ቀርቶ ሬሣም አልተማረከብንም። በአንፃሩ በየጊዜው የጠላት ጦርን በብዛት ይማርክ የነበረው የኛ ጦር ነበር።

በተባበሩት መንግሥታት ሥር ከዘመተው ጦር በብዛት በጠላት እጅ የተማረከው የአሜሪካ ወታደር ነበር። በጉዳት ደረጃ ስንወስደው ግን የቱርክ ጦር በጣም ጉዳት ደርሶበታል። ለጦርነት ግድ የሌላቸውና በቀላሉ የሚማረኩት ግን አሜሪካውያን ነበሩ። የታይላንድ ወታደሮችም እንደ አሜሪካውያን ናቸው። በጦርነቱ ፍጻሜ የምርኮኛ ልውውጥ በተደረገ በት ወቅት ከአረካካቢዎቹ አንዱ እኔ ነበርኩኝ። የሬሣ ልውውጥ ሳይቀር ተደርጓል። በዛን ጊዜ ጦርነት ውስጥ ከተሳተፉት ሀገሮች አንድም ምርኮኛ ያልተገኘባት ኢትዮጵያ ብቻ ነበረች። ይብዛም ይነስም ሌሎቹ ተማርከባ ቸዋል።

ፈለገ ጥበብ – ሌላስ በኮርያ ቆይታዎ ወቅት ካጋጠመዎትና እስከ አሁን የማይረሳ ትዝታ የፈጠረብዎት አጋጣሚ ይኖራል?

ጸባቴ አርአያሥላሴ – ብዙ ነው ስንቱ ይነገራል? ብቻ አንድ ሁለቱን ልንገርህ። ከሁሉ የማልረሳው የኢትዮጵያ ወታደሮች አንድ ስትራቴ ጂያዊ ተራራን ከጠላት ያስለቀቁበት አጋጣሚ ነው። አሜሪካውያን፣ ግሪኮች፣ ቱርኮች ብቻ ሁሉም ያንን ተራራ ከጠላት ለማስለቀቅ በየተራ ሞከሩ፣ ግን አልቻሉም። በመጨረሻ ይህ ነገር አልተቻለምና ኢትዮጵ ያውያን ይግቡ ተባለ። ትዝ ይለኛል ሻለቃ ተፈራ ወልደ ትንሣኤ ይባላል። የተወሰነ ጦር ይዞ ወደ ተራራው ገሰገሰ። ከከባድ ፍልሚያ በኋላ ኢትዮጵያውያኑ ተራራውን በቁጥጥር ሥር አዋሉት። የሚገርመው ግን ተራራው ሙሉ በሙሉ በኢትዮ ጵያውያን ቁጥጥር ሥር ሲውል በሕይወት የቀሩት የኢትዮጵያ ወታደሮች ሻለቃውና አንድ ሌላ ወታደር ብቻ ነበሩ። በመትረየስና በቦምብ ጠላትን አጋይተው ነበር የያዙት። እጅግ በጣም ከባድ ውጊያ ነበር፤ ከዛ በኋላም በአካባቢው እንደዚያ አይነት ከባድ ጦርነት አልነበረም።

ሌላው የማልረሳው አጋጣሚ በኳስ ውድድር ወቅት የተከሰተው ነገር ነበር። ጦሩ በዕረፍት ጊዜው ይዝናናል፣ እርስ በራሱም የኳስ ጨዋታ ውድድር ያደርጋል። አንዱ ሀገር ሌላውን ወደሠፈሩ ይጠራል ያኛውም በሌላ ቀን በፈንታው ይጋብዛል፣ በዚህ መልክ የኛ ጦር ከእንግሊዞች፣ ከአሜሪካውያንና ከኮርያውያን ጋር የደርሶ መልስ ጨዋታ አደረገ። አንድ ቀን ግሪኮች የኛን ልጆች ወደ ሠፈራቸው ጠርተው ተጫወቱ። ይሁንና በጨዋታ ሳይሆን በአድልዎ ረታን አሉ። መልሰን እኛ ጋበዝናቸው። ከዘጠኝ ሺህ በላይ የግሪክ ወታደር አብሮ መጣ።

ጨዋታው ተጀመረ። ግሪኮች የትዕቢት ተግባር ጀመሩ። እነርሱ ጥቁሮች ናቸው በማለት ጨዋታውን በመተው የኛን ተጫዋቾች በጥፊ ይማቱ ጀመር፣ በሜዳው ላይ ሦስት ብርጌድ የግሪክ ጦር አለ (4500) የኛ አንድ ሻለቃ ብቻ ነው (1500)። ተጫዋቾቻችን በጥፊ ሲመቱ ያዩ የኛ ወታደሮች ወደሜዳው ገቡ። ግሪካውያንም ግልብጥ ብለው ገቡ። ጨዋታው ቀረና ቅልጥ ያለ ድብድብ ተጀመረ። ደግነቱ ሁሉም ወታደር ትጥቅ አልነበረውም። ስለዚህ በቦክስም በጭንቅላትም፣ በወንበርም ብቻ ባገኙት ሁሉ ይደባደቡ ጀመር። ቅልጥ ያለ ድብድብ ተነሳ። ብዙም ሳይቆይ የኛ ጦር አሸነፈ። በዚህን ጊዜ የተመታውም ያልተመታውም የግሪክ ወታደር ሁሉ መሬት ላይ ተኛ። በኋላ የአሜሪካ የጦር አዛዥ ራሳቸው ነጭ ባንዲራ ይዘው መሃል ሜዳ በመግባት ሁኔታውን ካረገቡ በኋላ ሁለቱንም ወገኖች አስታረቁዋቸው። በመጨረሻ ግሪካውያኑ ወደ ሆስፒታል የኛ ጦር ደግሞ ወደ ሰፈሩ ጉዞአቸውን ቀጠሉ። የዛን ቀን ሁኔታ አይረሳኝም ሌሎችም አሉ ግን ታሪኩ ብዙ ስለሆነ ለአሁኑ ይበቃል።

ፈለገ ጥበብ – ግዳጃችሁን ፈጽማችሁ ከኮርያ ስትመለሱ በአዲስ አበባ የተደረገላችሁ አቀባበል ምን ይመስል ነበር? እርስዎስ በምን ሥራ ተመደቡ?

ጸባቴ አርአያ ሥላሴ – ወደ ሀገራችን ስንመለስ ከፍተኛ አቀባበል ነበር የተደረገልን። ሚኒስትሮች፣ ጀኔራሎች፣ ሌሎችም ከፍተኛ ባለሥልጣናት የክብር አቀባበል ካደረጉልን በኋላ ወደ ጃንሆይ ቀርበን ሽልማትም ተቀበልን። በበኩሌ፣

1. የወርቅ ሜዳይ ከነ ምስክር ወረቀቱ
2. የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የብር ሜዳይ ከነ ምስክር ወረቀቱ
3. የተባበሩት መንግሥታት ሜዳይ ከነ ምስክር ወረቀቱ
4. የኮርያ የጦር ሜዳይ ከነ ምስክር ወረቀቱ
5. በአንገት የሚጠለቅ የወርቅ መስቀል ተሸልሜአለሁ።

ከኮርያ ከተመለስን ከጥቂት ቀናት በኋላ ጃንሆይ አስጠሩኝና «ከአሁን በኋላ ወደ ቤተ ክህነት አትመለስም፣ ጦሩን እያስተማርክ በየሆስፒታሎች የሚተኙትን ሕሙማን እየጠየቅክ ከጦሩ ጋር ትሆናለህ» አሉኝ። በዚህ መሠረትም ጉዳዩ ለጄኔራል መንግሥቱ ተነግሮ ደመወዜ በሚገባ ተስተካክሎ በሻምበልነት ማዕረግ በ4ኛ መምሪያ ሥራዬን እስከ 1953 ዓ.ም ቀጠልኩ። ወደ ኮርያ ስዘምት በመቶ አለቅነት መዓረግ ነበር የሄድኩት።

ፈለገ ጥበብ – ጦሩን መንፈሳዊ ትምህርት ከማስተማር ሌላ ተጨማሪ ሥራ ነበርዎት?

ጸባቴ አርአያ ሥላሴ – እኔ አልፈለግኩም ነበር። ነገር ግን ጃንሆይ ራሳቸው አስጠርተው ገንዘብ እየጠፋ (እየባከነ) ስለተቸገርን አንተው አንቀሳቅሰው ብለው ከነበረኝ መንፈሳዊ ኃላፊነት በተጨማሪ ገንዘብ እንዳንቀሳቅስ አደረጉ። ሥራው ቀላል አልነበረም በቀን ከአንድሚሊዮን ብር በላይ ይወጣ ይገባ ነበር።

ፈለገ ጥበብ – የገንዘብ ነገር ከተነሳ ስለ «አባ ሐና» ትንሽ ቢያጫውቱን። እስከ አሁን ድረስ አንድ ሰው ገንዘብ ቋጣሪ ከሆነ አባ ሐና ነው የሚባለው። በእርግጥ አባ ሐና የዚያን ያህል ገንዘብ አፍቃሪ ነበሩ?

www.ethiopianorthodox.org

ጸባቴ አርአያ ሥላሴ – አባ ሐና ፈዶ ነበር የሚባሉት፣ እኔ በቅርብ አውቃቸዋለሁ ሰውየው ደግ ነበሩ። በዛው ላይ መናኝ ናቸው። በቅቤ የተሠራ ወጥ፣ ሥጋ አፋቸው ውስጥ አይገባም። ምግባቸው ሽሮ፣ ጐመን ነበር። ገንዘብን በተመለከተ ግን በዓይኔ ያየሁት የለም እርግጥ በወሬ ጃንሆይ ገንዘብ ይስጡ ብለው ሲያዙዋቸው ቀንሰው ይሰጣሉ ይባላል፣ በወሬ ደረጃ ነው።

ፈለገ ጥበብ – ጦሩ ጋር እስከ 1953 ዓ.ም ድረስ እንደቆዩ ተናግረዋል። ከዛ በኋላ የት ሄዱ?

ጸባቴ አርአያ ሥላሴ – በ1953 የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ተደረገ። ከዛ በኋላ ሁኔታዎች ተቀያየሩ። እኔም የጀኔራል መንግሥቱ ታማኝ ነው በሚል ምክንያት በቅጣት መልክ እንድዛወር ተደረግሁ።

ፈለገ ጥበብ – መፈንቅለ መንግሥቱ ሲፈጸም ከመጀመሪያ እስከ ፍጻሜ በቦታው የነበሩ እንደ መሆንዎ መጠን ስለሁኔታው አጠር አድርገው ሊገልጹልን ይችላሉ?

ጸባቴ አርአያ ሥላሴ – ውስጥ ለውስጥ ዝግጅቱ ከተጀመረ ትንሽ የቆየ ይመስለኛል። በክብር ዘበኛ ግቢ ሬድዮ ጣቢያ ተቋቁሞ ነበር። ክቡር ዘበኛ በዚህ ሬድዮ ጣቢያ አማካኝነት ግልጽ ያልሆነ የዓመጽ መልእክት ያስተላልፍበት ነበር ይባላል። በፊትም ቢሆን እነ አቶ መኮንን ሀብተ ወልድ የሬድዮ ጣቢያ መቋቋሙን ተቃውመውት ነበር፤ የማሳመጽያ መሣሪያ ነው በሚል። በሌላ በኩል መፈንቅለ መንግሥቱ ከመከናወኑ በፊት መኮንኖች በአንድ ክፍል ሆነው ለብቻቸው ይሰባሰቡ ነበር፣ እኛ ስንገባ (ስንመጣባቸው) ይበታተናሉ። ይህ ሲሆን በተደጋጋሚ አስተውል ነበር። በዚህ በኩል የጠረጠራቸው ግን አልነበረም።

ሁኔታውን ለማሳጠር መፈንቅለ መንግሥት በተካሄደበት ዕለት ሚኒስትሮች፣ አልጋ ወራሽ እነ ራስ ስዩም ሁሉ አንድ ቤት ታጐሩ። እኔ ቤቴ ነበርኩኝ፣ ጠቅላላ ግምጃ ቤቱ በኔ ሥር ስለነበር ኮሎኔል ጌታቸው የበላዩ ነበሩ፣ ቤት መጥተው የመኪና ጡሩምባ አሰሙ። ስወጣ ይፈለጋሉ ቶሎ ብለው ለብሰው ይምጡ አሉኝ። ለባብሸ ስወጣ እርሳቸውም የጦር ልብሳቸውን ለብሰዋል «ምነው ሀገር ሰላም አይደለም?» ስላቸው «ዝም ብለው ይግቡ አባ» አሉና በመኪና ይዘውኝ ሄዱ። ክብር ዘበኛ ግቢ ስንደርስ ሜዳው ሁሉ በጦር መኪና ተሞልቷል። ጀኔራል መንግሥቱ ንዋይ ከአባ ሐና ጋር ሜዳው ላይ እየተጫወቱ ቆመዋል። ቀረብ ብየ እጅ ስነሳ ጀኔራል መንግሥቱ መስቀል ያሳልሙኝ አሉኝና አሳለምኩዋቸው። በኋላ በሉ ቢሮዎ ቁጭ ብለው ይጠብቁ አሉኝና ቢሮየ ሄጄ ቁጭ አልኩኝ። ሁላችንም ተጨነቅን ምንድነው ነገሩ ስንል አንዳንድ መኮንኖች ጦር ሠራዊቱ ስላመጸ ቤተ መንግሥቱ እንዳይያዝ ብለን ነው ይሉናል። ከትንሽ ጊዜ በኋላ ሁለት ወታደሮች መጥተው በሬ ላይ ቆሙ። ሌላ ሰው እንዳይገባ እንዳይወጣ ተደረገ። ስንቅ ወጪ እያደረግን በመስጠት ላይ እንዳለን ተኩስ ተጀመረ። ከኔ ጋር የነበሩ ሁለት ወታደሮች ተመተው ወደቁ። እኔ ወደኋላየ ሸሸት ብዩ ቁጭ አልኩኝ። ወታደሩ ለምን እንደሚዋጋ አላወቀም ነበር። በፊት የተነገረው ጦር ሠራዊቱ በንጉሡ ላይ አምጿል የሚል ነበር በኋላ ግን ነገሩ ሲሰማ እንዴት እኛ ጃንሆይን እንከዳለን እያለ እየተወ መሄድ ጀመረ፣ ሸሸ፣ በእርግጥ የተዋጋም ተዋጋ የተያዘም ተያዘ ጦር ሠራዊት አሸንፎ ገባ ቀኑ ሐሙስ ይመስለኛል እነ ተፈሪ ወልደ ትንሳኤ ቤታቸው ቁጭ እንዳሉ ተያዙ።

ጦርነቱ ሳያበቃ ጀኔራል መንግሥቱ አስጠሩኝና እጅነስቸ ገባሁ፣ ከዛ በቁጣ «እናንተ ገንዘቡን አሸጋችሁ ጦሩ እንዲፈታ አደረጋችሁት አይደል? ቆይ...ቆይ...ከአለቃ ጋር አብራችሁ እንድትመጡ አሉና አዘዙ። ሻለቃ ዮሐንስ ይባላሉ ቶሎ ይዘሃቸው ና አሉዋቸው። ኮነሬል ጌታቸው ሸሽተው ተደብቀዋል። እኔም ሻለቃ ዮሐንስ እንሂድ ስላቸው ሞኝ ሊረሸኑ እኮ ነው ይልቅስ ቤትዎ ላድርስዎ ብለው ቤቴ አደረሱኝ፣ በዚህም ሕይወቴ ተረፈ። ቤቴ ገብቼ ቁጭ እንዳልኩ ቤቴ በወታደር ተከበበ፣ ምንድነው ጉዱ ስላቸው አንተ የመንግሥቱ ንስሐ አባት ነህ አሉኝና አሠሩኝ። እቃየን በሙሉ አንድ ሳያስቀሩ ዘረፉት፣ ማታ ስለቀቅ ቤቴ ባዶውን አገኘሁት።

ቅዳሜ ጃንሆይ እንደ መጡ አስጠሩኝ። መኮንኖች ሁሉ ታስረው ታስረው ተኮልኩለዋል። እጅ ነሳሁ ጃንሆይን ሳያቸው አለቀስኩኝ፣ ምን ሆነህ ነው አለኝ «ገፈፉኝ፣ ዘረፉኝ፣ ራቁቴን ነኝ» አልኩዋቸው። አዘኑ፣ ግምጃ ቤቱን ጠርተው 1500 ብር ስጠውና ልብሱን ይልበስ ብለው አዘዙ። በኋላ ግን ሰዎች እሱኮ የመንግሥቱ አድራጊ ፈጣሪ ነው እያሉ ሲያስቸግሩዋቸው ለጊዜው ከሥራ ታገድሁ። ከትንሽ ጊዜ በኋላ እንደ ገና ወደ ቤተ መንግሥት ተጠርቼ ሄድኩኝ። በዚህ ጊዜ ጃንሆይ ቤተሠሪ የሚባል ጡረታ ቤት ደብረ ሊባኖስ አለ ወደዛ እንድትሄድ አሉኝ ተነስቼ ሄድኩኝ። እነ ጀኔራል መንግሥቱም ጦር ፍርድ ቤት ቀረቡ ተከለ ሃይማኖት አደባባይ ተሰቀሉ። እኔ ግን ሲሰቀሉ በዓይኔ አላይም ብዩ አልሄድኩም።

ፈለገ ጥበብ – ለመሆኑ ጀኔራል መንግሥቱ ንዋይ ምን ዓይነት ሰው ነበሩ? ወንድማቸው ገርማሜንስ ያውቁዋቸዋል?

ጸባቴ አርአያ ሥላሴ – ጀኔራል መንግሥቱ በጣም ርኅሩህ፣ ደግና ጀግና፣ ቁመናቸው የሰጠ፣ መልካቸው ያማረ ሰው ነበሩ። ሲበዛ ርኅሩህ ነበሩ። ሀገራቸውን ይወዳሉ፣ ወታደሩን ያፈቅራሉ፤ አንድ ቀን በዓይኔ ያጋጠመኝን ልንገርህ። አንድ ወታደር ከነሚስቱ መጣ ሚስቱ ልጅ አዝላለች እንደገና ታቅፋለች፣ ባልም ልጅ ታቅፏል። ጧት ቢሮ ሲገቡ ጀኔራል ያዩዋቸዋል። ራሳቸው ወደነርሱ ሄደው ምን ሆናችኋል አሉዋቸው። ወታደሩም «ይኸው ልጆቻችን የምናበላቸው ጠፋ ተቸ,ገን ነው የመጣነው አላቸው» በዛን ጊዜ የአምስት መቶ ብር አንድ ኖት ነበር። እጃቸውን ኪሳቸው ውስጥ ከተው አንድ ባለ አምስት መቶ ብር ኖት ሰጡት። ወታደሩም እኔ ቋሚ የሆነ ነገር ነው የምፈልገው ሲላቸው ስሙን ጻፉና እርሱ ኋላ ይፈጸምልሃል አሁን ለልጆችህ ይህችን ይዘህ ሂድ አሉትና እልል እያለ ሄደ።

ጦሩም ቢሆን በጀኔራል መንግሥቱ ላይ የነበረው ፍቅር በጣም ከፍተኛ ነበር። ከፍቅሩ የተነሳ ያለቅሳል። እንደኔ ጀኔራል መንግሥቱ ከልባቸው በጃንሆይ ላይ ያመጹ አይመስለኝም፣ ወንድማቸው ገርማሜ ያሳሳታቸው ይመስለኛል። ገርማሜ ጋርም ቢሆን እንተዋወቃለን። ጨካኝ ነበር። በተለያዩ ቦታዎች በአውራጃ ገዥነት ሠርቷል። ገዥ ሆኖ በተሾመበት ቦታ አንድ ባላባት በበቅሎ ተቀምጦ ሲሄድ ካየ በቅሎውን አስቁሞ ባላባቱን ያስወርድና አሽከሩን በቅሎዋ ላይ አስወጥቶ ባላባቱን ጠመንጃ አሸክሞ በል ተከተል ይለው ነበር። በመፈንቅለ መንግሥቱ ወቅት ጠመንጃ ይዞ ያዋጋ ነበር፣ የጦር ልብስ ግን አልለበሰም ነበር።

ፈለገ ጥበብ – አሁን ደግሞ ወደ ደብረ ሊባኖስ ልመልስዎ ደብረ ሊባኖስ ሥራ የጀመሩት እንዴት ነበር?

ጸባቴ አርአያ ሥላሴ – ወደ ደብረ ሊባኖስ የሄድኩት በቅጣት መልክ ነው። ከዛ በፊት ደመወዜ ብር 200 (ሁለት መቶ ብር) ነበር። በ1954 ዓ.ም ወደ ደብረ ሊባኖስ ስመደብ ግን ደመወዜ 75 ብር ብቻ ነበር። እኔ ወደ ቦታው ስሄድ ሥፍራው ባዶ በረሃ ነበር። ሙዝ፣ ብርቱካን ወይን የመሳሰሉት አትክልቶችን በመትከልና በማስተከል ለመጀመሪያ ጊዜ ልማት ያለማሁት እኔ ነበርኩኝ። እዛ በሄድኩ በዓመቱ አዲሱ ቤተ ክርስቲያን ተሠርቶ አልቆ ስለ ነበር ኅዳር 9 ቀን 1965 ዓ.ም ጃንሆይ ሊመርቁ መጡ። ሁሉም እየሄደ እጅ ሲነሳ እኔ ብቻ አልሄድም ብየ ቀረሁ። ጥሩት አሉና ስመጣ «አኩርፈሽ ነው?» አሉኝ። ከዛ እኔም ሁለት መቶ ጦር ይገፍ በሰልፍ ተቀበልኩዋቸው።

ገዳሙን እየተዘዋወሩ አትክልቱን ሲያዩ በጣም ገረማቸው። መኝታ የንም አሳየሁዋቸው፣ የምተኛው መሬት ላይ ነበር የእመቤታችን ቤተ ክርስቲያንም አሠርቻለሁ። በጣም ደስ አላቸው። ወደ ክብር ዘበኛ ተመለስ አሉኝ፤ እኔ ግን ከአሁን በኋላ ገዳም ውስጥ ለመቀመጥ ነው የምፈልገው አልኩዋቸው። በወር 335 ብር ተፈቀደልኝና የሴቶች ገዳም፣ ቤተሳሊሆም ጡረታ ቤት፣ ጫጋል ቀራንዮ መድኃኔ ዓለም ገዳም፣ አጣምሬ እንዳስተዳድር መኳአከ ሰላም አርአያ ሥላሴ ተብዩ ተሾምኩኝ። በሌላ ጊዜ ደሞ ጃንሆይ ገዳሙ እጅግ መልማቱን አትክልት በስፋት መተከሉን፣ የመነኮሳት ኑሮና ሥርዓት መሻሻሉን ሰምተው ካዩ በኋላ ደብረ ሊባኖስ ገዳም ጭምር ደርበህ አስተዳድር አለኝ። እስከ 1978 ዓ.ም ድረስ ጸባቴ አርአያ ሥላሴ ተብየም እነዚህን ገዳማት በአንድነት አስተዳድሬአለሁ።

ፈለገ ጥበብ – ጸባቴ ኃይለኛ ናቸው ይባላል፣ በዚህ በኩል ያለዎት አስተያየት ምንድነው?

ጸባቴ አርአያ ሥላሴ – ኃይለኛ አይደለሁም፣ ሰነፍ ሠራተኛ፣ ዳተኛ ሰው ግን አልወድም፤ የኔ መመርያ ሥራ ብላ ነው። ታድያ እኔ ሰውን ሳሠራ ራሴ ጭምር እየሠራሁ ነው። እኔ የማልሠራውን ሥራ ሌላ ሥራ እንዲሠራ አላደርግም። ደብረ ሊባኖስ ስሄድ መነኮሳት ሁሉ እግርና እጃቸው አጣጥፈው ነበር የሚውሉት፤ እኔ ከሄድኩ በኋላ ግን መሥራት የሚችሉ በተለይ ወጣት መነኮሳት እንዲሠሩ አደረግኩኝ። በመስኖ የተለያዩ አትክልቶችን ማልማት ጀመርን። ፊት መነኮሳት የባሕርዛፍ ቅጠል አንጥፈው ነበር የሚተኙት። በኋላ ግን ሁላችንም ባደረግነው ጥረት ቤት ሠራን፣ የጥጥ ፍራሽ ተገዛ፣ ሌላው ቀርቶ ምግቡም ቢሆን በሥርዓትና በሚገባ መመገብና መዘጋጀት የተጀመረው እኔ ከሄድኩ በኋላ ነበር።

በሌላ በኩል እኔ ወደ ደብረ ሊባኖስ ከመሄዴ በፊት መነኮሳት እንደፈለግኩት ወደከተማ ይሄዱ ነበር። እኔ ግን በየከተማው እየሄዱ መዞር፣ መጠጥ ቤት መግባት ከአንድ መናኝ መነኩሴ ጋር የሚሄድ ጠባይ ባለመሆኑ ከለከልኩ። እንደዛ የሚያደርግ ቢገኝ እንደ ጥፋቱ መጠን ይቀጣል፣ ከገዳሙም ይታገዳል። በዚህ በኩል ቀልድ አላውቅም። በዚህ በዚህ ምክንያት ነው ኃይለኛ የሚሉኝ። ከዚህ ውጭ ባሳለፍኳቸው 52 የሥራ ዓመታት ምስጋናና ሽልማት ካልሆነ በስተቀር በሥራዩ ቅጣትም ሆነ ተግሣጽ ደርሶብኝ አያውቅም።

ፈለገ ጥበብ – አልታዘዝም እምቢ ለሚልዎት ሰውስ ምንድነው የሚያደርጉት?

ጸባቴ አርአያ ሥላሴ – አልታዘዝም የሚል አጋጥሞኝ አያውቅም። ቅድም እንዳልኩት በመጀመሪያ ደረጃ ሰውን የማዘው ራሴ ጭምር እየሠራሁ ነው፤ በሁለተኛ ደረጃ ሁሉም ሰው ሰነፍ እንደማልወድ ያውቃል። ይሁንና በጉልበቴ የተጠቀምኩበት አጋጣሚ ትዝ የሚለኝ አንድ ነገር አለ። አንድ ሰው ነበር፣ ፀረ ማርያም የሆነ። እዛ ክቡር ዘበኛ እያለሁ ነው፣ ሰውየው ለስሙ መነኩሴ ነው። ስሙ አባ ሃብተ ማርያም እንደዛ ይመስለኛል። ይቀድሳል እመቤታችንን ግን ይጠላል። ለኔ ደግሞ እመቤታችንን ከሚጠላ የበለጠ ጠላት የለኝም፤ በእመቤታችን ቀልድ አላውቅም። ታድያ ይህን ሰው መነኩሴ ሰው ሁሉ ያማዋል፣ ይጠላዋል።

ከእለታት አንድ ቀን ሁለታችን አንድ ጉድጓዳ መንገድ ላይ ለብቻችን ተገናኘን። መጥቶ ሰላም አለኝ እኔም ሰላም አልኩት። በኋላ አባ እየቀደስክ ማርያም አታማልድም ትላለህ አሉ ምንድነው ነገሩ? አልኩት እርሱም መልሶ «አዎ አሁንም አታማልድም» አለኝ፤ በቃ ከዛ በኋላ ራሴን አላውቅም፤ ቀስ ብየ መጠየቅና ማሳመን ሲገባኝ ተነሣሁና በጥፊ ስለው ወደቀ። እንደ ወደቀ ረግጬ ረግጬ ጥየው ሄድኩኝ። በማግስቱ ጀኔራል መንግሥቱ ዘንድ ከሰሰኝ።

«ይኸው እንደዚህ ዓይነት የእርስዎ መነኩሴ ደበደበኝ» አላቸው፤ እርሳቸውም በፍጹም እርሳቸው አይደባደቡም ውሸት ነው አሉ። እርሱም ይጠሩና ይጠየቁልኝ አይዋሹም ሲላቸው አስጠሩኝና «አባቴ ይህ መነኩሴ ደበደቡኝ ብሎ ከሰዎታል» አሉኝ፤ «እኔም አዎን ደብድቤዋለሁ» አልኩዋቸው። ጀኔራል መንግሥቱም መልሰው «ምን አድርጎ ነው?» ሲሉኝ «ፀረ ማርያም ነው እመቤታችንን ያንቋሽሻል፣ ይሰድባል...» ብዩ ንግግሩን ከመጨረሴ «ይኼ መነኩሴ? ቆብ አድርጎ?» ብለው በጥፊ ሲሉት ተንደባለለ። እዛ እያለ በጡጫ በእርግጫ ቢሉት ሰዎች መጥተው ገላገሉት፣ እኔም መልሸ ገላጋይ ሆንኩኝ እርሱም ከዛ ሮጦ እንደ ወጣ ቀረ፤ ከዛን ቀን ጀምሮ የቤተ ክርስቲያን ደጅ ረግጦ አያውቅም። ውጭም ቢሆን እኔን ከሩቅ ሲያየኝ ይሮጣል ይደበቃል። ጀኔራል መንግሥቱ ሃይማኖታቸውን አክባሪ በተለይ ደግሞ እመቤታችንን እጅግ ያፈቅሩ ነበር።

ፈለገ ጥበብ – ከደብረ ሊባኖስ ገዳም በኋላ የትሠሩ?

ጸባቴ አርአያ ሥላሴ – በበኩሌ ከገዳም የመውጣት ምኞትም

www.ethiopianorthodox.org

ፍላጎትም አልነበረኝም። ነገር ግን በብዙ ልመና በተለይ ቦታውን መልክ ታስይዝልናለህ በሚል ጌተሰማኒ ገዳም ለአራት ዓመት ተኩል ያህል ሠርቻለሁ። እዛም ገዳሙን ከማሳጠር ጀምሮ የተለያዩ የልማት ሥራዎችን አከናውኛለሁ። አሁን ደግሞ እዚሁ ጠቅላይ ቤተ ክህነት የተከሊልና ጋብቻ መምሪያ ኃላፊ ሁኜ በመሥራት ላይ ነኝ።

ፈለገ ጥበብ — በወጣትነቴ ጊዜዬ ሳልሠራው ቀረሁ ብለው የሚቆጩበት ነገር ይኖራል?

ጸባቴ አርአያ ሥላሴ — የፍላጐቴ የምኞቴ ያህል ብዙ ባለመማሬ ይሰማኛል። ብዙ ብማር የበለጠ ቤተ ክርስቲያኔን አገለግል ነበር እላለሁ፤ በተረፈ ከሕፃንነቴ ጀምሮ እድሜን በሙሉ ያሳለፍኩት ቤተ ክርስቲያኔን በማገልገል ላይ ስለሆነ ደስተኛ ነኝ።

ፈለገ ጥበብ — ለአሁኑ ወጣት ትውልድ የሚያስተላልፉት መልእክት ምንድነው?

ጸባቴ አርአያ ሥላሴ — ወጣቱ ከሁሉ አስቀድሞ መልካም ሥነ ምግባር ሊኖረው ይገባል። አባትና እናቱን ታላላቅ እህቶቹንና ወንድሞቹን ማክበር መታዘዝ አለበት። የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው። እግዚአብሔርን መፍራት ማለት ደግሞ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መፈጸም ማለት ነው። ወላጆችም ቢሆኑ ልጆቻቸውን በሚገባ ማስተማር አለባቸው። ልጆች ሥነ ሥርዓትን፤ ጨዋነትን፤ ከወላጆቻቸው፤ ከቤታቸው፤ ካለተማሩ ከሌላ ሊያገኙት አይችሉም። ወጣቶች የሀገር ተረካቢዎች፤ የኛ ተተኪዎች ናቸው። ለዚህ የምናበቃቸው ደግሞ እኛ ወላጆች ነን። በዚህ በኩል ቤተ ክርስቲያናችን ትልቅ አስተዋጽኦ ማበርከት ያለባት የምስለኛል። ኋላፊነትም አለባት። ወጣቱ በበኩሉ ራሱን ለትምህርት ዝግጁ በማድረግ ከአጓጉል ልማዶች መራቅ አለበት። ከሁሉ በፊት ራሱን ከመጥፎ ነገሮች ሊጠብቅ የገባል። ምክንያቱም ሀገሩንም ሆነ ቤተ ክርስቲያኑን ሊጠብቅ የሚችለው በቅድሚያ ራሱን መጠበቅ ሲችል ነውና።

# የሥነ ልቡና አገልግሎት ለወጣቶች

## «የአሸናፊነት ምስጢር»

የማነ ገ/ማርያም /ዶ/ር

ሰዎችን እንደ ተፈጥሮአዊ ጠባያቸውና ዝንባሌአቸው መሠረት ከ4 ቦታ ልንመድባቸው እንደምንችል የየሀገሩ የሥነ አእምሮ ወይም የሥነ ልቡና ጠበብት ያረጋግጡልናል።

### 1ኛ. የልጅነት ዕድሜ

የሕፃንነት ወይም የጨቅላነት ዕድሜን ትተን ሰው ነፍስ ከሚያውቅበት ጊዜ አንስቶ ያሉትን ዓመታት ከቆጠርን በሰው የሕይወት ዘመን የመጀመሪያው ዕድሜ የልጅነት ዕድሜ ነው። በዚህ ዕድሜ የሚገኘው ሰው 1ኛ. ደስተኛ ነው፤ ሳቂታ ነው። 2ኛ. ስለ ወደፊት ኑሮው ምንም ሐሳብ፤ ምንም ጭንቀት የለውም። 3ኛ. ግልጽ ነው፤ የዋሕ ነው። ምንም ነገር አይደብቅም፤ የመጣለትን ይናገራል፤ እንደ መጣለትም ያደርጋል። ሰዎች ምን ይሉኛል የሚል ይሉኝታ የለውም። ስለዚህም እንደ አዋቂዎች ማስመሰል አያውቅም። 4ኛ. ራሱን ለማናቸውም በጎም ይሁን ክፉ ተጽእና የመስጠት፤ እንደ አካባቢው ሁኔታ የመሆን ጠባይ አለው፤ እንዳደረጉት ይሆናል። ይህ በመሆኑም ምክንያት በሁሉም ሀገር «ልጅነት የፈለጉትን ነገር ቢጽፉበት የሚቀበል ሠሌዳ ነው» ይባላል።

በዚህ ዕድሜ የሚታዩት ድክመቶች ዋነኞቹ የሚከተሉት ናቸው 1ኛ. ነገሮችን ጠለቅ ብሉ የማገናዘብና የመገምገም ችሎታ የለውም፤ ሐሳቡ ተንሳፋፊ ነው 2ኛ. በጥፋቱ ተቀጥቶና ተመክሮ ወዲያው መልሶ ከዚያው ጥፋት ላይ ይወድቃል 3ኛ. በትንሽ ነገር ይታለላል 4ኛ. ከቁም ነገር ይልቅ ጨዋታና ቀልድ ይወድዳል።

### 2ኛ. የወጣትነት ዕድሜ

ወጣትነት ከልጅነት በኋላ ከጉልማስነት በፊት ያለ የዕድሜ ክልል ነው። በዚህ ዕድሜ የሚገኝ ሰው አእምሮውም አካሉም ትኩስ ነው። ትኩስ በመሆኑም ምክንያት ብዙ ሊሠራ ይችላል። ወጣት ብዙውን ጊዜ ያለበትን ተጨባጩን ዓለም ትቶ በሐሳቡ በሚፈጥረው ዓለም ውስጥ ገብቶ በዚያ ውስጥ ይኖኛል። በዚህ ዕድሜ የሚገኝ ሰው ያሉት ድክመቶች የሚከተሉት ናቸው። 1ኛ. ቶሎ ይበሳጫል 2ኛ. ሁሉም ነገር በትክክል እንዲሠራ፤ ፍትህ እንዲኖር፤ ሰው ሁሉ እንደ ዕድሜውና እንደ ኃላፊነት ቦታው መሠረት ጨዋ፤ ቁም ነገረኛ ሐቀኛ እንዲሆን ይሻል። ጥፋት አይቶ በአስተያየት የማሳለፍ ጠባይ የለውም። እንዴት እንደዚያ ይሆናል ብሉ ቱግ ማለትና አጥፊውን ከፊቱ ላይ መናገር፤ ለነገ ያለማለት ሁኔታ ይታይበታል። 3ኛ. ጉልበት ስላለው ለደረሰበት ጥቃት አጸፋታውን ለመመለስ ወደ ኋላ አይልም። 4ኛ. አደገኛ የሆነን ነገር እንኳ ምንም አያደርገኝም በማለት የመዳፈርና ራሱን አሳስፈላጊ ለሆነ አደጋ የማጋለጥ ሁኔታ ይታይበታል። 5ኛ. ያሰበው ሳይሳካለት ሲቀር ቶሎ ያዝናል፤ ቶሉም ተስፋ ይቆርጣል 6ኛ. ያሰበው ሲሳካለትም በችሎታውና በዘዴው እጅግ የመኩራራትና የመደሰት መንፈስ ይታይበታል። ድል ሲያገኝ ጉረኛ ይሆናል። እርሱን የሚያቅተው ምንም ነገር እንደ ሌለ ስለሚያስብም ትንሽ ኩራት አለበት።

### 3ኛ. መካከለኛ ዕድሜ

ዛሬ ወጣቶች የሆናችሁ ሁሉ ቀጥላችሁ የምትገቡበት ዕድሜ መካከለኛ ዕድሜ ይባላል። መካከለኛ ዕድሜ (የጉልማስነት ወቅት) የሚባልበትም ምክንያት በወጣትነትና በሽምግልና ዕድሜ መካከል ያለ ዕድሜ በመሆኑ ነው። በዚህ ዕድሜ የሚገኝ ሰው ምራቁን ውጧል ይባላል። ረጋ ያለ ሰው ነው። ይሁንና የወጣትነት ዕድሜ ጠባይ እስከተወሰነ ጊዜ ድረስ ወዲያው ሙሉ በሙሉ ለቅቆት ስለማይሄድ እንደ እርሱ ልክ ባይሆንም እንኳ አንዳንድ ጊዜ ችኩል የሚልበት ጊዜ ያጋጥማል። በአመዛኙ ግን የረጋ ሰው ነው። ምራቁን ውጧል የሚባለውም በዚሁ ምክንያት ነው። ችግር ይችላል። ከፊቱ አደጋ ሲያጋጥመውም የሚቋቋምበት ድፍረት አለው። ይህም ዕድሜ እንደ ቀሩት ሁሉ የራሱ ድክመቶች አሉት። ጥቂቶቹን ለመጥቀስ 1ኛ. በዚህ ዕድሜ የሚገኝ ሰው በሐሳቡ ግትር ነው። የተሳሳተ ሐሳብም ይዞ ትክክለኛ ነኝ በማለት በሐሳብ የመጽናት ጠባይ ያሳያል። ስለሆነም ሐሳቡን ማስቀየር በጣም ያዳግታል። እንዲሁም ሥልጣን ይወድዳል፤ ሀብትም ጥምር። እኔ የምለው መሆን አለበት ባይ ነው። የሚለው ካለሆነም ይበሳጫል፤ ለቅጣትም ይነሣል። 2ኛ. በዚህ ዕድሜ የሚገኝ ሰው የቅንዓትና የበቀልም ስሜት ይጠነክርበታል።

### 4ኛ. የሽምግልና ዕድሜ

1ኛ. ሽማግሌ የረጋ ሰው ነው። ከብዙም ነገር የተቆጠበ ነው 2ኛ. ሽማግሌ ስሜቱም ቀዝቃዛ ነው 3ኛ. እንደ ፈለገው ለመሆን ከዕድሜውም አንጻር ስለሚያፍር ሁሉንም ነገር አምኖበትም እንኳ ባይሆን በይሉኝታ ከማድረግ እጁን ሰብሰብ ያደርጋል። እንደዚያ ማድረግ እንደማያምርበት ያውቃልና።

ሽማግሌ የረጋ ሰው ነው ስንል ግን በአስተዳዳጉና በአካባቢው ምክንያት የሽማግሌነት ጠባይ የማያሳይ «ቅሌታምና



ባለጌ» የሆነ አንዳንድ ሽማግሌም መኖሩን ሳይዘነጋ ነው። ነገር ግን የእንዲህ ዓይነቱ የአንዳንድ ሽማግሌ ጠባይ ሽማግሌዎችን በሙሉ እንደዚያ ናቸው አያሰኛቸውም። እንዲህ ያሉትን አንዳንድ የሽማግሌ ቀላሉችን ከሐሳባችን ውጭ ካደረግን ሽማግሌ የሆነ ሰው በአመዛኙ የረጋ ሰው ነው፤ ጭምት ነው፤ ቁም ነገረኛም ነው። ራሱ በሌላው ሰው ላይ የኃይል ሥራ ልፈጽም በማለት አምባገር የመክፈት ፍላጎት የሌለው ከመሆኑም በላይ ገፍቶ የመጣበትን የኃይል ሥራና አምባገር እንኳ በኃይል የመጋተርና የመቋቋም ወኔ የለውም፤ ይፈራል፤ ምክንያቱም ያን ሳድርግ ቢልም እንኳ አቅሙ እንደሌለው ያውቃልና።

ስለ ተለያዩ የሰው ዕድሜዎች መለያ ጠባዮች እንደ መግቢያ ይህን ካልሁ በኋላ ወደ ተነሳሁበት ቁም ነገር ልሻገር። «የሥነ ልቡና አገልግሎት ለወጣቶች» በሚል ርዕስ ስር ለአሁኑ መልካም ሥነ ልቡና ለወጣቶች ምን አገልግሎት እንዳለው፤ ለምን እንደሚጠቅማቸው እንዴት እንደሚጠቅማቸው በሚሉ ጽንሰ ሐሳቦች ለማተኮር እፈልጋለሁ።

ስለ ሥነ ልቡና ስንናገር ስለማናቸውም ዓይነት ሥነ ልቡና ሳይሆን አዎንታዊ ስለሆነ፤ ገንቢ ስለሆነን ሥነ ልቡና መሆኑን አንባቢያን ልብ እንድትሉልኝ እፈልጋለሁ። ስለ እንዲህ ዓይነቱ የሥነ ልቡና ጥቅም ስናገር ብዙ ሰው «ሞራል» እያለ በሚጠቀምበት ቃል ትርጉም ነው። ለማናቸውም ሥራ ሞራል ያስፈልጋል ስንል ለሥራው ድፍረት ያስፈልጋል ማለታችን ነው። ሞራል አለን ስንል ሥራውን በአሸናፊነት እንወጣዋለን ማለታችን ነው። ሞራል ራስን የመተማመን መንፈስ ነው። ማናቸውንም ሥራ በሞራል መጀመርና ሥራው እስኪፈጸምም ድረስ በሞራል መቀጠል አስፈላጊ የሆነ ሥነ ልቡናዊ ትጥቅ ነው። ያለዚህ ዓይነቱ፤ መንፈስ ያለዚህ ዓይነቱ ሥነ ልቡና ሊፈጽሙት የሚችሉት አንዳችም ታላቅ ሥራ አይኖርም። ማናቸውንም ሥራ በድል አድራጊነት ለመወጣት የአሸናፊነት ሥነ ልቡና ያስፈልጋል። በዚህ የአሸናፊነት ሥነ ልቡና በመታገዝ የሚንቀሳቀስ ሰው አንዳችም ነገር አይበግረውም። በአሸናፊነት ሥነ ልቡና በመታገዝ የሚንቀሳቀስ ሰው ማናቸውንም ሥራ የፈለገውን ያህል አስቸጋሪ ቢሆን በድል አድራጊነት ይወጣዋል። ሰዎች በሥራቸው የሚፍረከረኩት በሥነ ልቡናቸው ሲፍረከረኩ ነው። ለሥራቸው መፍረክረክ የሚያበቃቸው የሥነ ልቡናቸው መፍረክረክ ነው።

አንድን ሯጭ እንደ ምሳሌ አድርገን እንውሰድ። የሚወዳደራቸው ወይም የሚወዳደሩት ባላጋራዎች ከእርሱ ይልቅ ብርቱዎችና ፈጣኖች እንደሆኑና እነርሱም ድል ማድረግ እንደማይችል ከተሰማው፤ እነርሱን ለማሸነፍ ተስፋ ከቆረጠ ተወዳድሮም ሊያሸንፍ እንደማይችል በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል። ገና ከውድድሩ መነሻ መሥመር ላይ ይደነግጣል፤ ይሸበራል፤ ይርበተበታል፤ እግሩ ይተሳሰራል። የልቡ ምትም ከፍርሃት የተነሣ በኃይል ስለሚመታ ምቱ ለራሱም እየተሰማው ይረበሻል። ፍርሃት – ፍርሃት እያለው ከውድድሩ ውስጥ ገብቶም ምንም የረባ ውጤት አያመጣም። በእንዲህ ዓይነት ሥነ ልቡና ውስጥ ሆኖም ከሚወዳደር ይልቅ ባይወዳደር ይመረጣል። መንፈሱ ስለተሸነፈ አካሉም ይሸነፋል። በመንፈስ ውስጥ የሌለ ኃይል በአካልም ውስጥ የለም፤ ለራሱ ለአካሉ ኃይል የሚሰጠው መንፈስ ነውና። የጀግናው አትሌታችን የሻለቃ ኃይሌ ገብረ ሥላሴ ኃይልም ያለው ከአሸናፊነት ሥነ ልቡናው ላይ ነው። ልብ ያለው ወጣት ነው። ስለዚህም እስካሁን እያሸነፈ ነው።

አሁንም በጀመርነው – የሩጫ ፉክክር ምሳሌ ለመቀጠል አሸንፋለሁ ብሉ በራስ መተማመን አስፈላጊ የሆነ ሥነ ልቡናዊ ዝግጅት ወይም ሥነ ልቡናዊ ትጥቅ ሲሆን ሌላው አስፈላጊ ነገር ሙያዊ ዝግጅት ወይም ሙያዊ ትጥቅ ነው። ራስን መተማመንም ቢሆን እንዲሁ ከባዶ ተነሥቶ አይደለም። ከባዶ ተነሥቶም መሆን የለበትም። ብዙ ልምምድ ማድረግ ያስፈልጋል። አንድ ሯጭ (ለሌሉቹም ይኸው ነው) ራሱን እየተማመነ በዚያም ላይ ሳይታክት ደህና ልምምድ ሲያደርግ ድል ያገኛል። ያገኘውም ድል ለተከታዩ ውድድር ያዘጋጀዋል። ለተከታዩ ውድድር የአሸናፊነት ሥነ ልቡናውን አሸንፋለሁ የሚለውን በራሱ ላይ የመተማመን መንፈሱን በይበልጥ ያጠነክርለታል። ያደረገውን ተከታታይ ልምምድና በተለያዩ ቦታዎችም ያስመዘገባቸውን ድሎች በዓይነ – ልቡናው ወደ ኋላ መለስ ብሉ በማስታወስ አሁንም ድሉ የራሱ መሆኑን ይገነዘባል። ራሱን የሚተማመነው ያለ ምክንያት አይደለም። በራሱ ለመተማመን ያበቃው 1. በቂ ልምምድ ማድረጉ 2. ተከታታይ ድሎችን እንደ ተጐናጸፈ ማስታወሱ ነው። እነዚህ ሁለት ምክንያቶች በራሱ እንዲተማመን ያደርጉታል። የአሸናፊነት ሥነ ልቡናን ያጐናጽፉታል።

በራስ መተማመን የሚመሠረተው በድል አድራጊነት ተሞክሮ ላይ ነው ይሉናል ዶ/ር ዶኒስ ዌትሊ ( ) በተባለው መጽሐፋቸው፤ መለሰ ወልደ ሥላሴ የአሸናፊነት ሥነ ልቦና ወደ አማርኛ በተረጐሙት ውስጥ በገጽ 36 ላይ እንደሚነበበው ለራስ መተማመን መንፈስ ሙያዊ ልምምድ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑንም ዶ/ር ዶኒስ ዌትሊ አስምረውበታል። በቂ ልምምድ ማድረግና ድል ማስመዝገብ ሁለቱ አንድ ላይ ሲጣመሩ ራስን የመተማመን መንፈስን፤ የአሸናፊነት ሥነ ልቡናን እውን እንደሚያደርጉት ዶ/ሩ ይነግሩናል፤ በተጠቀሰው መጽሐፋቸው መለሰ ወልደ ሥላሴ «የአሸናፊነት ሥነ ልቦና» ብለው በተረጐሙት መጽሐፍ ውስጥ በገጽ 36–37። ቃሉም እንዲህ ይላል።

«በራስ መተማመን ባሕርይ የተመሠረተው በድል አድራጊነት ተሞክሮ ላይ ነው። አንድ አዲስ ነገር በምንጀምርበት ጊዜ የሚኖረን እምነት ትንሽ ነው። ድል ማድረግ እንደምንችል ከተሞክሮ አልተማርንምና። ብስክሌት መንዳት ስንማር በበረዶ ላይ ስንሸራተት በበረዶ ላይ አካላዊ እንቅስቃሴ ስናደርግ ፈጣን የሆነ ጄት አውሮፕላን ስንነዳና ሰዎችን ስናስተዳድር በራሳችን መተማመን የምንጀምረው ቀስ በቀስ ከተሞክሮ እየተማርን ነው። ድል ድልን እንደሚወልድ አያጠራጥርም። አሸናፊዎች በተገኙት ድሎች ያተኩራሉ እንጂ ከዚህ በፊት የገጠሙዋቸውን ሽንፈቶች አያስታውሱም። ከስሕተታቸው ከተማሩ በኋላም ከአእምሮአቸው ፍቀው ያጠፉዋቸዋል። ይሁን እንጂ አብዛኞቻችን ምን ስንሠራ እንገኛለን? ያጋጠሙንን ሽንፈቶች በማስታወስና ያገኘናቸውን ድሎች ጨርሶ በመርሳት በራስ የመተማመን ባሕርይ እንዳይኖረን እናደርጋለን። ሽንፈቶችን ማስታወስ ብቻ ሳይሆን ከስሜት ጋራ በአእምሮአችን እንቀርጻቸዋለን፤ ራሳችንን መውቀስም እንጀምራለን። አሸናፊዎች ግን ከዚህ በፊት ብዙ ሽንፈቶች ቢገጥሙዋቸውም ነገሩ አያሳስባቸውም። ያገኙዋቸውን ድሎች እያስታወሱና እያጠነከሩ እነርሱን አጥብቆ መያዝ ነው የሚያሳስባቸው።»

ራስን የመተማመን ስሜት፤ አሸንፋለሁ፤ ይሳካልኛል የሚለው እምነት ለማናቸውም ዓይነት ሥራ አስፈላጊ መሆኑን አሁንም ዶ/ር ዶኒስ ዌትሊ በዚያው መጽሐፋቸው በተጠቀሰው በአማርኛ ትርጉሙ እንዲህ ይሉናል።

«ተሸናፊዎች ሲናገሩ ዕድሌ ሽንፈት ያመጣብኛል ይላሉ። አሸናፊዎች ሲናገሩ ግን ዛሬ ጥሩ ነበርኩኝ። ነገ ደግሞ የተሻለ እሆናለሁ ይላሉ። አሸናፊዎች አካል፤ በአእምሮ የታዘዘውን እንደሚፈጽም ያስተውላሉ» (ከመለሰ ወልደ ሥላሴ ወደ አማርኛ በተተረጐመው መጽሐፋቸው ገጽ 81)

«ተጠራጣሪዎች አያሸንፉም። አሸናፊዎች ደግሞ አይጠራጠሩም» ይሉናል አሁንም ዶ/ር ዶኒስ ዌትሊ በዚያው በተጠቀሰው መጽሐፋቸው መለሰ ወልደ ሥላሴ ወደ አማርኛ እንደ ተረጐሙት ገጽ 73 ላይ። ንግግራቸውንም በመቀጠል ራሳቸውና ሌሎች ሰዎችም ከልምድ ያገኙትን ቁም ነገር እንዲህ ሲሉ ያካፍሉናል (ከተጠቀሰው

www.ethiopianorthodox.org

መጽሐፋቸው የአማርኛ ተርጉም ገጽ 85–86)

«የምታስበው ይታይሃል የምታየውንም ታገኛለህ የምታገኘው የምታየውን ነው። ወደኋላ የሚጉትትህ ማንነትህ ሳይሆን ስለ ራስህ ያለህ የተሳሳተ አመለካከት ነው።»

ቀና አቅጣጫ የያዘ ሥነ ልቡና ከጤንነትም አኳያ ቢሆን ከፍተኛ አገልግሎት አለው። አንድ ሰው በጠና ታምሞ እንኳ ሳለ ዛሬ ተሽሎኛል ከሰሞኑ ይሻለኛል ብሎ ካሰበና ሊጠይቁት የሚመጡትን ሁሉ በዚሁ እምነት ከተናገራቸው በእውነትም ጤንነቱ ይመለስለታል። እምነት መድኃኒት ስለሆነ ተሽሎኛል ብሎ እንዳሰበውና እንዳለው ሁሉ በእውነትም ይሻለዋል። የሚሆነው በሐሳቡ እንዳሰበው ነው። ሐሳብ በአካል ላይ ተጽእኖ አለው። ስለ ራሳችን ያለን ሐሳብ በአካላችን ሁኔታ ላይ በተጨባጭ ይሠራል። የአካላችን ሁኔታ ሐሳባችን እንደሚለው እሱ እንደሚያስበው ይሆናል። አንተነትህን የሚሰጥህ አንድን ሥራ ለመፈጸም እንድትችልም እንዳትችልም የሚያደርግህ፣ ጤናማም በሽተኛም የሚያደርግህ ሐሳብህ ነው፤ ስለ ራስህ ያለህ ሐሳብ። ሐሳብ ያድናልም ይገድላልም። ስለዚህ ሐሳቡን መቆጣጠር የቻለ በአካሉ ላይ ሊደርስ የሚችለውንም ሁኔታ ሊቆጣጠር ይችላል። ስለ ራስህ ያለህ ሐሳብ ታማሚ ከሆነ አካልህም ታማሚ ይሆናል። ሐሳብህ ደህና ከሆነ አካልህም ደህና ይሆናል። ባጭሩ የምትሆነው እንደምታስበው ነው። ምን ታስባለህ? ያን ነው የምትሆነው። ዶ/ር ዶኒስ ዌትሊም ከፍ ሲል እንደጠቀስሁት የምታየውን የምታስበውን ታገኛዋለህ፤ የምታገኘው የምታየውን ነው፤ የምታስበውን ነው ሲሉ የተናገሩት ቃል እውነት ያለበት ሐሳብ ነው።

አሁንም ዶ/ር ዶኒስ ዌትሊ ይህንኑ ሐሳባቸውን በማጠናከር እንዲህ ይላሉ። «አእምሮአችን በምኞት ሲዋጥ አያሌ አካላዊ መገለጫዎች ይኖሩታል። የምትፈራው ነገር ይደርስብሃል። የጠረጠርከውን ነገር ታገኛለህ። እንደ ገመትከው ሆነህ ትገኛለህ። በራሴ ላይ ይደርሳል የምትለው ትንቢት ያለው ኃይል የሰብአዊ ፍጡር አንዱ አስገራሚ ባሕርይ ነው። ከፍ ሲል ከተጠቀሰው የዶ/ር ዶኒስ ዌትሊ መጽሐፍ የአማርኛ ትርጉም ገጽ 77። ይህንኑ ሐሳባቸውን ለማጠናከር ዶ/ር ዶኒስ ዌትሊ በተጠቀሰው መጽሐፋቸው የአማርኛ ትርጉም (በመለሰ ወልደ ሥላሴ እንደተተረጐመው) በገጽ 78 ላይ እንዲህ ይላሉ። ሉ. ተራቪና እንደ ጃክ ኒኮሉስ ኃይለኛ ሰውነት የለውም። ይሕ የሚል አካላዊ እንቅስቃሴም የለውም። በሜዳውም ሲታይ ይህን ያህል ደስ አይልም። ይሁንና አሸንፋለሁ ብሎ ስለሚጠብቅ ያለው ከፍተኛ ምኞት አስደናቂ ነው። በአንድ ቃለ መጠይቅ «የካናዳና የአሜሪካ ግጥሚያዎችን አሸንፈአለሁ። በሦስተኛ ግጥሚያም ለማሸነፍ እፈልጋለሁ። በእንግሊዝ አገር በሚደረገው ግጥሚያም ለማሸነፍ እንደምችል ይታየኛል ሲል ተናግሮአል። እውነትም እንዳለው አሸነፈ!»

ስሙ ስለተጠቀሰው ስፖርተኛ ዶ/ሩ የተናገሩት ታሪክ የሚያሳየን ሐሳብ፤ እምነት ለአካል ጥንካሬ መስጠቱንና ለድልም ማብቃቱን ነው። አንድ እስፖርተኛ በሐሳብ የሚታየው ድል አካሉን በጥሩ ሁኔታ እንዲገኝ ያደርገዋል። ሯጭም ከሆነ የእግሩ ጅማቶች ተፈታትተው ለሩጫ ፍጥነት ያግዙታል። ልቡም በድካም አይፈርስም፤ ይጠነክራል። ሐሳብ በአካል ላይ ተጽእና እንዳለው እንደ ሐሳቡ ዓይነት በአካል ላይ በጎም ክፉም ነገር ሊደርስ እንደሚችል ዕውቅና ያላቸው ታላላቅ የሕክምና ጠበብትም የሚያረጋግጡት ሐቅ ነው። በአካል ላይ የሚደርሱ እጅግ ብዙዎች ችግሮች፣ እጅግ ብዙዎች በሽታዎች፣ – ሞት ጭምር – የሚመጡት ከሐሳብ ጭንቀት መሆኑ በብዙ ጥናቶች ተረጋግጧል። የጨጓራ፣ የኩላሊት፣ የደም ግፊት ሌላም ሌላም ዓይነት ችግር ያለባቸው ሰዎች ችግራቸው የሐሳብ የጭንቀት ችግር ሁኖ ተገኝቷል። አሁንም ዶ/ር ዶኒስ ዌትሊ እንዲህ ሲሉ በጥናት የተረጋገጠና በተግባርም የታየ ሐሳብ ይነግሩናል።

«በአእምሮና በአካል መካከል ስላለው ዝምድናና አንዱ ሌላውን እንዴት እንደሚነካው ከተደረገው ጥናትና ምርምር የተገኙ አያሌ ውጤቶች አሳይተዋል። በሽታ በጀርም ወይም በሕዋሳት ብቻ እንደማይመጣ ሊቃውንቶች እያወቁት መጥተዋል። ሁሉም ሰዎች ሕዋሳት ቢኖሩዋቸውም ጥቂቶች ብቻ ይታመማሉ። ይልቅ የሕመም መንሥኤ ገለሰቦች በሕይወት ላይ ካላቸው አመለካከት ጋር በቅርብ የተዛመደ ሆኖ ተገኝቷል።

ፍርሃትንና ጭንቀትን የሚያስከትሉ ሁኔታዎች አያሌ የሰውነት አሠራሮችን ስለሚጫኑ ሰውነታችን የሕመም ጠንቆችን ለመከላከል በውስጡ በሚፈጥራቸው ፕሮቲንና ቅመም ላይ ጫና ሊያደርስባቸውና አሠራራቸውም ሊቃወስ ይችላል። እነዚህ አስጨናቂ ሁኔታዎች ሆርሞን እንዳያመርቱ እጢዎቻችንን ሊያቃውሱ ይችላሉ፤ ስሜታዊ ሚዛንን በማምጣት ረገድ ሆርሞኖች ከፍተኛ ሚና አላቸውና። ስሜቱ የተቃወሰበት ሰውም ለአደጋ በጣም የተጋለጠ ነው። የሆድ ወይም የጨጓራ ቁስል ከበላነው ሳይሆን ከሚበላን ነገር እንደሚመጣ ተረጋግጧል ከፍ ብለን ከጠቀስነው ከዶ/ር ዶኒስ ዌትሊ መጽሐፍ በመለሰ ወልደ ሥላሴ የአሸናፊነት ሥነ ልቦና ተብሎ ከተተረጐመው ውስጥ ከገጽ 76 የተወሰደ)

«የሆድ ወይም የጨጓራ ቁስል ከበላነው ሳይሆን ከሚበላን ነገር እንደሚመጣ ተረጋግጦአል የሚለውን የዶ/ር ዶኒስ ዌትሊን ሐሳብ ለአንድ አፍታ እናጢነው። ሰው ሁሉ የተባሉት በሽታዎች መጡብኝ ብሎ የሚያስበው ከበላው ምግብ እንደሆነ ነው። በቀደምዕለት ወይም ያለፈው ዓመት ከእገሌ ቤት እንዲህ እንዲህ ዓይነት ምግብ በልቼ ነበር። ከዚያ ወዲህ ጤናም የለኝ ይላል። ነገር ግን ዶ/ር ዶኒስ ዌትሊ ከበላነው ሳይሆን ከሚበላን ነገር ነው የሁለቱም በሽታዎች መንስኤው ብለው ሐሳቡን አርመውታል፤ አስተካክለውታል። በእውነትም እርሳቸው እንዳሉት የተባሉት ሕመሞች ከጭንቀታችን ወይም ከንዴታችን፣ ከቁጭታችን ሊመጡ እንደሚችሉ ማሰብ ይቻላል። ጭንቀት፣ ንዴት፣ ውስጥ ውስጡን ለብዙ ጊዜ ሲበላን፣ ውስጥ ውስጡን ሲያኝከን፣ ውስጥ ውስጡን ስናብሰለስለው ለጨጓራና ለሆድ ሕመም እንዳረጋለን። ይህም እውነት መሆኑን ማረጋገጥ ከተፈለገ የሚከተለውን ሐቅ ልብ እናድርግ። ንዴት የሌላቸው ብስጭት የሌለባቸው ጭንቀትም የማያውቁ አንዳንድ ሰዎች ከዚህ ሁሉ ነጻ ናቸው። ይህ ዓይነቱ በሽታ የሚያጠቃው ብስጭት፣ ንዴት፣ ያለባቸውን ሰዎች ነው። ስለዚህም ለሆድም ሆነ ለጨጓራ በሽታ መፍትሄው ከዚህ ወይም ከዚያ ምግብ መቆጠቡ አይደለም። ዶ/ሩ እንዳሉት መንስኤው በምንበላው ምግብ ሳይሆን በሚበላን ነገር፣ በሐሳባችን በምናብሰለስለው በምናውተለትለው ነገር ነው ማለቱ ትክክለኛ ይመስላል። ለዚህ ሐሳብ እውነተኛነት ፍንጭ ሊሰጡን የሚችሉ የአንዳንድ ሰዎች ታሪክም ዶ/ር ዶኒስ ዌትሊ ከአንድ ስመ ጥር የሕክምና ባለሟል ከዶክተር ቤንሰን መጽሐፍ አጣቅሰው የሚነግሩን በእውነት የደረሰ ታሪክ እንዲህ ሲሉ ይገልጹልናል።

በዶክተር ቤንሰን መጽሐፍ ውስጥ አንድ የተመዘገበ ምሳሌ እናገኛለን። እርሳቸውም መንገድ በሄደበት ጊዜ በአንድ የቀድሞ ጓደኛው ቤት ስለተኛ አቦሪጅናዊ ወጣት ይነግሩናል። ጓደኛው ለቁርስ ያዘጋጀለት ምግብ ከአንዲት የበረሃ ወፍ የተሠራ ነበር። ይሁንና እንግዳው ወጣት እንደዚህ ያለ ምግብ እንዳይበላ በጥብቅ ተከልክሎ ነበር። ወጣቱ ሰው ምግቡ በበረሃ ወፍ የተሠራ እንደሆነ ለማወቅ ጥያቄ ቢጠይቅም እንግዳ ተቀባዩ አይደለም ሲል መለሰለት። ወጣቱም ምግቡን ከበላ በኋላ ወደ አገሩ ተመለሰ። ከብዙ ዓመታት በኋላ ሁለቱ ጓደኞች እንደገና ሲገናኙ ሽማግሌው አሁንም የበረሃ ወፍ ይበላ እንደሆነ ጓደኛውን ይጠይቀዋል። የጐሣው ሽማግሌዎች እንዳይበላ በጥብቅ አዘውት ስለነበር እንደማይበላ ይገልጽለታል። ሽማግሌውም ለወጣቱ የተከለከለውን ምግብ እንዴት እንዳበላ እንደ ተቀባዩ እንዴት እንዳታለሉት እየሳቁ ለወጣቱ ይነግሩታል። ወጣቱም ከመጠን በላይ ፈራና መንቀጥቀጥ ጀመረ። በ24 ሰዓት ውስጥም ሞተ።

በምዕራቡ ዓለም አያሌ ተመሳሳይ ጥንቆላ ሞት እንዳደረሰ በብዙ ታሪኮች ተረጋግጦአል። 43 ዓመት ሲሞላሽ ትሞቺ አለሽ ሲል ጠንቋዩ ትንቢት ተናገረ። ይህ ትንቢት የተነገራት የጠንቋዩ ደምበኛ የአምስት ዓመት ልጅ በነበረች ጊዜ ማለትም ከ38 ዓመት በፊት ነበር ትንቢቱ የተነገራት። ይህች ትንሽ ልጃገረድ ይህን አስፈሪ ትንቢት በአእምሮዋ ውስጥ እንደቀረጸች ታድጋና 43ኛውን የልደት በዓልዋ ባከበረች ሳምንት ሞተች ሲል የእንግሊዙ የሕክምና መጽሔት ዘግቧል።

የዚህች በሽተኛ ከፍተኛ ስሜታዊ ውጥረት የቀዶ ጥገናውን አካላዊ ውጥረት አሸንፎ ገድሉአት እንደሆነ ከመገረም አልፈን የምንለው የለንም ሲሉ ዶክተሮቹ ተናግረዋል።

ይህች አነስተኛ ቀዶ ጥገና የተደረገላት በውጭ ስትታይ ጤናማ መስላ የምትታየው የአምስት ልጆች እናት እሞታለሁ ብላ ፈርታ ይሆናል ሲሉ ዶክተሮቹ አሰቡ። ከሁለት ቀን በኋላ ሞተች።

ሴትየዋ ስለ ጥንቆላው ታውቅ ለነበረችው እህትዋ ከመናዘዝዋ አንድ ቀን ቀደም ብሎ የማደንዘዣ መድኃኒት ከተወጋሁ በኋላ አልነቃም የሚል እምነት እንደነበራት እህትዋ ተናግራለች።

ቀዶ ጥገናው በሚደረግበት ቀን ሴትየዋ እንደምትሞት እርግጠኛ መሆንዋን ለአንዲት ነርስ በጠዋቱ ብትናገርም ዶክተሮቹ ስለዚህ ፍርሃት የሚያውቁት ነገር አልነበረም። ቀዶ ጥገናው ከተደረገ ከአንድ ሰዓት በኋላ ሕሊናዋን ስታ ፀጥ አለች። ምንም ምክንያት ሳይኖረው ከፍተኛ ውስጣዊ መድማት መኖሩን በአስከሬኑ ምርምር ሊረጋገጥ የቻለ ጉዳይ ነው። የእንግሊዝ ሕክምና ማሕበር አፈ ቃላጢ ይህን በሚመለከት «ምንም ሕክምናዊ መግለጫ ማቅረብ አይቻልም። ይልቅ ጠንቋዮቹ ትሞታላችሁ ባሏቸው ቀንና ሰዓት የሚሞቱ ሰዎችና የዚህች ሴት ሞት ተመሳሳይ ሆኖ እናገኘዋለን» ሲል ተነግሮአል።

በሺዎች የሚቆጠሩ በጣም የተለያዩ ሰዎች የሕይወት ታሪካቸው በጥንቃቄ ሲጠና የጤና ለውጦችን ማለትም ሕመም አደጋና እርግዝናም ሳይቀር በመጠኑ በትድሚያ ሊታወቅ እንደሚችል አያሌ አዋቂ ጠበብትን አሳምኖአል፤ በመለሰ ወልደ ሥላሴ ከፍ ሲል ከተጠቀሰው ከዶ/ር ዶኒስ ዌትሊ መጽሐፍ የአማርኛ ትርጉሙ ገጽ 75–76።

ሐሳብ፣ ጭንቀት፣ ፍርሃት ምን ያህል የጤንነት ችግር እስከሞት ድረስ ሊያደርስ እንደሚችል ዶ/ር ዶኒስ ዌትሊ ከዶክተር ቤንሰን መጽሐፍ አግኝተው የተረኩልን ታሪክ ያረጋግጥልናል።

የበረሃ ወፍ ሥጋ አትብላ ተብሎ በጐሣው ሽማግሌዎች ተነግሮት ሳለ ከቤቱ አሳድሮት (አስተናግዶት) የነበረው ሽማግሌ አታለሎ ሥጋውን ካበላው ብዙ ዓመት ካለፈ በኋላ ዳግመኛ በተገናኙ ጊዜ ምን ሥጋ አብልቶት እንደ ነበር ሲነግረው በድንጋጤ የተንቀጠቀጠውና በ24 ሰዓት ጊዜ ውስጥ ለሞት የበቃው ወጣት የሞተው በተባለው ወፍ ሥጋ ምክንያት ሳይሆን ከድንጋጤ መሆኑን መገመት ይቻላል፤ ምክንያቱም ችግሩ የነበረው ከራሱ ከወፉ ሥጋ ቢሆን ኑሮ ብዙም ዓመት አይቆይም ነበር። አሁን ግን ታሪኩን እንደ ተረዳነው ለብዙ ዓመት በሰላም ኑሮ ሳለ የምን ሥጋ እንደ በላ እውነቱ ሲነገረው በድንጋጤ መንቀጥቀጡና መሞቱ ከወፉ ሥጋ ሳይሆን ከድንጋጤ የመጣ መሆኑን መረዳት ይቻላል። የበረሃ ሥጋ ወፍ መብላት ምንም ችግር እንደማያመጣ በመካከሉ ያስተማረውና ሐሳቡን ያስለወጠው ሰው ቢኖር ኑሮ ምን ሥጋ እንዳበሉት ቢያውቅም ኑሮ እንኳ ምንም አይሆንም ነበር። ስቶ ነገሩን በቸልታ ያልፈው ነበር። ስለዚህም ያ ወጣት የሞተው የበረሃ ወፍ ሥጋ ስለ በላ ነው አንልም። ይልቁንስ የሞተው ዶ/ር ዶኒስ ዌትሊ ከፍ ሲል በጠቀሱት ሐሳብ ለመጠቀም በበላው ሥጋ ሳይሆን እርሱን ራሱን ወጣቱን በበላው ጭንቀት ነው ማለቱ ይቀልላል።

ፍርሃትና ጭንቀት በአካል ላይ ተጨባጭ ችግር የሚታይ ችግር ሊያደርስ እንደሚችል ከፍ ሲል ከተጠቀሱት ምሳሌዎች ሌላ የሚከተለውም ምሳሌ ያሳያል የሚል እምነት አለኝ።

አንዲት ኮረዳ ባል በማግቢያ ዕድሜዋ ላይ ፊቷ ብጉር ወይም ሌላ ተመሳሳይ የፊት ችግር እንዳያገኛት ልታስብ ልትሰጋ ትችላለች፤ ምክንያቱም ያን ዓይነት ነገር ከወጣብኝ ፊቴን ስለሚያበላሽብኝ ብዙ ፈላጊም አላገኝም የሚል ጭንቀት ሊኖራት ይችላልና ነው። እንዲህ አድርጋ ለብዙ ጊዜ ካሰበችና ሌት ከቀን ከተጨነቀች ከየት መጣ ሳትለው የፈራችው ነገር ሊደርስባት ይችላል። ፍርሃቷ፣ ጭንቀቷ ችግሩን ይጠራዋል። አካል ለፈሩት ለሰጉበት ነገር ይታዘዛልና። ስለዚህም ነው ለምንም ነገር ፍርሃት ስጋት የሌላቸው ሰዎች ብዙውን ጊዜ የአካል ችግር ሳይደርስባቸው የሚበልጠውን የሕይወት ዘመናቸውን በሰላም የሚኖሩት። ምክንያቱ ይህ እንጂ እነርሱ ከሌላው ሰው የተለየ አካል ኑሮአቸው አይደለም ችግር የማይደርስባቸው። ስለ ምንም ነገር ግድ የሌላቸው ሰዎች ስለሆኑ ችግሩም አያገኛቸውም። እሱም አይፈልጋቸውም።

ከዚህ በመቀጠል ከወጣቶች ጋር ውሎ የሚያደርጉ፣ የሥራቸው ጠባይ ከወጣቶች ጋር የሚያገናኛቸው ሰዎች ወጣቶችን እንዴት አድርገው ቢይዙዋቸው ከእነርሱ ጋር በጋራ ጥሩ ሥራ ሊያከናውኑ እንደሚችሉ ደግሞ ከሽምግልና ዕድሜዬ ያገኘሁትንና ዕድሜ ልኬንም ከወጣቶች ጋር ያሳለፍሁ ሰው እንደመሆኔ መጠን ከዚያ ያገኘሁትን አንዳንድ ልምድና ትውስታ ባካፍላችሁ ምናልባት ትንሽ ሳይጠቅማችሁ አይቀርምና ተከታተሉኝ።

ወጣት በሚገባ ከያዙት ተግባቢ ነው። ወጣት ላወቁበት ጠባዩ አስደሳች ነው። ወጣት ጠባዩ ልስልስ ነው። ወጣት ትሁት ነው። ወጣት ጥሩ ባልንጀራ ነው። ከእርሱ ጋር መሥራት ያስደስታል። ይሁንና ከእርሱ ጋር ተስማምቶ ለመኖርና ፍሬ ያለው ሥራ በጋራ ለመፈጸም ጠባዩን ማወቅና እንደ ጠባዩ መሆን ግድ ይሆናል። ከወጣት ጋር በሰላም ለመኖር የፈለገ ሰው ወጣት የማይፈልገውን ነገር ከማድረግ መቆጠብ አለበት። ይህንንም ዘርዘር አድርገን ለማየት እንሞክር።

ከሁሉም በፊት ወጣት እንደ ሕጻን ልጅ እንዲታይና እንዲሸነገል አይወድም። ትናንት ሲያውቁት ሕፃን ስለነበር ትናንት ማሙሽ ስለነበር ዛሬም እንደ ትናንቱ በማሙሽነት እንዲያዩትና ጆሮህን ልያዝ እንዲሉት አይወድም። ለሴቷም ወጣት ይኸው ነው። ወጣት ከተወቀሰም (ሊወቀስ ግድ አስፈላጊ ከሆነም) ለብቻው ጠርቶ መውቀስ፣ መምከር እንጂ ከጓደኞቹ ፊት በተለይም ደግሞ ከሴቶች እህቶቹ ፊት ሊወቅሱትና ክፉ ቃል ሊናገሩት አይወድም የዕድሜውን እናሳነት ተመልክቶ ማንም ክብሩን ዝቅ አድርጎ እንዲያየው አይወድም። ወጣት የአትንኩኝ ዕድሜ ነው። ወጣት ተከባብረን እንኑር ባይ ነው። ካልደረሱበት አይደርስም። ከደረሱበትም አይለቅም። ወጣት ከደረሱበት የሰው ነብር ነው። ወጣት ከደረሱበት እንደ ነብር ትንሽ ይበቃዋል። በጥሩ ሁኔታ በአክብሮትና በፍቅር ለያዘው ግን ቅቤ ነው። አሁንም ወጣት ማስመሰልን አይወድም። ወጣት ሰውን የሚያከብረው ሽማግሌ ስለሆነ ወይም የቤተ ክርስቲያን ሰው ስለሆነ ማለትም ቄስ ወይም መነኩሴ ስለሆነ ባለሥልጣንም ስለሆነ አይደለም። የሚያከብረው የሚያስከብር ጠባይ ሲያይበት ነው። እንደ ዕድሜው እንደ ኃላፊነት ቦታው ሰብሰብ ያለ ጨዋ ሰው፣ ረጋ ያለ ሰው ሁኖ ሲያገኘው ብቻ ነው።

ወጣት ሌላው የማይወድደው ነገር መንቻካነትንና ንዝንዝን ነው። ነዝናዞች ከሆኑ ሽማግሌዎችንም ቢሆን በሽምግልናቸው ምክንያት ብቻ ሊያከብራቸውና የሚሉትን ሊሰማ ፈቃደኛ አይሆንም። እናስተምርህ እንምከርህ ቢሉት በሆዱ መጀመሪያ እናንተ ራሳችሁ ትምህርት ያስፈልጋችኋል፤ መጀመሪያ እናንተ ተመከሩ በማለት ለሚናገሩት ቃል ቁም ነገር አይሰጠውም። ሌላም አስፈላጊ ነገር አለ። ወጣት ጥሩ ሲሠራ ለሚሠራው ሥራ ዕውቅና እንዲሰጠውና የሥራ ዕድገት እንዲያገኝ ይሻል። ይህን መጠየቁም ክፋት የለውም፤ ተገቢ ጥያቄ ነው። ሠርቶ እንዳልሠራ ደክሞ እንዳልደከመ ከታየ ግን ሞራሉ ይነካል። አሠሪውንም ይጠላል ይንቀዋልም። በእርሱ ሥር መቆየትንም ስለማይሻ ዕድል ካገኘ አንድ ቀን አያድርም። ጥሎት ይሄዳል።

ከዚህ በላይ ስለ ወጣቶች የገለጽሁዋቸው በጎ ቃላት ለብዙዎቹ ወጣቶች የሚስማሙዋቸው ናቸው። ይህን ስል ግን አልፎ – አልፎ ወጣቶችን በክፉ የሚያስነሱ ክፉ ምግባር ያላቸው ወጣቶች የሉም ማለቴ አይደለም፤ አሉ። ነገር ግን የአንዳንድ ክፉ ወጣቶች መኖር ወጣት ሲባል ይኸው ነው አያሰኝም። በአስተዳደጉ ምክንያት ደግሞም በሚደርስበት አንዳንድ የአድልዎ ሥራ በመናደድና ተስፋ በመቁረጥ ጠባዩ የከፋ አንዳንድ ወጣት ሊኖር ይችላል። ከዚህ አንጻር እሱንም እንኳ ቢሆን በክፉ ዓይን ማየትና መወንጀል አይገባም። በወጣቱ ላይ

www.ethiopianorthodox.org

የማያስደስት ትንሽ ጥፋት በታየ ቁጥር መናደድና መጮህ ከመጣማ ግን ሊቀርለት ነው? እንዲህ ከሆነ ከሽማግሌስ ቀበጥ የለም ወይ? ቀበጥ የለም ወይ ስል ከዕድሜው ጋር የማይሄድ ቀላል ሽማግሌ የለም ወይ ነው። እንዴታ አለ እንጂ። መንፈሳውያን ከተባሉ ሰዎችስ ስሙን ብቻ የያዙ እንትል መነኩሳትና ቀሳውስት የሉም ወይ? ጠባያቸውና ምግባራቸው ከስማቸው ጋር የማይሄድ ዓለማውያን የሆኑና ከዓለማውያንም እጅግ የከፉ የሉም ወይ? እንዴታ አሉ እንጂ፤ የቀለሉ እንዳሉ ሁሉ የከበሩም አሉ። ናስና ቆርቆሮ የሆኑ እንዳሉ ሁሉ ወርቅና እንቁ የሆኑም አሉ። ሁሉም አንድ አይደሉም።

አሁን ደግሞ ወጣቶችን እናንተ እያልሁ እስቲ በሁለተኛ መደብ ላነጋግራችሁ። የምሰጣችሁ ምክር ስላለኝ አድምጡኝ። ሳልሸሽጋችሁ ድክመታችሁን ከፊታችሁ እነግራችኋለሁ። ይህንም የማደርገው ስለ ምወዳችሁ ነው። ደጋግሜ ያየሁባችሁ ድክመት ስለሆነ አርሙት። ድክመት አለባችሁ የምለውም እንዲህ ነው።

በኅብረተሰብ ውስጥ ከአንድ የሆነ የሥራ ቦታ ላይ አንዳንድ ድክመት ስታዩ ለምን እንደዚያ ይሆናል? – ያ መሆን የለበትም ብላችሁ ወዲያውኑ ቱግ ትላላችሁ። ወዲያውም ኩርፍ ትላላችሁ። ከቁጣችሁ የተነሣም ክፉ ቃል ይወጣችኋል፤ በዚህም ሰውን አሳዝናችሁ ሰውም እንዲያሳዝናችሁ ታደርጋላችሁ። ብዙም ትዕግስት የላችሁም። በእርግጥ ክፉ ነገር ሲፈጸም አይታችሁ ማዘናችሁ በራሱ ክፉ አይደለም በጎ እንጂ። መቈጣታችሁ ሁሉም ነገር በትክክል ይሠራ ማለታችሁ ስለሆነ ጤናማ አስተሳሰብ ነው። በዚህ ቅር መሰኘታችሁ ተገቢ ነው። ታዲያ እንዲህ ሲሆን ቁጣችሁ መጠን እንዲኖረው ያስፈልጋል። ልክ እንዲኖረው ያስፈልጋል። ከልቡ የወጣ ነገር ጥሩ አይደለም። እንደ ማር ጣፋጭ የለም። ነገር ግን ከበዛ እሱም እንኳ ይመራል። ነገሮች በትክክል ይሠሩ ማለታችሁ በራሱ በጎ ነገር ሳለ አንድም ነገር እንኳ መዛነፍ የለበትም ማለታችሁና አጥብቃችሁ መቆጣታችሁ አግባብነት የለውም።

ሁሉም ነገር በትክክል መሠራት አለበት ለምትሉት ሐሳብ እኔ ደግሞ ለምንድን ነው? ወይም እንዴት ነው? ሁሉም ነገር በትክክል ይሠራ የሚባለው? እላለሁ። ያለነው እኮ በጎደሎ ዓለም ውስጥ ነው። በእርእያንታችን ልንለውጠው ልናሻሽለውና ልናሳድገው በሚገባን ዓለም ውስጥ ነው ያለነው። ፍፁም የሆነ ዓለም ቢሆን ኑሮ ግብዝነትም ተንኮልም ጭካኔም ሌላውም ሌላውም ሁሉ ድክመት አይኖርበትም ነበር። እንደዚያ ከሆነ ደግሞ እናንተም የሚያሳዝናችሁና ክፉ ቃል እንዲወጣችሁ የሚያደርጋችሁ ነገር አይኖርም ነበር። በዚህ ክፉ ዓለም በዚህ ጉደሎ ዓለም ውስጥ እየኖሩ ለጥቃቅን ሁሉ ነገር ከዙና ከተበሳጩማ ግበድ ይመጣል። በዚህ ጉደሉ ዓለም ውስጥ እየኖረ የሚበሳጭን ሰው እኔ የማየው ከቆሻሻ ነገር ላይ ቁሞ ወይም ተቀምጦ ምን ሸተተኝ ብሎ አፍንጫውን እንደሚይዝና እሪ ብሎ እንደሚጮህ ዓይነት ሰው አድርጌ ነው። በሁሉም ነገር ላይ የሚያዝንና ተስፋ የሚቆርጥ ወጣት ከሁሉም መጀመሪያ የሚጐዳው ራሱን ነው። ራሱን በመጐዳትም በተዘዋዋሪ መንገድ አገሩንም ይጐዳል። በንዴትና ተስፋ በመቁረጥ የሚበሳጭ ከሆነ አገር ጤናማና ገንቢ ትውልድ ታጣለች። ወጣቶች ያለ አገራችን ማን አለን? ትሉ ይሆናል። አዎ ነው። ነገር ግን አገርስ ያለ እናንተ ማን አላት?

የነገይቱን ኢትዮጵያ ተረካቢዎች መሆናችሁን አትዘንጉ። እኛ በቅርቡ እናልፋለን። በቅርቡ ስለምናልፍም ተረካቢ መኖር አለበት። የምትረከቡንም እናንተ ናችሁ። ስለዚህ በንዴትና በብስጭት ጤንነታችሁን የሚጐዳ ነገር መፈጸም የለባችሁም ምክንያቱም እንደዚያ በማድረግ አገራችሁን ትጎዳላችሁና። የተመኛችሁት ነገር ሁሉ ዛሬ ባይሳካላችሁ ነገ ሊሳካላችሁ ይችላል። ነገም ባይሳካላችሁ የተነገ ወዲያውን ደግሞ ለማየት ትዕግሥት ይኑራችሁ። በትዕግሥት ሁሉ ነገር ይጨበጣል። በጣም ሽማግሌ የሆነ ሰው እንኳ ቢሆን ከአሁን በኋላ ምን ያህል ጊዜ ልቆይና ነው ተስፋ የማደርገውና የምታገሰው ይል ይሆናል። ነገር ግን እናንተ ወጣቶች ናችሁ። ስለዚህም ያን ልትሉ አትችሉም። ወደፊት ገና ብዙ ዕድሜ አላችሁ፤ ገና ብዙ ትቆያላችሁ። ስለዚህ በጣም መቻኮል በትንሹም በትልቁም ተስፋ መቁረጥ የለባችሁም። እኛ ሽማግሌዎቹ እንኳ እኛ ብዙ የማንቆየው እንኳ ገና እንቆያለን ገና እንኖራለን ብለን እናስባለን። እንደዚያ ብለን ስለምናስብም ተስፋ አንቆርጥም። ነገ እንዲህ አድርጌ ተነገ ወዲያ ደግሞ እንዲህ ሆኜ ከዚያም በኋላ ይህን ይህን አድርጌ ከዚህ እደርሳለሁ እንላለን። እኛ እንኳ ከእኛ ይልቅስ ይህን ማለቱ በይበልጥ በእናንተ በወጣቶች ላይ አያምርም? – እንዴታ ይበልጥ የሚያምረው በእናንተ ላይ ነው። ጤና ካላችሁ ሁሉንም ትደርሱበታላችሁ። የሀገር ተረካቢዎች እንደ መሆናችሁ መጠን ተወደደም ተጠላም ዛሬ በሌሎች የተያዘው ቦታ ሁሉ የእናንተው ነው።

## ስለ ዐሥርቱ ቃላት

ከዐሥርቱ ቃላት መዠመርያው አንዱ
በፍጹም ልቡና እግዚአብሔርን ውደዱ።
ከመጽሐፍ ቃል ወጥቶ በሰንበት የሠራ
ዕረፍት አያገኝም ከሰማይ መከራ።
አባትና እናቱን በምግብ የማይረዳ
ተበድሮ በልቶ አልከፈለም ዕዳ።
አልታገሥ ብሎ የሰው ነፍስ ገዳይ
በምድር ርስት ያጣል ስንኳንስ በሰማይ።
ዝሙት የወደደ ሞቱን ማሰብ ትቶ
እንስሳ ነው እንጂ ምን ይባላል ከቶ።
የሰው ገንዘብ ሲሰርቅ ልቡ የማይሠጋ
ሲገረፍ ይኖራል በእሳት አለንጋ።
በሐሰት መስክሮ በሐሰት የማለ
ከብርሃን ጨለማ ይሻለኛል አለ።
ከሰው ሚስት የሚሄድ ጠላት ነው ለራሱ
ወዲህም በሥጋው ወዲህም በነፍሱ።
የሰውን ከብት አይቶ መውደድ መመኘት
ከኵነኔ በቀር አያሰጥም ሀብት።
መንግሥተ ሰማያት አትገኝም ነፍሳ
ሰውን ካልወደዱ እንደ ራስ አድርጎ።

## ስለ ስድስቱ ቃላት

«ማቴ.5:22:28:32:34፤ 39:41»

ስድስቱ ቃላትን ጽፎልናል ከፍሎ
ወንድም ከማሳዘን ተጠበቁ ብሎ።
ለኔ ትኹን ብሎ ሴትን መመልከት
እጅግ ፍጹም በደል ታላቅ ኀጢአት።
ሳትመንዝርበት ሚስቱን የሚፈታ
ይፈረድበታል በላይኛው ቦታ።
በውነት እንኳ ቢኾን መሐላ ይቅር
ይሻለናልና የላይኛው ክብር።
ክፉ ለሠራ ሰው በጎ የመለሰ
ዘላለም ይኖራል ጸጋ እንደ ለበሰ።
ጠላትን ቢወዱ ይወዳል ፈጣሪ
ርሱ ስለ ሆነ የኹሉ አሳዳሪ።

## የስድስቱ ቃላት መርገፍ

ሌሎችም መጻሕፍት ብለውናል ሲያዙ
የምድሩን ትታችሁ የሰማዩን ያዙ።
እኹን ምን አለና እንደ ሰው ደንቁር
ለምድር የሚለውጥ የሰማዩን ኑሮ።
ኹሉን ያታልላል የዚህ ዓለም ተድላ
ጥቂት ሳይሰነብት ሳይገኝ ለኋላ።
የሥጋ መከራ ይፈጸማል በድሜ
ለነፍስ መከራ የለውም ፍጻሜ።
ገሃነም ከገቡ አይገኝም ተስፋ
ለትሉ እንቅልፍ የለው እሳቱም አይጠፋ።
የኋላ መከራ አይወርድም ከራስ
ይህን እያሰበ ሰው ኹሉ ያልቅስ።

አለቃ ዕንቁ ባሕርይ

(ራስ ጉበና ቤት የነበሩ ሊቅ የገጠሙት

# ስስትግቡእ

(እስትግቡእ – ጥርቅም፣ የተቀመመ፣ የተሰባሰበ እንደማለት ነው)

## የጉድ ዘመን

በ1907 ዓ.ም አዶከበሬ የተባለ የዛር ዓይነት በሽታ በሸዋ ባላገር ላይ ተገኝቶ ሴቱንም ወንዱንም ያስጨፍረው ጀመር፤ በሽታው ከትግሬ የመጣ ነው ስለሚባል በሽተኛው የትግርኛ ዓይነት እየተናገረ ይቀባጥራል፤ በሽታውንም ለመሸኘት ድግሥ መደገስ ስለሚያስፈልግ ድሃው ሕዝብ ባለጣጣ ሆነ።

ዳግመኛ ሞያሌ የተባለ በእግር ላይ የሚገባ የቁንጫ ዓይነት በሽታ በዚህ ዘመን ስለመጣ የሁሉም እግር በወረንጦ ሲዘነጠል ይውል ጀመር። ስሙ ሞያሌ መባሉ በሽታው የመጣው በቦረና ውስጥ ካለው ሞያሌ ከተባለው ሥፍራ በመሆኑ ነው እየተባለ ይነገር ነበር።

ጣጣቴ የተባለ በሽታ ደግሞ በዚሁ ዘመን መጣ፤ የትኩሳት በሽታ ነው፤ የጥንጥላ መገተርያ ብረት በእሳት አግሎ የበሽተኛውን ገላ በተተኮሱት ጊዜ ይንጣጣ ነበርና ከዚህ የተነሳ የበሽታው ስም ‹ጣጣቴ› ተባለ።

እንዲሁም ደግሞ ዕጣን እየተጨሰ ቡና የመጠጣት ልማድ በሸዋ ባላገር ዘንድ የተጀመረው በዚሁ ጊዜ ነው። ከዚያ በፊት ግን ይህ ዓይነት ልማድ የሚታየው በነጋዴዎችና በእስላሞች በተለይም በቃልቻች ዘንድ ነበር። በበረሃ ሥፍራ ነፍጠኞችም የዚሁ ዓይነት የቡና ሱስ አለባቸው። እነዚያ ነፍጠኞች ወይም ነጋዴዎች ወደ አገር ቤት በተመለሱ ጊዜ ዕጣን እያጨሱ ቡና ይጠጡ ነበርና ሌላውም ሰው እነርሱን አይቶ ተከተለ። ይልቁንም የየመንደሩ ሴቶች የቡና ወንፈል እያበጁና ተራ በተራ እየተጠራሩ ቡና ሲያፈሉና ሲጠጡ መዋል ጀመሩ፤ ይህ ልማድ በባላገር ሆነ በከተማ እየተስፋፋ ስለሄደ ብዙ ሰው የቡና ሱሰኛ ሆነ። የቤተ ክህነት ሰዎችም በቤተክርስቲያን የሚጨስ ዕጣን ለቡና ማጨስ እምልኮ ባዕድ ነው እያሉ ተቃውመው ነበር። የሆነ ሆኖ ውሎ አድሮ እየተለመደ ሄደ።

1907 ዓ.ም አፄ ምኒልክ ያረፉበት ዘመን ነው።

## ከሃይማኖት ማኅደራችን

በ1905 ዓ.ም በደሴ እስላሞችና ክርስቲያኖች የሃይማኖት ክርክር አድርገው ነበር። ክርክር ሲጀመር አፈ ጉባኤው አለቃ በዛብህ እንዲህ አሉ፤ «ከመከራከራችን በፊት እስላሞች የተረቱ እንደሆን ክርስትና ሊነሱ እኛም ብንረታ ወደ እስልምና ልንገባ እንፈራረም» ከዚህ በኋላ እስላሞች መረታታቸውን አምነው አንፈርምም አሉ።

ልጅ ኢያሱ የቀጨኔ መድኃኔ ዓለምን በ1903 ዓ.ም እንደመሠረቱ የፕሮቴስታንቶችንና የካቶሊካውያንን ሃይማኖት ከኢትዮጵያ ውስጥ ለማጥፋት አሰቡ። አስበውም አልቀሩ በሚሲዮናዊ ትምህርት ቤት የሚማሩትን የኢትዮጵያ ልጆች ሁሉ በዘበኛ እያስያዙ አሠሩ። የተገረፉም አሉ። ምክንያቱም ፈረንጆች መንፈሳውያን፣ ገባርያን ሰላም መስለው፣ ወንጌልን እንሰብካለን እያሉ የኢትዮጵያን ሕፃናት በልብስና በስኳር እያታለሉ ጠባያቸውን ይለውጡብናል፤ ሃይማኖታቸውን ያጠፉብናል፤ መንግሥታቸውን አክባሪ፣ አገራቸውን አፍቃሪ፣ አይሆኑም፣ በምግባር የረከሱ፣ በሃይማኖት ያልጸኑ የጥቅም ተገዥዎች ይሆናሉ። ሚሲዮን ማለት ሰላይ ማለት ነውና ኢትዮጵያን ወንዟን፣ ተራራዋን፣ ዱሯን፣ ገድሏን፣ እየሰለሉ ከውጭ ጠላት በተነሳብን ጊዜ መሪ ሆነው ይመጡብናል ብለው አሰቡ።

የታሪክ ትዝታዬ በአቤቱ ኢያሱ ዘመን ገጽ 32–33 ያልታተመ

• • •

«ትግል ከመሬት ጋር ነው፣ ትልቅ ሰው ማለት ለመሬት ሎሌነት ያደረ ነው፣ ከዚያም ቢያንስ ከሌላ ጌታ ከማደር ለኔ ያደረ ነው» አፄ ምኒልክ

• • •

«የሰው ሀገሩ ምግባሩ የላም ሀገሩ ሣሩ» አፄ ታዎድሮስ

(ሥነ ምግባር 1948)

## የደንቆሮ ወገኑ ብዙ ነው

ሁለት ቄሶች ባንድ ቀለም ተከራከረው አለቃ ገብረሃና ዘንድ ሄደው «ይመስክሩልን» ቢልዋቸው አለቃ ፊታቸውን ወደ አንደኛው ዞር አደረጉና «ወንድሜ የደንቆር ወገኑ ብዙ ነውና እንዳታስደበድበኝ አልመሰክርም» ብለው መሰከሩ ይባላል።

## የመምህሩ ጸሎት

መምህር የተባለው ቅጽል የተሰጠኝ በማን ነው? በነቢያት (በጥንት ፈላስፎች) ይልቁንም በክርስቶስ (እሱ መምህር ዘበአማን፣ መምህረ ዓለም፣ ቀጥሎስ በሐዋርያት) መምህርነት የሚያኮራ ሥራ ነው እንደዘመኑ አነጋገር፣ እንደዘመኑ ሥልጣኔ፣ ያበላል አያበላም ሌላ ጉዳይ ነው። ለመንፈስ ኩራት ለሰው ልጅ ቀዋሚ አገልግሎት መምህርነት የመጀመሪያውን ደረጃ የያዘ ነው። ብበላ ባልበላ ሆዴ አምጣ ይለኛል አስተማሪነቴ ልብ ይሞላልኛል።

## አገር ቤቱ

ከራሩ ይደረደራል፣ መሰንቆው ይታኛል፤ አዝማሪው አደግድጎ እንዴትነሽ አገሬ ይላል፣ በየት? በአገር ቤቱ፣ በአገር ፍቅር ተመስጦና ተቃኝቶ ነው። አገር ቤቱ ታታሪ ያደርጋል፤ አገር ቤቱ ባህል ጠባቂ ሃይማኖት አክባሪ ያደርጋል። አገር ቤቱ ውሃ ዋናተኛ ፈረስ ጋላቢ ያደርጋል። አገር ቤቱ ቆፋሪ አራሽ ቸርቻሪ ያደርጋል። አገር ቤቱ በግድ ጥረትን ያስተምራል። አገር ቤቱ ኅብረትን ያስተምራል፤ አገር ቤቱ ተባብሮ መንገድ መከፈትን ያስጠናል፤ አገር ቤቱ ለሚሠራ ጀግና በተፈጥሮው ያመቹ ብዙ ነገሮች አሉት። አገር ቤቱ የእድገትን ዘመቻ ያስተምራል፤ አገር ቤቱ ለሰነፍ ያሸብራል፣ አገር ቤቱ ለትጉህ ከአዕዋፍና ከደኖቹ ጋር አዲስ ሕይወት ይሰጣል።

አገር ቤቱ በከተማ የሚለምኑና የሚቀላውጡ ሥራ ወደው ቢዘምቱበት ከልክስክስ ሥራና ከሰው ሸክምነት ይገላግላቸዋል። አገር ቤቱ ያልተማረውን ሁሉ መግቦ አሠርቶ የሚያሳድር ነው። ኢትዮጵያዊ ሁሉ ያገር ቤቱ ፍቅር ይደርብህ፤ ሰዎች የሠሩትን ሕንፃ እየቆጠርክ በከተማው ፍቅር ብትነብዝ የምታገኘው ነገር የለም።

የሥራ ጸሎት ከመንግሥቱ መኮንን
(መምህር አብራራው)

## ስለ ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ የመዝሙር ሰላምታ

ሰላም ይገባዋል ለዚህ ለቅዱስ ሰው
ባራዳ ገበያ ደሙን ላፈሰሰው።
እስቲ ሰላም ብዮ ስምህን ላነሳሳው
ያካለ ወልድ ልጅ የዚያ የሊቁ ሰው።
እመኑብኝ ቢለን ያ የሮማ ንጉሥ
አንገቱን ሰጠልን ሐዋርያው ጴጥሮስ
ጳውሎስ ተከናንቦ ሞትን ይደበቃል
ጴጥሮስ ለመትረየስ ደረቱን ይሰጣል።

(ተክስተ ብርሃን መጽሐፍ 1933 ዓ.ም ተቀንጭቦ የተወሰደ)

## የፍቅር መቋጫው

አባትና እናት ይወደዳሉ ወላጆች ናቸውና
ሚስት ትወደዳለች አካል ናትና
ልጅ ይወደዳል የሥጋ ቁራጭ ነውና
ወንድም ይወደዳል ክንድ ነውና
እህት ትወደዳለች የሥጋ አካፋይ ናትና
ገንዘብ ይወደዳል የሥጋ ሕይወት ነውና
ልብስ ይወደዳል የሥጋ ሞገስ ነውና
መብል፣ መጠጥ ይወደዳል የሥጋ መቋቋሚያ ነውና
መሬት ይወደዳል ታርሶ ይበላልና
ቤት ይወደዳል ዙር መግቢያ ነውና። ከእነዚህ አሥሩ በበለጠ የምትወደደው ግን ሀገር ናት። ሀገር ከሌለች ሁሉም አይኖሩምና።